በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

ህዳር/ታህሣስ ፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፬
$2.75
ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

# ላንዳፍታ




በዚህኛው እትም

**"ቀበጥ ሙሽራ ከወደ ፈረንጅ አገር"**

**"ሩዋንዳን ያደማት ማነው?"**

- በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች
- ኑሮ በአሜሪካ
- አዳምና ሔዋን አላለልኝ ይሆን
- ልብ ወለድ የዴብራ ጦስ ዕጣዬ

# LANDAFTA

*An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine*
*(Amharic is the official language of Ethiopia)*
November/December, 1994 Vol. 3. No.4





# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ው ጫ

# CONTENTS

2 ከአዘጋጁ

3 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወረቃየሁ)

6 እንዲህ ሆነ
ዜናዎች ከኢትዮጵያ
(ከኢትዮጵያ ወኪል)
"ሩዋንዳን ያደማት ማነው?" (ሰይፉ መኩሪያ)

12 ጥንቅር ከዚህም ከዚያም
አንድ ጥያቄ አለኝ!

19 ልብወለድ
የዴብራ ጦስ (ገረሱ)
ዕጣዬ (አብረኸት)

25 ኑሮ በአሜሪካ
ላንዳፍታን በሞቅታ (ጣጤው)
"የማወቅ ትርጉሙ . . ."(አይን ምስክር)

30 አዳምና ሔዋን
"ቀበጥ ሙሽራ ከወደ ፈረንጅ አገር" (አብዬ)
አላለልኝ ይሆን (ትዝታ አለብኝ)

37 ባላገርና ፖለቲካ (ከአለፈው የቀጠለ)

43 የግጥም ጉባኤ

46 ቢስቁም ባይስቁም

47 ጨዋታና ሰንጠረዥ



ፕሮፌሰር አሥራት (8)



የህገ መንግሥት ጉባኤ (7)



የሰላም ነፃ ሠራተኛ ማህበር (6)

ሽፋን - "ኩራት ኩራት አይልሽም ወይ?" ጋብቻ በአገራችን

"ላንዳፍታ" የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1994

ላንዳፍታ
፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፬
LANDAFTA
Nov/Dec 1994 V. III - No. 4

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Girma Zegeye*

**Distribution**

Atlanta, GA
- California Mart
- Sweet Auburn Grocery

Chicago, IL
- Ethio-Village Rest.
- Tesfaye B. (Hoddo)

Daton, OH
- Rainbow Cafe

Dallas, TX
- Maru Grocery
- ET. Beauty Supply

**Huston, TX**
- Rendevous Coffee

**L.A., CA**
- Merkato
- Damera

Oak Land, CA
- Albo-African Shop

San Jose, CA
- St. Claire news Stand

Seatle, WA
- Addis Cafe

St. Louis, MO
- A & Z Liquor

St. Paul, MN
- Merkato

Tampa, FL
- Ibex Ethiopian restaurant

**Washington D.C.**
- Addisu Gebeya
- Family Food Market
- Merkato Market
- Nini Market (Alex.)
- Tana (Silver Spring)

Windsor, Ontario
- Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax (404)728-9122

# ከአዘጋጁ

## አንባብያንን ይቅርታ እንጠይቃለን።

የላንዳፍታ መጽሄት የዚህ የህዳር/ታህሣስ እትም በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት የዘገየ መሆኑን እየለጽን ከእንግዲህ እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ በወቅቱ ለማውጣት ቃል እንገባለን። አንባብያን ላደረጋችሁልን ትዕግሥት ምስጋናችን ከፍትኛ ነው።

## ውድ አንባብያን

መጽሄታችንን በየጊዜው በምትሰጡን ምክር እያሻሻልን ከዚህ ደርሰናል። አምዶቻችን እንደቀድሞው ናቸው። በይቅጥላል ሰለሚቀርቡት ታሪኮች አንዳንድ አንባብያን የሰጣችሁንን አስተያየት በተግባር ለማዋል ጥረት እያደረግን ነን። የሚደርሱን የገጠመኝ ታሪኮች በጣም ረጃጅም ከሆኑ ያለን ምርጫ በዚሁ ልምድ መቀጠል ነው። አሁን የተጀመሩትን ታሪኮች እንደጨረስን ለወደፊቱ በአንድ ቢበዛ በሁለት ወይም ሶስት እትም የሚያልቁ ታሪኮችን ለመጻፍ አስብናል። ስለአምዶቻችን ያላችሁን አስትያየት አትንፍጉን፤ እናንት ውድ አንባብያንን የማያረካ ነገር ማቅረብ ዓላማውም የለንምና።

እስቲ እኛም አንድ ነገር እንለምናችሁ። መጽሄቷን አስተዋውቁልን። ኢትዮጵያውያን በሚገኙበት ቦታ ሁሉ ለማዳረስ የቻልነውን ያህል ጥረት ብናደርግም ያሰብነውን ያህል አልተሳካልንም። ስለዚህ እናንተም ባላችሁበት ቦታም ሆነ በሌላ አካባቢ የምታውቋቸውን ጓደኞቻችሁን ስምና አድራሻ ላኩልና እኛ እንላክላቸው። በአላችሁበት ቦታ ከአስር በላይ መጽሄት በማከፋፈል ለምትርዱን ሁሉ ኮሚሽን የምንከፍል በመሆናችን ደውሉልንና እንነጋገር። ይህችን የምትወዷት መጽሄት በስፋትና በጥረት እንድትቀጥል እናንተም አስተዋጽዎ አድርጉልን።

## የ1987 ዓ.ም. የቀን መቁጠሪያ በቅናሽ

በተዋባ ግራፊክስና ከለር ሰንድቅ ዓላማችንን ጨምሮ ያዘጋጀነውን ካሌንደር አይተውታል። አጽዋማትንና በዓላትን በደምብ ይገልጻል። የፈረንጆቹንና የኛን አቆጣጠር በትክክል ያሳያል። ለገና ስጦታ ሊሆን ይችላል። ዋጋው $4.00 ብር ብቻ ነው። አሉበት ቦታ ወይም በስጦታ መልክ እንዲደርስሎት የሚፈልጉበት ቦታ በመጀመሪያ ደረጃ የፖስታ አገልግሎት እንልክሎታለን። ከአስር በላይ በአንዴ ለሚገዛ እያንዳንዱ $3.40 ሳንቲም ይሆናል።

Send Money Order Payable to LANDAFTA

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

ለመሆኑ እንዴት ከርማችኋል? ለጤንነታችሁ እንደምናችሁ? ኑሮና ብልሃቱስ እንዴት ይዞአችኋል? እኛ ደህና ነን። እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነን። ክረምቱን ወጥተናል፤ መስቀልን ተኩሰናል፤ ደመራ አብርተናል። የሐምሌና የነሐሴ ጥቅጥቅ ጨለማ ጽልፎ ለመስከረም ብሩህ ቀናት በቅተናል። ይህቺን ነገ እበላታለሁ ብሎ በኮሮጆው ቋጥሮ አስፋልት ላይ ድፍት ብሎ የሚያድረው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከየስፍራው የቃረመውን ፍርፋሪ ጠራርጎ ከሚወስድበት ጎርፍ፣ እላዩ ላይ ከሚወርድበት ዶፍ እፎይ ብሏል።

የመስከረም አደይ አበባ ለጥቅምት አዝመራና እሸት ስፍራውን እየለቀቀ ነው። የመስከረሙ ብሩህ ቀናት ቆንጠጥ በሚያደርገው የጥቅምት የማለዳ ውርጭና የምሽት ብርድ እየተተካም ነው። የክረምቱ ዝናብ በመጠናቀቂያው ከባድ ዝናብ ጥሎ ብዙ የጎርፍ አደጋ አደረሰ። በአዲስ አበባ በፍልውኃ አካባቢ ብዙ ጎጆዎችን እየፈነቃቀለ የሳሎን ዕቃ፣ የማድ ቤት ኮተት፣ አልጋና ፍራሽ ሳይቀር እንደ ክፉ ዘራፊ ጠራርጎ ይዞ ነጎደ። ቤቱን ጎርፍ የወሰደበት እሪታውን ሲያቀልጥ፣ ሌላው ደግሞ ጎርፍ የሚያንከባልለውን ኮተት ለማስጣል፣ የተረፈ ዕቃ ቢኖር ለመመንተፍ የነበረው ውካታና ግርግር ነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ እንዲህ አልነበረም።

"የበላችው ያገሳታል በላይ በላዩ ያጎርሷታል" እንዲሉ ቀደም ሲል በነበረው ተፈናቃይ ላይ ጥቂት ሺህ ተፈናቃይ ዜጎች ተጨምረዋል። አቅም ያለው ከዶፍ የተረፈ ቤቱን ጠጋግኖ፣ ያልቻለም ትናንሽ የላስቲክና የሳጠራ ጎጆዎችን በየጥጋጥጉ ሰርቶ ኑሮን ተያይዞታል። ምርጫ የለም። የቸገረው እርጉዝ ያገባል ስትወልድበት ገደል ይገባል - ዛሬ ዛሬ የምትገባዋ እርጉዝ ላትገኝ ትችላለች። የሚገባበትም ገደል ላይገኝ ይችላል።

ከአዲስ አበባ ውጪ ወባ ክፉኛ ገኗል። ብዙ ሰው አጥመልምሎ የተወሰኑትንም ገድሏል። በወሎ፣ በሀብሮ ወረዳ፣ በዝዋይ አካባቢ፣ በአዋሽ አርባና በዱብቲ አካባቢ ከወትሮው በከፋ ሁኔታ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እየሞቱ ነው። ብቻ ይህ ሁሉ ሆኖ ደህና ነን። ደህና ነን እንላለን። መሽቶ ከነጋ ደህና ነን ነው የሚባለው። አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ ተያይዘነዋል። . . . አፈር ያልገባው የነሐሴ ቆፈን ጅማቱን ሸምቅቆ ከቤት ያላዋለው፣ የክረምቱ ዶፍ ከአፈር ያልቀላቀለው፣ መሰንበት ደጉ ረጅሙን የበጋውን ወራት ሐሩርና ቁር ለመቋቋም ደግሞ ይንከላወሳል። . . . ነጋዴው ለማትረፍ፣ ገበሬው አዝመራውን ለመሰብሰብ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሌላውም እንደየባሕሉና እንደየአቅሙ ሠርግ፣ ዳንኪራ፣ ጭፈራና ፈንጠዝያ ይሞክራል።

በየፈናው እየተርመሰመሰ ነው። DV-1 ሎተሪ የደረሳቸውም ፎርም ሲሞሉ፣ ፎቶ ኮፒ ሲያደርጉ፣ አሜሪካ አገር ላለ ዘመድ አዝማድ፣ ጓደኛ፣ ወዳጅ፣ ስልክ ሲመቱ ሃሎ፣ በጣም ሃሎ ሲሉ ሰንብተዋል። ከዚህ ጨለማ አገር፣ ከጨለማ ፖለቲካ ውልቅ ለማለት! . . . ግን የሚያልሙት የተስፋ ዓለም የገነለት አሜሪካ ዕውን ይሁን ሕልም ጊዜ ይለየዋል።ሹሞቻችንም በአዲስ ዓመት አዲስ ሩጫ ይዘዋል። ጊዜ የላቸውም። ተጣድፈዋል።

በመንገዳቸው ላይ የቆመ የሚመስላቸውን ሁሉ እየደፈጠጡ ይጣደፋሉ። ለዓይን የጠሉትን አፍሰው ወደ ከርቸሌ ይከታሉ። ወደ ሰንዳፋ ይወሽቁታል። ጠጉሩን በደረቁ ላጭተው እያዋረዱ ቢያስፈልግ ነፍስህም በእጃችን ነች ይሉታል። በባዶ እንጀቱ በስፖርት ይቀጡታል። ይህቺን "ሽግግር" የምትለዋን መጠሪያቸውን ወደ ቋሚነት ለውጠው "የተመረጡ ዲሞክራቶች" ለመባል፣ የሥልጣን ኮርቻዋን ለመቆናጠጥ፣ ለመደላደል ሽር ጉድ እያሉ ነው። እበላ ባዩ ግልገል ሹም ደግሞ እስር እስራቸው ኩት ኩት ይላል። ነግ በእኔ የማያውቀው ገልቱ በሹሞች ካልቾ ቅሰሙ በተሰበረው ላይ ያሾፋል። እንደልጅነቱ ተገዶ ጠጉሩን በተላጨው ላይ ይስቃል። ድህነት ያጠራሞተው ሕዝበ አሕዛብ እየተገፋም እየተዠለጠም ይከተላል። ሲጮሁበት እንደገደል ማሚቶ መልሶ ይጮሃል።

ሰሞኑን እየተቆጠርን ነው። በዘር ማንዘር፣ በጎሳ፣ በብሄር ብሄረሰብ እንቆጠራለን። ቅራቅንቦአችን፣ ኮተታችን ተቆጥሮ ይመዘገባል። ሜዳ ላይ የሚያድረው ኢትዮጵያዊ ደግሞ ከነዲሪቶው ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ይቆጠራል። አልቀረበትም። . . . ቁጥራችን ሳይበዛ እርባታችን ሳይበረክት አይቀርም ይባላል። 50 ሚሊዮን ስንባል የነበርን በዘንድሮው ቆጠራ ወደ 80 ሚሊዮን እንዳንደርስ ተፈርቷል።

ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? በየጊዜው እንዴት ናችሁ? እያልኩ ልቤ ይወልቃል! እንዲህ ነን የሚል ጎበዝ የለም። እንኳን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ሆነህ እዚህም ብትመጣ ገና ብዙ መናቅና ጥፍራም ሆነህ መገመት ሊኖርብህ ነው እንዳትሉኝ!

በፈረንጅ አገር ስላላችሁት ብዙ ብዙ እንሰማለን። በአሜሪካ፣ በአውሮፓ በተቀረውም አገር ያሉ ኢትዮጵያውያኖች ስለመቱት የረሃብ አድማ፣ ስላደረጉት የድጋፍና የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ፣ ለዓለም ስለሚያሰሙት ጩኸት፣ ስላበሩት የሻማ መብራት ተማፅኖ (Candle Vigil) ብዙ

እንሰማለን። በህብረትና በአንድነት መቆማችሁን እንደየነገራችን እንተረጉመዋለን። ደግሞም ትናናቃላችሁ ይባላል። . . . የተማረ–ያልተማረ፣ ፈረንጅ አገር የሰነበተ–በቅርቡ የመጣ፣ . . . የሙያ ሥራ የሚሰራ፣ በተገኘ በምናምኑ የሚንጠላጠል . . . ወዘተ እየተባባላችሁ ትናቆራላችሁ ይባላል። የተማረው ክፍል ሁሉን አውቃለሁ ይላል አሉ። ቲፎዞ ለማብዛት ባለ ብዙ clique ለመሆን ሽር ጉድ ነው አሉ። የሌላውን አስተያየትና ዕምነት ከቁም ነገር ሳይጥፍ የራሱን አቋምና እምነት ብቻ ተቀበሉኝ ለማለት ይዳዳዋል ይባላል። አሜሪካ የሰነባበተው ደግሞ One doesn't make a mistake if stayed long in US እያለ በቅርብ የመጣውን ስደተኛ በንቀት ዓይን የጎንዮሽ ያየዋል አሉ። በየምኑ በየምክንያቱ ትናናቃላችሁ ትናቆራላችሁ ይባላል። እንሰማለን።

ለመሆኑ ከሠላማዊ ሰልፉ መልስ – ከሻማ ተማፅኖው በኋላ ይሆን መናናቁ መናቆሩ የሚጀመረው? . . . እንዴት ሆኖ ነው አሜሪካ አገር ብዙ የኖረ አይሳሳትም የሚባለው? እውን አይሳሳትም? ወይስ ስደት ለወሬ ያመቻል መሆኑ ነው? እንዴት ቢቀብጥ ነው የተማረ የተመራመረው ትምህርት ያልሆነለትን ወገኑን ዝቅ አድርጎ ቁልቁል የሚያየው? እኔን ብቻ ስሙኝ የሚለው? እንዴትስ ሆኖ ነው አሜሪካ ገና የደረሰው ምንም የማያውቅ ጥፍራም ባላገር ሆኖ የሚቆጠረው? የተማረ ያልተማረ ወገኑን ሲንቅ፣ በፈረንጅ ምድር የሰነባበተው በአዲስ መጪው ላይ ሁሉን እንደሚያውቅ ሆኖ ሲቆናጠር የጋራ የሆነው ትልቁ ነገር "ህብረት" አይጎዳ ይሆን? የተማረው ባልተማረው ሲስቅ፣ ያልተማረውም በተራው ያንጓጥጣል። አናንቆ ያላግጣል።፣ አንዱ ሌላውን ቁልቁል ሲያየው በወዳጅ ዘንድ ማሳፈሩ በጠላትም ፊት ማስናቁ ይቀራል? የናቁት ሰፈር በአህያ ይወረራል እንደሚባለው የተረት ተረት የእንቆቅልሽ አገር የእንቆቅልሽ ልጆች እያደርጋችሁ ይሆን?

. . . ገበያ እንዴት ዋለ ቢሉ አንዱ በአንዱ ሲስቅ እንደማለት መሆኑም አይደል!!!

ይሄ ሁሉ የአሉ አሉ፣ የሰሚ ሰሚ፣ ያልነበረ የሌለ ነው የምትሉኝ ከሆነ በሉ እርፌ እንድቀመጥ ልክ ልኬን ንገሩኝ!

በቸር ይግጠመን።
የናንተው ወርቋየሁ

# ይህን እንመስላለን !!



የተለያዩ

ገፅታዎቻችን







## የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ለሁለት ተከፈለ።

### ወሳኝ ጠቅላላ ስብሰባ ሰሞኑን ያካሂዳል።

በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) የሥራ አስፈፃሚ አባላት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ኮንፌዴሬሽኑ ለሁለት ተከፍሏል። የአለመግባባቱ መነሻ የኢኮኖሚ መዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም መንግሥት በወሰደው የሠራተኛ ቅነሣ እርምጃዎች ላይ የአቋም ልዩነት በመፈጠሩ ነው። የአቋም ልዩነቱ መፈጠር ይፋ የሆነው የኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ዳዊ ኢብራሂም መንግስት እያካሄደ ያለውን የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ሰራተኛው ያልተሳተፈበት በአለም ባንክ፣ በአለም አቀፍና የገንዘብ ድርጅቶች ግፊት የሚካሄድ በማለት ጋዜጣዊ መግለጫ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

የዚህ አንጃ አቋም የመንግስትን ፖሊሲ የሚደግፍ ሲሆን ችግሮችም ቢኖሩ ከመንግሥት ጋር በሰላም ለመደራደር እፈልጋለሁ ባይ ነው። ይህ አንጃ በብዙሃኑ ሰራተኛ ዘንድ ድጋፍ ባይኖረውም ከፍተኛ የመንግሥት ድጋፍና እይዞህ ባይነት እንዳለው የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና በመንግሥት ሚዲያ የተሰጠው ሰፊ ጊዜ ምስክር ነው ሲሉ ብዙ ወገኖች የዚህን ቡድን የመንግስት ወገንነት በእርግጠኝነት ይናገራሉ። የተቀሩትን 80 አባላት የያዘውና በአቶ ዳዊ የሚመራው ቡድን ደግሞ ኮንፌዴሬሽኑ ከመንግስት ጋር ለመደራደር ያደረገው ጥረት ምላሽ የተነፈገው ስለሆነ ሠራተኛው ለመብቱና ለሥራው ዋስትና መከበር ክንዱን ማስተባበር አለበት የሚል አቋም አለው።



አቶ ዳዊ ኢብራሂም
የኢ ሠ ማ ኮንፌዴሬሺን ሊቀመንበር



ከኢ ሠ ማ ኮንፌዴሬሽን የታገደውና ራሱን "የሰላምና የነፃ ሠራተኛ ማኅበር" ብሎ የሰየመው ቡድን ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ

መግለጫው እንደተሰጠ የአንዳንድ ድርጅቶች የሠራተኛ ማሕበራት የተቃውሞ መግለጫ አውጥተዋል። በተቃውሞ መግለጫዎቻቸው የመዋቅር ማስተካከያውን ፕሮግራም በጉጉት ስንጠብቀው የነበረ በማለት አቋማቸውን የገለጹም ማኅበራትም ነበሩ። ከኋላ አንዳች የፖለቲካ ተፅዕኖና ግፊት ሳይኖር ይህን መሰሉ መግለጫ የሠራተኛ ማኅበራት አቋም ነው ለማለት ያስቸግራል። ቀጥሎም ለ11 ቀናት በተካሄደው የኮንፌዴሬሽኑ ስብሰባ መሣሪያ እስከመማዘዝ በደረሰ አለመግባባትና ፍጭት ተካሄደ። በመጨረሻም ፀሐፊውን ጨምሮ 23 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ታግደዋል። የታገዱት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት 80፝ ያህሉ ከአንድ ብሄረሰብ የወጡናቸው የሚል ፍንጭ እንዳለ ሆኖ "የሠላምና የነፃ ማኅበር ፈላጊ" በማለት ተደራጅተው በኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ላይ ክስ መስርተዋል። የኮንፌዴሬሽኑም የባንክ ሂሳብ በፍ/ቤት ውሳኔ ታግዷል።

የሽግግር መንግሥቱ አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን በሰጡት መግለጫ በመዋቅር ማስተካከያው ፕሮግራም መነሻ የተፈናቀለ ሠራተኛ የለም ሲሉ ተናግረዋል። ስድስት ሺ ያህል ሠራተኞች ተፈናቅለዋል የሚለውን የኢሠማኮ ስሞታ ግን በዝርዝር አላብራሩትም። ይህ በዚህ እንዳለ ጥቅምት 25 ቀን የኢሠማኮ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቷል። በአንጃነት የወጣው ቡድን የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮቻቸውን እንዳይልኩ በመንግሥት ሚዲያ በስፋት በመቀስቀስ ላይ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ማኔጅመንቱ ጣልቃ በመግባት በአቶ ዳዊ በሚመራው ቡድን ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውን ሠራተኞች ከሥራ በማሰናበት ላይ ይገኛል። የጠቅላላ ስብሰባው መካሄድ የመንግሥትን የፖለቲካ ጥቅም ስለሚጎዳ ስብሰባው እንዳይሳካ ብዙ ርብርቦሽ ሊደረግ ይችል ይሆናል ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ። በኢሠማኮ ውስጥ የተፈጠረው አንጃም ሆነ ከዚያ በኋላ እየተደረጉ

ያሉት እንቅስቃሴዎች ኢሕአዴግ የሠራተኛውን ማሕበር ከጎኑ ለማሰለፍ በሠርጎ ገቦች አማካይነት የፈጠረው ትርምስ ነው ሲሉ ተቃዋሚ ወገኖች ይተቻሉ።በመጨረሻ በደረሰን ዜና በሁለቱ የኢሠማኮ አንጃዎች መካከል ስምምነት እስከሚደረስ ድረስ ሁለቱም ወገኖች ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍ/ቤት አግዷል።

## የሕገ መንግስት ጉባኤ በይፋ ሥራውን ጀመረ

### ተቃዋሚዎች በመጪው ምርጫ አይሳተፉም

የወደፊቱን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የሚያፀድቀው የሕገ-መንግሥቱ ጉባኤ በይፋ ስራውን ጀምሯል። ይህ ጉባኤ በሕገመንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን የተዘጋጀውን ረቂቅ ሕገመንግሥት ሙሉ-ለሙሉ ለማጽደቅ ወይም እንዳለ ለመጣል ወይም ማሻሻያዎችን ሊያደርግ ስልጣን አለው ተብሏል። በግንቦት 28ቱ ምርጫ ለተመረጡት ለእነዚህ የሕገ-መንግሥት ጉባኤ አባላት ፕሬዚዳንት መለስ ባደረጉት ንግግር የሕገ-መንግሥት ማርቀቁን ሂደትና ሕገመንግሥቱን ራሱን እስካሁን ከተዘጋጁት ሕገመንግስቶች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ብለውታል።



ፕሬዚዳንት መለስ የሕገ መንግሥቱን ጉባኤ በንግግር ሲከፍቱ

እንደታዛቢዎች ግምት ኢሕአዴግ 90% የሚደርስ ድምፅ በጉባኤው ውስጥ የያዘ በመሆኑ የብሄረሰቦች ዕድል እስከመገንጠልና ሌሎች አወዛጋቢ የሕገ-መንግስቱ አንቀጾች ያለ አንዳች ተቃውሞ እንደሚፀድቁ ይናገራሉ። 22 ድርጅቶችን በማቀፍ በጉባኤው ውስጥ ከፍተኛ ድምፅ የያዘው ኢሕአዲግ የሕገ-መንግስቱን ይዘት በሚፈልገው መንገድ ለማስኬድ እንደሚቻለው የሚተነብዩት የፖለቲካ ታዛቢዎች አሁን የሚደረገውን ጉባኤ የቴክኒክ እንጂ የይዘት አይደለም ይላሉ። በሕገ መንግሥት ዝግጅቱም ሆነ እየተካሄደ ባለው ጉባኤ ላይ ያልተካፈሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች በመጪው ጥር ወይም የካቲት ይደረጋል በተባለው ጠቅላላ ምርጫ እንደማይሳተፉ አስታውቀዋል።በዚህ ረገድ ኢድኃቅ ባወጣው መግለጫ የአስተዳደር አውታሮችና የመከላከያ ሰራዊቱ ከኢሕአዲግ ተፅዕኖ ካልተላቀቁ የሚካሄደው ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ እንደማይሆን በመግለጽ በምርጫው እንደማይሳተፍ አሳውቋል። ከዚህም ሌላ ኦነግ፣ የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት፣ መድኅንና ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ሕገመንግስቱን ከማጽደቅና ጠቅላላ ምርጫ በአገሪቱ ላይ ከመካሄዱ በፊት ያቀረቧቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟላ በመጠየቅ በምርጫው ላይ እንደማይሳተፍ አስታውቀዋል።

ተቃዋሚ ኃይሎችን ከሽግግር መንግስቱ ጋር ለማቀራረብና በመጪውም ምርጫ እንዲሳተፉ ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩት የቀድሞ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው የመሳተፍ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ከአንድ የውጭ ዜና አውታር ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ተናግረዋል። እንደርሳቸውም አባባል ተቃዋሚ ድርጅቶች ከምርጫው ራሳቸውን ማግለላቸው ታላቅ ስህተት ነው ይላሉ።

የኢትዮጵያን የወደፊት ዕድል ሊያሳምሩ የሚችሉት ከሆነ በአሸናፊነት ካልሆነ በተቃዋሚ ተሸናፊነት በሚኖራቸው ሚና ነው በማለት ተቃዋሚዎች በመጪው ምርጫ ቀደም ሲል የሰሩትን ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደግሙ አሳስበዋል። ይህን የሚ/ር ካርተር አቋም ተቃዋሚ ድርጅቶች የማይቀበሉት ሲሆን የፖለቲካ ተንታኞችም የታዳጊ አገሮችን እምባገነናዊ ባሕርይ ካለመረዳት ወይም ለመረዳት ካለመፈለግ የተሰነዘረ ወደ አንድ ወገን ያደላ ሲሉ ይተቻሉ።

## በቀድሞ መንግሥት ባለስልጣኖች ላይ ክስ ተመሠረተ

ከመስከረም 1987 ዓ.ም ጀምሮ ለፍርድ ይቀርባሉ የተባሉት የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣኖች ጉዳይ እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ ድረስ ዘግይቶ የክሱ ቻርጅ ለፍ/ቤት መቅረቡን የልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ አስታውቋል። የቀድሞውን መሪ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ በሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ የቀረበው 269 ገጽ የያዘ የክስ ቻርጅ በማስረጃ የተረጋገጡ በሚታወቁ 1823 ሰዎች ላይ ለተፈፀመው ግድያና በ99 ሰዎች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። በመጀመሪያው ዙር ክስ የተመሠረተባቸው እነዚህ የቀድሞ ባለሥልጣኖች የደርግ አባላት የነበሩ መሆኑ ሲገለጽ በሌሎችም ላይ በተከታታይነት ክስ መመስረቱ እንደሚቀጥል ልዩ አቃቤ ሕጉ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል የቀድሞ ባለሥልጣኖች ፍ/ቤት ቀርበው ጥፋታቸው ተረጋግጦ የሚሰጣቸውን ውሳኔ ከማወቃቸው በፊት እየሞቱ መሆኑ ተዘግቧል። በዚህ መሰረት የቀድሞው ፕሬዚዳንት ልዩ ረዳት የነበሩት መንግስቱ ገመቹ፣ የልዩ ጥበቃ ኃላፊ የነበሩት ሻለቃ ደመቀ ባንጃው፣ ጄኔራል አስራት ብሩን ጨምሮ በርካታ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት በእስር ላይ እንዳሉ በሞት ተለይተዋል። በተያያዘ ሌላ ዜና በኢጣሊያ ኤምባሲ በጥገኝነት የሚገኙት የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር በኋላም ከፕሬዚዳንት መንግሥቱ መኮብለል ቀጥሎ ባሉት ቀናት የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን በሞት አፋፍ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል።

## ፕሮፌሰር አሥራት በሌላ ክስ ፍ/ቤት እየተመላለሱ ነው

ዕውቁ የሕክምና ባለሙያና የመአህድ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ሕዝብን በሕዝብ ላይ በማነሳሳት የጦረኛነት ወንጀል በተመሠረተባቸው ሌላ ክስ ምክንያት ከታሰሩበት ወህኒ ቤት ፍ/ቤት በመመላለስ ላይ ይገኛሉ። መስከረም 26 ቀን 1987 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፕሮፌሰሩ ከአሁን በኋላ የዳኞችን ህሊና ላለማስጨነቅና በደጋፊዎቻቸው ላይ የሚደርሰውን ዱላና እስራት ላለማየት፣ ተጨማሪ ክርክር ላለማንሳት ጠበቆቻቸውን ያሰናበቱ መሆኑን ገልፀው ሊፈፀምባቸው የታቀደውን ውሳኔ እንዲያሰሙአቸው ዳኞቹን ጠይቀዋል። ፕሮፌሰሩ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ማመልከቻቸው "እምባገነናዊ በሆነ፣ ጎሰኝነትን መመሪያው ባደረገና የፖለቲካ አየሩ በቂምና በቀል በተመረዘ ሥርዓት ውስጥ የሕግ የበላይነት ይኖራል፣ የዳኝነት ነፃነት ይከበራል ማለት ስለማይቻል በፈጠራ ተቀነባብሮ በቀረበባቸው ክስ ጠበቃ አቁመው መከራከሩ ውጤት አልባ ነው" ሲሉ አስታውቀዋል።

ፕሮፌሰሩን ለዚህ ውሳኔ ያደረሳቸው በቀጠሮአቸው ዕለት መስከረም 10 ቀን 1987 ዓ.ም በከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ መንግሥት በደጋፊዎቻቸው ላይ የወሰደው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል። የራሴን ጠበቆች አሰናብቻለሁ ፍ/ቤቱም ሌላ ጠበቃ እንዲያቆምልኝ አልፈልግም ባሉበት በዚህ ማመልከቻቸው በሰላማዊ መንገድ ድጋፉን ለመግለጽና ቅሬታውን ለማሰማት በየቀጠሮው የሚሰበሰበው ሕዝብ በእርሳቸው ምክንያት አስቃቂ ግፍ ሲፈፅምበት ማየትና መስማት እንደማይችሉ ግልጽ አድርገዋል። በተያያዘ ዜና የፕሮፌሰሩን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ዜናውን የዘገበው የጦቢያ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የፍ/ቤቱን ክብር የሚነካና የፍትህ ስርዓቱን የሚዘልፍ ጽሁፍ አትመው አሰራጭተዋል የሚል ክስ ተመስርቶባቸው የስድስት ወር እስራት ተፈርዶባቸው ከርቸሌ ወርደዋል።

መስከረም 10 ቀን 1987 ዓ.ም ከፍተኛው ፍ/ቤት በሺህ የሚቆጠሩ የመአህድ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ሌሎች ተመልካቾች መሣሪያ በታጠቁ ፖሊሶች ታፍሰው መታሰራቸው የሚታወቅ ሲሆን በእስረኞች ላይ ስለተፈጸመው ድርጊት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶችና የዓለም ሕብተረሰብ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። ሁኔታውን የተከታተሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች መንግሥት መአህድን ለማጥፋትና ለማዳከም የፍትህ አካሎችን እያዘመተ ነው ሲሉ ይተቻሉ።

ዘግይቶ በደረሰን ዜና ፕሮፌሰር አሥራት ባቀረቡት ማመልከቻ ችሎት ደፍረዋል ተብለው ሌላ ተጨማሪ ስድስት ወር የተፈረደባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።



ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ

## ከፍርድ አደባባይ የታፈሱት መግለጫ ሰጡ

መስከረም 10 ቀን 1987 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅጥር ግቢ የፕሮፌሰር አሥራትን ክስ የችሎት ሂደት ለመከታተል ሂደው የነበሩ የመአህድ ደጋፊዎችና ሌሎች ታጋቾች በእስር ላይ ለቆዩበት 25 ቀናት ስለደረሰባቸው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በሒልተን ሆቴል መግለጫ ሰጥቸዋል።

ለዲፕሎማቶች፣ ለሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና ለጋዜጠኞች በተሰጠው በዚህ መግለጫ:-

▶ አንድ ቀን ሙሉ ያለ አንዳች መጠለያ በዕለቱ የነበረው ዝናብና ብርድ በላያቸው ወርዶ ያለ ምሳና ውኃ እንዲውሉ መደረጉን፣ መፀዳጃ ቤት መከልከላቸውን፣

▶ ቀሳፊው የኤድስ በሽታ እጅግ በሚያስፈራ ሁኔታ በተስፋፋበት በዚህ ወቅት በአንድ ምላጭ ሁለትና ሶስት ሰው እንዲላጭ በማድረግ በመሣሪያ በማስገደድ ፀጉራቸው በደረቁ መላጨቱን፣

▶ ከቤተሰብና ከጠበቃ ጋር እንዳይገ ናኙ፣ ለህመማቸው ማስታገሻ የሚወስዱትን መድሃኒት እንዳያገኙ መደረጋቸውን፣

▶ ጢት ጢት በውርጭና በብርድ የአካል ቅጣት እንዲቀበሉ መደረጋቸውን በመጥቀስ ሰብአዊ ክብራቸውን በማዋረድና በመድፈር ኢሰብአዊ ድርጊቶች በመንግሥት ተፈጽሞብናል ሲሉ አማረዋል። 1500 የሚሆኑ የመአህድ ደጋፊዎች፣

በቀጠሮና በሌላ ጉዳይ በዕለቱ በፍ/ቤቱ የተገኙ ግለሰቦች የታሰሩት ሳያስፈቅዱ ሠላማዊ ሰልፍ በመውጣታቸው ነው ሲሉ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሲያስታውቁ ቁጥራቸውንም ከ450 የማይበልጡ ብለዋቸዋል። አምባሳደር ዮዲት ዕምሩን ጨምሮ በርካታ አዛውንቶች፣ ሴቶችና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላቸው በርካታ ግለሰቦች ላይ መንግስት የወሰደውን እርምጃ በማንአለብኝነትና በሕገ-ወጥነት የተፈፀመ ነው ሲሉ ተቃዋሚ ድርጅቶችና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች አውግዘውታል።

ታሳሪዎቹ ደረሰብን ለሚሉት ሕገ-ወጥ ድርጊት በመንግሥት በኩል ምንም ማስተባበያ ያልተሰጠ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ፕሬዚዳንት መለስን ጨምሮ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከአሜሪካው አምባሳደር ሚ/ር ሂክስ ጋር ሳይነጋገሩ እንዳልቀረ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይጠቁማሉ። መንግሥት ይህን መሰሉን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የፈፀመው በአሜሪካ ጉብኝታቸው ወቅት በፕሬዚዳንት መለስና በተከታዮቻቸው ላይ የደረሰውን ጥቃት ለመበቀል ሳይሆን አይቀርም በማለት የፖለቲካ ታዛቢዎች የራሳቸውን ግምት ሰጥተዋል። ምናልባትም ጠቅላላ ምርጫ ተደርጎ ኢሕአዴግ ስልጣኑን በዘላቂነት እስከሚያደላድል ድረስ ቁጡና እስካሁን ከሚታየው ይበልጥ ሰብዓዊ መብትን የሚደፍር ሊሆን እንደሚችልም ይተነብያሉ።

## በደብረታቦር እንግሊዛውያን ታፍነው ነበር

በደብረ ታቦር አካባቢ ሲዘዋወሩ የነበሩ ባልና ሚስት እንግሊዛውያን ባልታወቁ ፀረ-ኢሕአዴግ ኃይሎች መስከረም 26 ቀን 1987 ዓ.ም ታፍነው እንደነበረና ምንም አደጋ ሳይደርስባቸውና ሳይንገላቱ ጥቅምት 2 ቀን መለቀቃቸውን የዜና ምንጮች ዘግበዋል። ግለሰቦቹን ያፈነው ኃይል በወቅቱ ምንም የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከሽግግሩ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት እንዳላጋጠመውና መጠኑ በውል ያልታወቀ ገንዘብም መውሰዱን የዜና ምንጮች ገልፀዋል።

ሁለቱ እንግሊዛውያን እንደተያዙ በእንግሊዝ ኢምባሲና በሽግግር መንግስቱ ባለስልጣናት አማካኝነት ብዙ ጥረት መደረጉ ሲታወቅ አጋቾቹ ማንነታቸውን አለመግለጣቸውና ክፍያ (ransom) አለመጠየቃቸው ተጠቅሷል።

እንግሊዛውያኑ ባልና ሚስት መግለጫ ለመስጠት እንደማይፈልጉና የደረሰውን ሁኔታ ግን አገራቸው ሲደርሱ በዝርዝር እንደሚያቀርቡ ፍንጭ ሰጥተዋል። እንግሊዛውያኑን በቁጥጥር ስር አውሎ የነበረው ታጣቂ ማንነት በኦፊሴል ባይገለጥም በደብረ ታቦርና አካባቢዋ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ጀኔራል ኃይሌ መለስ የሚመሩት ቡድን ሕልውናውን ለማሳወቅ ያደረገው ሳይሆን እንደማይቀር ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገምታሉ። ይህንንም በማድረግ በኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ ሰፍኗል እየተባለ በስፋት የሚነገረው ፕሮፖጋንዳ ስህተት መሆኑን ለማሳየትና በሽግግር መንግስቱ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደርም ጭምር ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል። ሁኔታውን ከ18 ዓመት በፊት የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር በትግራይ ክፍለሀገር እንቅስቃሴ ሲጀምር ሕልውናውን ለማሳወቅ ታይለር የተባሉ እንግሊዛዊ ባልና ሚስት ከማገቱ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን ዜናውን ያሰራጩት ምንጮች ገልፀዋል።

በሐረርጌ ምዕራባዊ ዞን የኬር ኢትዮጵያ ሰራተኛ በኦነግ ተጠልፈው ከተወሰኑ ቀናት ፍለጋና መሯሯጥ በኋላ የጤንነት ጉድለትና ችግር ሳይደርስባቸው መለቀቃቸው ታውቋል።

## ኤርትራና ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነፃ ለመገበያየት ስምምነት ተፈራረሙ

ከነፃይቱ አገር ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩም ሆነ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚገቡ ሸቀጦች፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርቶች ካለአንዳች ቀረጥ በነፃ እንዲገቡና እንዲወጡ የሚያስችል የኢኮኖሚ ውል ስምምነት መደረጉ ተገለጠ።

በዚህ ውል መሰረት ከአንደኛው አገር ወደ አንደኛው አገር ለሚላኩትም ሆነ ለሚወጡት ሸቀጦች የሚጠየቀው በአንደኛው አገር ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ባለው ማንኛውም ነጋዴ በህጋዊ መንገድ መገዛታቸውንና በሚታወቁ ኬላዎች ማለፋቸውን ብቻ ነው። ከሌሎች አገሮች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦች ላይ የሚጣለው የገቢ ንግድ ታክስ ወይም በኤክስፖርት ሸቀጦች ላይ የሚከፈለው የውጪ ንግድ ታክስ አይመለከታቸውም።

የመንግስት ባለስልጣኖች የተደረገውን ስምምነት ለሁለቱም አገሮች የጋራ ዕድገት የሚበጅ በማለት ሲያሞካሹት የኢኮኖሚ አዋቂዎች ደግሞ ለአንድ ወገን ያጋደለ ኢትዮጵያን ለኤርትራ ለማጉረስ ግዴታ የገባችበት ስምምነት ሲሉ አጥላልተውታል።

ከጨውና ከክብሪት ሌላ ሁነኛ የኢንዱስትሪ ምርት ከሌላት ኤርትራ ኢትዮጵያ የምታገኘው ጥቅም እንደማይኖር በመጥቀስ ኢትዮጵያ ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ቆዳና ሌጦ፣ ልዩ ልዩ ማዕድናት ወደ ኤርትራ በገፍ እንዲጓጓዝ ለማድረግና የኢትዮጵያውያንን ገበያ የኤርትራ ሸቀጦች ማራገፊያ ለማድረግ የታቀደ ኢትዮጵያን የማጥፋቱ አንዱ አይነተኛ መንገድ ነው በማለት በርካታ ኢትዮጵያውያን ስምምነቱን አይደግፉትም። በእርግጥም በዚህ ስምምነት አዲሲቱ አገር ኤርትራ ካለ አንዳች የውጪ ምንዛሪና ወጪ፣ ካለአንዳች ቀረጥ ከኢትዮጵያ በሚፈልስላት የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርት ያለባትን የምርት እጥረት ማካካስ እንደሚቻላትና ከቡና ከቆዳና ሌጦ ላኪዎች አገሮች መካከል አንደኛዋ ልትሆንና የውጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅሟም በኢትዮጵያ ኪሣራ ሊያድግ እንደሚችል ይታመናል። ኤርትራውያን የመከላከያ ሰራዊቱን አመራር ጨምሮ የፖሊሲ አወጪነትና ቁልፍ የሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ኃላፊነት ቦታዎችን በያዙበት ሁኔታ ኢትዮጵያ ይህን መሰሉን የውል ስምምነት ማድረጓ ሊያስገርም እንደማይገባ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይተቻሉ።

በሌላ ዜና ኤርትራ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተገንጥላ የራሷን ጳጳሳት ወደ ግብፅ ልካ የጳጳስነት ማዕረግ እንዲያገኙ ማድረጓ ተዘግቧል።

## በሺ የሚቆጠሩ ዜጎች በፍርሃት ውስጥ ናቸው

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሠመጉ) ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ያለ ፍርድና ያለ ፍትሕ በእስር ቤት በመታጎራቸው፣ በመደብደባቸውና በመገደዳቸው የተነሣ አብዛኛው ሕዝብ ዛሬም በፍርሃት በመሸማቀቅ የሚኖር መሆኑን አረጋገጡ። ፕሮፌሰሩ ይህን የገለጹት ለኢሠመጉ አባሎች ጠቅላላ ስብሰባ ባቀረቡት ሪፖርት ሲሆን በ1986 ዓ.ም ብቻ ከ3,300 በላይ አቤቱታዎች ለኢሠመጉ እንደደረሱት ገልፀዋል። አሁን ያለው የሽግግር መንግስት ለሕዝብ ያለበትን ኃላፊነት ሁሉ ለዕርዳታ ሰጪ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ያስረከበና ልመናውንም እንኳ በሞኖፖል ለመያዝ ከባድ ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝ ነው በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ "ከጅብ ዋሻ ወጥቶ ከጅብ ዋሻ ገብቷል።" ሲሉ ሀገሪቱ በአሳፋሪ ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ በሪፖርታቸው ገልፀዋል።

በተያያዘ ዜና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው መግለጫ የሽግግሩ መንግሥት በመቶ የሚቆጠሩ የተቃዋሚ ቡድኖች አባላትን በማፈን፣ በማሳደድና በማሰር ላይ መሆኑን ጠቅሶ ግለሰቦቹ በአስቸኳይ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ወይም እንዲፈቱ የሽግግር መንግስቱን ባለስልጣኖች ተማጽኗል። በዚህም መግለጫው የታሰሩና የደረሱበት ያልታወቀ ግለሰቦችንና ግድያ የተፈፀመባቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር አውጥቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ዜጎች እንደወጡ በመቅረት መታፈንና ግድያ እንደተፈፀመባቸው የተለያየ የዜና ምንጮች ከመዘገባቸው ሌላ አባሎቻቸው የታፈኑባቸው የፖለቲካ ድርጅቶችም የተቃውሞ መግለጫዎችን አውጥተዋል። በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሰሜን ሸዋና በአምቦ ያለ ምንም ጥያቄ ግለሰቦች በጅምላ መታሰራቸውና እንደወጡ መቅረትም የተለመደ ክስተት እየሆነ መምጣቱን የአካባቢው ነዋሪዎች በምሬት ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት ባወጣው መግለጫ ከደርግ ጊዜ ባላነሰ ሁኔታ በዜጎች ላይ ሰቆቃ እየተፈፀመ መሆኑን ገልጾ ለዚህም ተጠያቂው ኢሕአዲግ ነው ሲል የመንግሥት ባለሥልጣናት ከሕግ በላይ መሆን በአስቸኳይ እንዲቆም ጠይቋል። የኢሕአዲግ መንግሥት ከምንግዜውም በበለጠ ወደ ፍፁም አምባገነንነት እየተሸጋገረ ነው በተባለበት በዚህ መግለጫ በፖለቲካ እምነታቸው ብቻ በርካታ የደቡብ ህብረት፣ የመኢህድ፣ የኦነግ፣ የኢህአፓና የሌሎች ድርጅቶች ደጋፊዎችና አባላት ከያሉበት ተለቅመው በእስር ቤት እንደሚማቅቁ ይፋ አድርጓል። በፖለቲካ ፓርቲነት ተመዝግቦ ሕጋዊ ዕውቅና የተሰጠው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት አዲስ የማሳደድና የእሥራት ዘመቻ በአባላቱ ላይ መከፈቱን ገልጾ የዘጠና ሰባቱን ስም ዝርዝር ለመንግሥት አቅርቧል። ስለሚቀርብበትም ይህን መሰሉ በመንግስት በኩል የተሰጠ ማስተባበያ ግን የለም።

## በሰሜን ሸዋ ግጭቶች አልበረዱም

በሰሜን ሸዋ ክልል በመንዝ፣ በጅሩ፣ በመርሐቤቴና አካባቢው በሽግግር መንግሥቱ ሰራዊትና በአማፂያን መካከል የሚደረገው የመሣሪያ ቁርቋስና ግጭቶች እየተባባሱና እየከፉ መሄዳቸውን ከአካባቢው የሚደርሱ ዘገባዎች ይጠቁማሉ። መንግሥት ሽፍታዎች ናቸው በሚላቸው እየመካኙ በሰላማዊው ነዋሪ ላይ ጭፍጨፋና ኢሰብአዊ ድርጊቶች በማድረስ ላይ ስለመሆኑ የተለያዩ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። እንደዜና ምንጮቹ ዘገባ በመንግሥት ሰራዊት ላይ የሞትና የመቁሰል ጉዳት ያደረሱ ግጭቶች ተካሂደዋል።

ከመንግሥት በኩል በኦፊሴል የተሰጠ መግለጫ ባይኖርም አንድ የሰሜን ሸዋ አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን በክልላቸው ከአዲስ አበባ የተሻለ ሰላም እንዳለ ሰሞኑን ለመንግሥት ሚዲያ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል።

በተያያዘ ሌላ ዜና ሐረር በሚገኘው የቢራ ፋብሪካ ላይ ማንነታቸው ባልታዋቀ ታጣቂ ኃይሎች ጥቃት መድረሱ ተዘግቧል። መንገደኞችና ተሽከርካሪዎች በታጣቂዎች የተዘረፉበትና የተጎዱበት በርካታ ሁኔታዎች ተዘግበዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሰሞኑን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በክልላቸው የታጠቀ ሰራዊትም ሆነ ነፃ መሬት ያለው ድርጅት የለም ሲሉ ገልፀው ለ20 ዓመታት ለኦሮሞ ሕዝብ መብት መከበር እየታገልኩ ነው የሚለው ኦነግ ተራ ሽፍታ ነው ሲሉ ተናግረዋል። ይህ አባባላቸው ኦነግ እያካሄድኩ ነው የሚለውን የትጥቅ ትግል መካዳቸው እንደሆነ ሲገመት በኦሮሞ ልሣን ተጠቅሞ ብሄራዊ ትግሉን ማንቋሸሽ ነው ሲል ኦነግ በበኩሉ መግለጫውን አውግዟል።

በተያያዘ ሌላ ዜና ኦነግ ባወጣው መግለጫ ያቀረባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ተቀባይነት ሳያገኙ ሰላምና ዕርቅ ከቶውኑ አይታሰብም ብሏል።

በሌላ በኩል እንደ አንዳንድ ምንጮች ዘገባ ኢሕአዴግ ከዋናው ኦነግ ተነጥሎ የሚቋቋም ተለጣፊ ኦነግ ለማቋቋምና በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛል በማለት ፕሬዚዳንት መለስ በቅርቡ በጅቡቲ ያደረጉት ጉብኝት ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ይሉታል።

## የሕዝብና የቤት ቆጠራ ተካሄደ

ከጥቅምት 1 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በመላው ኢትዮጵያ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ተካሂዷል። የቆጠራው ተግባር በሕብረተሰቡ ዘንድ ከንብረት ይዞታና ተከትሎም ሊመጣ ከሚችለው የፖለቲካ ውሳኔ ጋር ተያይዞ በመጀመሪያዎቹ ሂደት ትብብር ተነፍጎት ነበር። ይህንንም ለማለሳለስ የመንግሥት ሚዲያዎች ስለቆጠራው ሰፊ ዘገባ ሲያቀርቡ ሰንብተዋል። አርዓያም ለመሆን ሲባል ቆጠራው ከጠቅላይ ሚኒስትሩና ከሃይማኖት አባቶች ተጀምሯል። ፓትሪያርኩ አቡነ ጳውሎስ ለምዕመኖቻቸው በሰጡት ማሳሰቢያ እመቤታችን ቅድስት ማርያም ከእጮኛዋ ዮሴፍ ጋር ለቆጠራ ወደ ገሊላ በሄደችበት ወቅት ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱን ጠቅሰው ሕዝቡ ለቆጠራው እንዲተባበር ባደረጉት ንግግር መነሻ ከአንዳንድ ወገኖች ዘንድ በተለይም ከግል ሚዲያዎች "ካድሬው ጳጳስ" የሚል ዘለፋ ሲሰነዘርባቸው ሰንብቷል።

መንግሥት ቆጠራው በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን የገለፀ ቢሆንም በሐረርጌ በአንዳንድ አውራጃዎች ውስጥ ሕዝቡ አላስቆጥርም በማለቱ በተነሣው ሁከት የ6 ሰዎች ሕይወት ማለፉ ተዘግቧል።



የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሲካሄድ (ጋምቤላ)

የቆጠራው ውጤት የአንዳንድ ብሄረሰቦችን ቁጥር ከፍ ለማድረግና የአንዳንዶቹን ዝቅ ለማድረግ፣ እንዲሁም በስልጣን ውክልና፣ በአከላለል፣ በበጀት ምደባ፣ በቋንቋና በባሕል ላይ ተፅዕኖ ለማድረግ ሊውል ይችላል በማለት ተቃዋሚ ድርጅቶች ስጋታቸውን ይገልፃሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር አሁን ባለው ዕድገት ከቀጠለ በ21ኛው ክፍለዘመን በስምንት እጥፍ አድጎ 400 ሚሊዮን ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል።

[redacted]

# ጥ ን ቅ ር ከዚህም . . .ከዚያም

## የአራዳ ሹክሹክታ

"የእርሳቸው (የፕሬዚዳንት መለስ) የጅቡቲ ጉብኝት ድንቅ ነው። ቢያንስ ቢያንስ አሜሪካ የታጣውን ጅቡቲ ለማግኘት ተችሏል። ጉሌድ ግን ያስገርማሉ። የማያልቅባቸው ሽላሚ። የየሥርዓቱን ሰው ሁሉ ይሸልማሉ። ኢሳያስ አፈወርቂ ጅቡቲ ያሉት መርከቦች የእኛ ናቸው ሲሉ ነበር። የእኛ ሰዎች ደግሞ የእኛ ባሕር ኃይል ይሉታል። ሰው ባሕር ላይ በምርኮኝነት የቆመን መርከብ የእኛ የባሕር ኃይል ነው ይባላል? ወይስ ከጅቡቲ በባቡር ሐዲዱ ጥግ ጥግ ቦይ ሊቆፈር ነው? ከሕንድ ውቅያኖስ አዲስ አበባ ድረስ እንዲዘልቅ? ኸረ ለነገሩ እርሳቸው ጉብኝት ሲሄዱ ባለቤታቸውን አስከትለው አይሄዱም እንዴ? እርሱም እኮ አንዱ የፕሮቶኮል መለኪያ ነው። የምን እንደወንደላጤ ለብቻ ጡል! ጡል!ማለት ነው?"

"የኢትዮጵያን መምህራን ማኅበርን በሁለት ቦታ ሊከፍሉት አገልድመው የሮጡት ወደ ፍርድ ቤት ነው። የማኅበሩን ገንዘብ ለማሳገድ። አሁን ደግሞ የሠራተኛ ማኅበሩን ሰንጥቀው ሲገቡና ተለጣፊ ሲያበጁለት ሮጠው የሄዱት ወደ ፍርድ ቤት ነው። ባንክ ያለውን ገንዘብ ለማሳገድ ምነው ቀዳሚው ፍጥጫ ገንዘቡ ላይ ሆነ?"

"መቼም ወደ አፍሪካ መሻገር ለእነርሱ የውርደት ያህል ቢሆንም እያደርግባቸውና አቶ ክሊንተን ከመካከለኛው ምሥራቅ ጉብኝታቸው ወደ ኢትዮጵያ ጎራ ብለው ቢጎበኙን የሚደረግላቸው አቀባበል እንዴት ይሆን? . . . በእንቁላልና በቲማቲም ወይስ በአበባ ምንጣፍ በሆታ በእልልታ! ያኔ በቡትሮስ ጋሊ ጉብኝት ወቅት አንድ ተማሪ ሞቶ ብዙዎች ቆሰሉ። ክሊንተን ቢመጡ ደግሞ . . . "
(ጦማር)

## ቁልቁል ስወርድ

በአንድ የገጠር ወረዳ አንቱ ተብለው የሚኖሩ አንድ ብላታ ነበሩ። ከጊዜ በኋላ ሀብታቸውና ተሰሚነታቸው እሽቆለቆለና የቀድሞ ማንነታቸው ተረሣ። በደህናው ቀን ሊያደርጉት ቀርቶ ሊያስቡት የማይችለው ነገር ሁሉ መድረስ ጀመረና አንድ አፈር ገፊ ገበሬ የገበሬ ልጅ የልጃቸውን እጅ ጠይቆ ያለ ምንም ውጣ ውረድ ተሰጠው። ነገሩ የከነከናቸው አንድ የብላታ ወዳጅ አንድ ቀን ብላታን ያገኟቸዋና:-

"ብላታ ልጅህን እገሌ ለተባለ የገበሬ ልጅ ሰጠሃት የሚባል ወሬ ሰማሁ። ለመሆኑ አንተና እሱ እንዴት ብላችሁ ተገናኛችሁ?" ብለው ይጠይቋቸዋል።

ብላታም "እኔ ቁልቁል ስወርድ እሱ ሽቅብ ሲወጣ ተገናኘን" ሲሉ መለሱላቸው ይባላል።
(ጦቢያ)

## "በነጭ ለባሽ መሃል"

የአነጋገር ለዛቸው የጣፈጠና አንቱ የተባሉ አንድ መሪጌታ በአንድ ወቅት ከአንድ የደብር ክብረ በዓል ላይ ይገኛሉ። ሰው ሁሉ ፀዳዳ ነበር የለበሰው። በተለይ ካህናት በሙሉ ነጭ ጥምጥማቸውን፣ ነጭ እጀ ጠባብና የክት ኩታቸውን ለብሰው ነጭ በነጭ ሆነዋል። መሪጌታ ግን ከዚያ ሁሉ ሰው መሃል አዳፋ ልብስ ለብሰው አልባሌ መስለው ይታያሉ። አንድ ወዳጃቸው አስጠሯቸውና

"መሪጌታ ሁሉም ፀዳዳ በለበሰበት በዛሬው ቀን ምነው አዳፋ ለበስክ? ሲሉ በመገረም ይጠይቁአቸዋል። መሪጌታም "ከዚህ ሁሉ ነጭ ለባሽ መካከል እኔ አዳፋ ባለብስ እርስዎም አይለዩኝም ነበር" አሉዋቸው ይባላል። (ተናገር)

## መኀለት አብዝቷል

አጤ ምኒሊክ ድንጋይ የሚፈጭ መኪና አገር ውስጥ አስገቡ ተባለና አገር ጉድ ጉድ ሲል ይኸው ወሬ በየክፍለሃገሩም ተናኝቶ አንድ የጎጃም አገር ሰው ይሰማሉ። ይህንን አገር ያስደነቀ ወሬ እውነተኛነቱን ለማየት ጎጃሜው ስንቃቸውን ሰንቀው፣ አሽከራቸውን አስከትለው፣ በቅሎአቸውን አስጭነው አዲስ አበባ ይመጡና ማሽኑ ከተተከለበት ከእንጦጦ ጋራ ይወጣሉ። የድንጋይ መፍጫ ማሽኑ ቋጥኝ ቋጥኙን እየጎረሰ ፈጭቶ ደቃቁን ሲያወጣ እንደ ጉድ እያስተዋሉት ሳለ አንዱ አሽከራቸው ጠጋ ብሎ:-

"ጌታዬ አዩት ይህን ተዓምር? አንዳች የሚያክለውን ድንጋይ እኮ ነው ዱቄት አድርጎ የሚተፋው" ይላቸዋል። ከተመሰጡበት ሃሳብ ብንን ብለው "አዎን አየሁት ልጄ! ብቻ ይበለው። እሱም (ድንጋዩም) መኀለት አብዝቶ ነበር። ስንት ዓመት ተንቀሳቅሶ እያውቅ ምን ያድርገው ታዲያ?" አሉ ይባላል።

## አንድ ጥያቄ አለኝ

● ይሄ ነፃ ፕሬስ የሚባለው መቼ ይሆን ከአገራችን ድራሹ የሚጠፋው? ወልደትንሣኤ – ከደሴ
▶ የእርስዎ ፀሐይ በምዕራብ ወጥታ በምስራቅ መጥለቅ ስትጀምር

---

● የመእሕድን ደጋፊዎች ጠጉር ላጭቶ ማጎሪያ ውስጥ መክተት ኃጢያት አይሆንም?አበበ – ከኡራኤል
▶ ለድርጊቱ ፈፃሚዎች ጽድቅ ቢሆንስ!

---

● አሁን ዘራፍ ብዬ በጀግንነት ወኔ ብነሳ ማን አባቱ ከፊቴ ይቆማል? ጥላዬ – ከኳስ ሜዳ
▶ እስቲ ይሞክሩ።

---

# ሩዋንዳን ያደማት ማነው?

(ከሰይፉ መኩሪያ)

(አትላንታ July 25th-1994)

ባለፈው የላንዳፍታ እትም ላይ "የጎሳ ፍጅትና የመሣርያ ገበያ በሩዋንዳ" በሚል ርዕስ ሥር ሩዋንዳ ውስጥ ለተፈጠረው ችግር መነሻና አባባሽ ጉዳዮች ከተለያዩ ዘገባዎች ያገኘኋቸውን ሀቆች በማጠናቀር አቅርቤ ነበር። የሩዋንዳው ሁኔታ ተባብሶ የውጪ ሀይሎችም በሩዋንዳ ውስጥ በሰፊው ገብተው በሚገኙበት ባሁኑ ወቅት ሌሎች አዳዲስ ዘገባዎች በፊት ያልቀረቡ ትንተናዎችን ይዘው መወጣት ጀምረዋል። የሩዋንዳን ጥንታዊ ታሪክ አሁን ከመናየው ቀውስ ጋር በማገናዘብ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት እነዚህ ዘገባዎች ሩዋንዳ ውስጥ ለተካሄደው/ለሚካሄደው የጎሣ ፍጅት ዋና ተጠያቂዊቹ ወይም የችግሩ ጠንሳሾች የውጪ ሀይሎች ናቸው የሚሉ ናቸው። እነዚህን ዘገባዎች በሚጠናከር ስለ ሩዋንዳ እንዲሁም በአጠቃላይ ስለ ጎሣ ፖለቲክ ሠፋ ያለ ግንዛቤ ይገኝ ይሆናል በማለት እነሆ በተከታታይ የሩዋንዳን ሁኔታ አቀርባለሁ።

ባለፈው ፅሁፍ ላይ ለሩዋንዳ የጎሣ ፍጅት ዋና ተጠያቂዎቹ የሩዋንዳው መንግሥትና ያፔትሪየቲክ ፍሮንት መሪዎች ናቸው የሚል አስተያየት ቢሠፍርም ፍጅቱን በማማባስ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉ የውጪ ሀይልች እንዳሉም ተጠቅሶ ነበር። ከዚህ አስተያየት መንጠቅ የሚሉት ያሁኖቹ ዘገባዎች ይአፍሪቃ መሪዎችን ታሪካዊ አመጣጥ በመመርኮዝ ያሁኑ የጎሣ ፍጅት ጠንሳሾች ምዕራባዊያን ናቸው። (Western govts.) የሚል መደምደሚያ ላይ አርፈዋል።

ኖቮ(Novo) የሚባለው የጀርመን መፅሄት በቅርቡ ባወጣው ዘገባ ላይ ሩዋንዳ በጎሣ ፍጅት ልትታወቅ የበቃችው ይምዕራባውያን ሚዲያ ያቀረቡልንን ሀተታ ያለአንዳች ምርምር ስለተቀበልነው ነው ብሏል። በማያያዝም በየቀኑ በቴሌቭዥንና በየጋዜጣው የምናያቸው የሬሳ ክምሮች የሩዋንዳ ችግር ጥንታዊ የጎሣ ጥላቻ ያመጣው ጣጣ ነው የሚል ግንዛቤ ሰጥተውናል ይልና ሆኖም ይህ ግንዛቤ ስህተተኛ ነው በማለት ይደመድማል። ይህንኑ የጀርመን መፅሄት አስተያየት በመደገፍ ሌላ አንድ እንግሊዝ አገር የሚታተም የግራ መፅሄት "THE INVENTION OF TRIBILISM" ብሎ ባወጣው የ July እትሙ ላይ "አፍሪቃ ውስጥ ጎሠኝነት የፖለቲካል ሀይል ሊሆን የበቃው ከቅርብ ግዜ ወዲህ መሆኑንና ይህም ሊሆን የቻለው የአፍሪቃውያኖችን አንገዛም ባይነት ለማዳከም ሲባል በቅኝ ግዥ ዘመን የፈለቀ የከፋፍለህ ግዛ ዘዴ እንደሆነና አፍላቂዊቹም ቅኝ ገዥዎች መሆናቸውን ያበስራል።

<u>ጎሣና ፖለቲካ</u>

አፍሪቃ ውስጥ "ያገር ሽማግሌ" ወይም የ "ሠፈር አለቃ" ይባሉ የነበሩት የጥንት መሪዎች አመጣጣቻውንና የአስተዳደር ኃላፊነታቸው ምን እንደነበረ ብንመለከት አሁን ከምናየው ሁኔታ ለየት ያሉ ነገሮችን እናገኛለን።

አፍሪቃውያኖች በነፃነት ይኖሩ በነበረበት ዘመን ያገር ሽማግሎች (ELDERS) ወይም የሠፈር አለቆች (ELDERS COUNCIL) የሚመረጡት ከህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ነበር። ሰው አክባሪዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ከራሳቸው በላይ የወገናቻቸውን ደህንነት ተመልካቾች፣ ስምምነትና ዕርቅ የማውረድ ችሎታ ያላቸውና እነዚህን በመሣሠሉ በጎ ተግባሮች የሚታወቁ ሰዎች በአገር ሽማግሌትና በሠፈር አለቀነት ይሾሙ ነበር። እነዚህ መሪዎች ተወጣጥተው የሚመጡትም ሀብት ከሌላቸው፣ በቂምጥናና በሌላ በሽታ ከታመሙት፣ በሥራ ጉብዝናቸው ከሚታወቁትና ከመሳሰሉት ክፍሎችም ሲሆን የምርጫው ይዘትም የአለቀነት ሹመታቸውና በመጠቀም አምባገነን ወይም ጨቋኝ ለመሆን መንገዱም ሆነ ችሎታውም ሊኖራቸው የማይቻላቸውን ሰዎች ጭምር ነበረ።

እነዚህ መሪዎች በህዝባቸው መሀል የሚፈጠር ችግርን በመወያየትና በመካከር አስፈላጊም ሲሆን አፈርሳታን ወይም ጉባዔን ጠርተው ስምምነትን በመፍጠር ችግርን የመፈታት አሠራር ባሃል ነበራቸው። ያገር ሽማግሌዎች ስምምነትንና ዕርቅን፣ መረዳዳትንና መተጋገዝን ከማምጣት በላይ አሁን የምናውቀውን ዓይነት ሥራ ማለትም የ'ለቲካ ሀይል (POLITICAL FORCE) ለመሆን የማይችሉ ነበሩ።

የመጀመሪያው ዓለም ጦርነት እንዳበቃ በህንድ አገር ውስጥ የተጀመረው የነፃነት እንቅስቃሴ ቅኝ ገዥ የነበረችውን እንግሊዝን አስደንግጧት ነበር። ፀሀይ አትጠልቅበትም ይባልለት የነበረውን የእንግሊዝ ግዛትን ያስተዳድሩ የነበሩት

ፔትሪየቲክ ግንባሩ የፈረንሳይን ሚና እንደሚቃወም መግለፅ ቢታወቅም ግንባሩ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ አዲሱን መንግሥት እንደምትቀበል ማስታወቅም "ሩዋንዳን በሚመለከት አንድ የፖሊሲ ለውጥ ሳይደረግ አልቀረም" የሚል ግምት አስገኝቷል። ባሁኑ ሰዓት የተ.መ.ድ.ን ውሳኔ ተገን በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆኖ የሚወናወነው የአሜሪካ መንግሥት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የቀረበችው ቤልጀም ነች።

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው የሩዋንዳው ፍጅት ከመጀመሩ በፊት የአነሻ ስምምነትን በሥራ ለማዋል ተብሎ የተመድ ሠላም ጠባቂ ሀይሎች በሩዋንዳ እንዲሠፍሩ ተደርጎ ነበር። ፍጅቱ ሲካሄድ የተ.መ.ድ ሀይሎች ቆመው መመልከታቸውንና ኋላም ፈረንሳይ በግሏ ወታደሮቿን ልካ ደቡብ ሩዋንዳ ውስጥ ካምፕ መሥራት ነበር። ባሁኑ ሰዓት ፈረንሳይ ጓዟን ጠቅልላ እንደምትወጣ ሲታወቅ በሌላ በኩል የተመድ ወታደሮች በገፍ ወደ ሩዋንዳ እየእየጎረፉ ነው።

የአሁኑ ሁኔታ በፔትሪየቲክ ግንባሩና በሩዋንዳው መንግሥት መሀከል የነበረው ግጭት ቦግ እልም ሲል እንደነበረና በሁለቱ ወገኖች መሀከል አንድ ዓይነት ስምምነት ለማምጣት ጥረት እንደነበረ ተጠቅሶ ነበር።

ሟቹ ፕሬዚዳንት ሀብያሪማና ጠንከር ያለ እምቢተኝነት ያሳዩ ስለነበር በውጪ ሀይሎች ግፊት የአሩሻ ስምምነትን እንዲቀበሉ ተደርገው ነበር። በዛን ግዜ ሀብያሪማና ላይ የበለጠ ተፅዕኖ ለማምጣት ተብሎ የፔትሪየቲክ ግንባር ወታደሮች ዋና ከተማ "ኪጋሊ" ውስጥ እንዲሰፍሩም ተደርጎ ነበር። ይህን ያደረገው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲሆን ዓላማውም ይቋቋማል ተብሎ በነበረው የጥምር መንግሥት ውስጥ የግንባሩን ተሳታፊነት ለማምጣት ነበር። ፊት ያልተገለጠ አሁን ግን ገሀድ የወጣ ነገር ቢኖር፣ በዛን ግዜ በሩዋንዳ ውስጥ የነበረው የ.ተ.መ.ድ ሀይል በውስጡ የቤልጅየም ወታደሮችን የያዘ እንደነበረና እነዚህ ወታደሮችም ከፔትሪየቲክ ግንባሩ ጋር ቅርብ እኑኝነት እንደነበራቸው ነው። ግንባሩ ኪጋሊ ውስጥ ሲቆይ የሠፈረበትን ቦታ በኪራይ መልክ ያቀረቡለት እነዚሁ የቤልጅየም ወታደሮች ሲሆኑ፣ የኪጋሊን አየር ማረፊያና የፕሬዚዳንቱን መኖሪያ አካባቢ ይቆጣጠሩ የነበሩትም እነዚሁ ወታደሮች ነበሩ። የሀብሪያማና መሞት እንደተሠማ ቶሎ ስልጣኑን ለመጨበጥ ፔትሪየቲክ ግንባሩ ወዲያውኑ አየር ማረፊያውንና ቤተ መንግሥቱን መደብደብ ይጀምራል። ይሄ ሁሉ ሲሆን የ ተ.መ.ድ ወታደሮች ቆመው መመልከታቸውንና ሩዋንዳ ውስጥ የተካሄደው የጎሣ ፍጅትም ከዛ በኋላ መሆኑን ዘገባዎቹ ይናገራሉ። ቤተ መንግሥቱን ይጠብቁ የነበሩት የመንግሥት ወታደሮች ከፔትሪየቲክ ግንባሩ ጋር የሞትና የሽረት ውጊያ ያማሄዱትም ያኔ መሆኑን ይጠቁማሉ።

የጀርመኑ መፅሄት ኖቮ(NOVO) በማያያዝ እንዳስቀመጠው ሩዋንዳ ውስጥ የሚገኙቱ ሁለቱ ጎሳዎች (ሁቱና ቱትሲ) ጥንታዊ ቅራኔ እንደሌላቸው ከመግለጡም በላይ ሁቱ ወይም ቱትሲ ጎሳዎች እንዳልሆኑም ይናገራል። እንደውም እንኳን ጎሣ መሆን ይቅርና ቋሚ የሆኑ ልዩነቶችም እንዳልነበሯቸው በመግለጥ ባሁኑ ጊዜ የምናየው የሩዋንዳ ችግር ቅኝ ገዥዎች በሩዋንዳ ህዝብ ላይ የጫኑት የከፋፍለህ ግዛ ችግሮች ናቸው ይላል። ይህም የከፋፍለህ ግዛ ዕቅድ ዘንድሮ አኖዲህ ህዝብ ሊያፋጅ የበቃውም በሩዋንዳ ላይ የሥልጣን ለውጥ ለማምጣት ሲሉ የውጪ ሀይሎች የጎነተሉት ጉዳይ ነው ይላል። የሶቬየት ኅብረት ድምጥማጡ ከጠፋ በኋላ የምዕራብ አገሮች አፍሪቃ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ለማጠናከር ከተለያዩ የአፍሪቃ መሪዎች ጋር ድርድር ውስጥ መግባታቸውንና በዚህ ድርድር አማካይነትም የተለያዩ መንግስቶች መገልበጣቸውን። አንዳንድ መሪዎችም በስስምምነት ስልጣን መልቀቃቸውን፣ አሻፈረኝ ያሉ መሪዎችም መሰደዳቸውን ማልሆነም መገደላቸውን በመጥቀስ በተለየ ባሁኑ ወቅት "ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ" እና "መልቃይ ፓርቲ" በሚሉ አርማዎች ስር የአፍሪቃ ህዝብ ለበለጠ ብዝበዛና ስቃይ መደረጉንና ይህንን ሥራ በግንባር ቀደምትነት የሚመራው የአሜሪካ መንግሥት መሆኑን ዘገባዎቹ የደመድማሉ።

በአሁኑ ጊዜ የምናየው የሩዋንዳ ህዝብ በገፍ መሰደድና በየቦታው መሞት ያልተጠበቀና ያልተገመተ ሀዘን ይመስላል። ከቅርብ ግዜ ጀምሮ የአሜሪካ ሚዲያ የሩዋንዳን መንግሥት መውቀስ እንደጀመረና አገራቸውን ጥለው ወደ ስደት የገቡት ህዝቦች "የሩዋንዳው መንግሥት በሬዲዮ ስለሚሰብካቸው ነው" በማለት ይህንን ለመቋቋም የአሜሪካ መንግሥት አንድ የሥርጭት ሀይሉ ሠፋ ያለ የሬዲዮ ፕሮግራም እንደሚጀምር ገልጧል። የፔትሪየቲክ ግንባሩ አሁን የሩዋንዳን ሥልጣን መያዙ ቢታወቅም ቅሉ ግንባሩ ወረራውን ከዩጋንዳ በመጀመር ስልጣኑን ለመያዝ እንደበቃ ሁሉ አሁን በስደት ላይ ያሉት ሁቱዎችም ግዜያቸውን ጠብቀው እንደገና ወደ ኪጋሊ ለመዝመት ማቀዳቸውን በገሀድ ተናግረዋል።

ዘገባዎቹ በመቀጠልም፣ በአፍሪቃ ውስጥ በመተረማመስ ላይ የሚገኘውን

ባለሚሎች ህንድ ውስጥ የተነሳውን ዓይነት የነፃነት እንቅስቃሴ በሌላው የእንግሊዝ ግዛቶች ውስጥ እንዳይነሳ አስቀድመው በመሥጋት አፍሪቃውያኖችን በየጎሳው በመለያየት የከፋፍለህ ግዛ አስተዳደር ዘረጉ። ታንጋኒካን ያስተዳድሩ የነበሩት SIR DONALD CAMERON የጥቁር ህዝብን በጎሣ መከፋፈል አስፈላጊ መሆኑን ሲናገሩ "ገዥነታችንን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመቀበል በአገሬው አለቆች አማካይነት ማለትም በአገሩ ሽማግሌዎችና በአማካሪዎቻቸው አማካይነት ግዛታችንን መጠበቅ የምንችለውና በኋላም ቁስ በቀስ የተማሩ ያገሬው ተወላጆች ስልጣኑን ሲይዙ በኛ መንገድ ማስተዳደር እንዲቀጥሉ የምንፈልግ ከሆነ አንድ ነገር መዘየድ ያስፈልገናል ብለው ነበር።

ቅኝ ገዥዎች ይህንን ፍልስፍና በመከተል ምንም ያህል "ፖለቲካ ሀይል" ያልነበራቸውን ያገር ሽማግሌዎች ቀስ በቀስ ወደ የመንግሥት ባለሥልጣንነት መቀየሩን ተያያዙት።

በዩጋንዳ ውስጥ ለምሳሌ፣ ያገር ሽማግሌዎችን ቅኝ ገዥዎች ይጠሩዋቸውና የጎሳ ወይም የብሄር "አለቆች" ብለው ይሰይሟቸዋል። ከዛ በኋላ ቀስ በቀስ እነዚህ አለቆች በጡረታ መልክ (በክብር) ከስራቸው ይገለሉና የሚሊዮን ትምህርት በቀሰሙ ዜጎች ይተካሉ። እነዚህ የድሮ ሽማግሌዎችን የተኩ አዲስ አለቆች በተራቸው ቀስ በቀስ ባህላዊ ከነበረው የሽምግልና ሥራ ለየት ያለ ሌላ ሥራ በሹመት መልክ ይሠጣቸዋል። በመጨረሻም በዚህ በአዲሱ ሥራ አማካይነት ፊት ሽማግሌዎች ከነበራቸው ህዝባዊ መሠረት እየራቁ በመሄድ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ የነበረው ያገር ሽምግልና ሥርዓት እየሟሸሸ ይሄድና ቅኝ ገዥዎች ሹመት የሚሰጡበት የአለቅነት ሥርዓት ይሠፍናል። ይህንን ታሪክ ያቀረበው ሀተታ ይባል ብሎ ዝርዝር ውስጥ በመግባት በቅኝ ገዥዎች ፍላጎት ተመርጠው በአለቅነት የሚሾሙት አፍሪቃውያኖች በታርዛን ሲኒማዎች ላይ የሚታዩትን ቺፍ (CHIEF) የመሠሉ መሆናቸውን ማነፃፀር ይቻላል ብኋል።

በሌላ ምሳሌ፣ LOFD FREDRICK LUGARD ይህንን የከፋፍለህ ግዛ ስልት በምዕራብ አፍርቃ ውስጥ እንደተጠቀሙበት ይነገራል። የናይጀሪያ አስተዳዳሪ በነበሩበት ወቅት (1902) በሰሜን ናይጀሪያ የከብት አርቢ ለነበሩት የፉላኒ ጎሣ ኢሚሮች ለይተው ስልጣን በመስጠት በተዘዋዋሪ እጅ ግዛታቸውን ከማስጠበቃቸው በላይ በዛን ዘመን ያስፋፉት ይህ የከፋፍለህ ግዛ አስተዳደር እሁን ድረስ የናይከሪያ ህዝቦችን የእርስ በርስ አለመተማመን እንዳሠመረው እናያለን።

ባሁኑ ወቅት አንዳንድ የአፍሪቃ መሪዎች ሥልጣናቸውን ላለመልቀቅ ወይም ሥልጣን ላይ ለመውጣት ሲሉ የሚጠቀሙት የጎሠኝነት ፖለቲካና የከፋፍለህ ግዛ ሥርዓት ምንጩ ቅኝ ገዥዎች የቆፈሩት ጉድጓድ መሆኑን እነዚሁ ዘገባዎች ይናገራሉ።

ወደ ሩዋንዳ መለስ ስንል የምናየው ጎሣ ፍጅት አመጣጡና ታሪኩ ከላይ እንደተጠቀሰው የቅኝ ገዥዎች ሆን ብለው የጀመሩት የከፋፍለህ ግዛ ውጤት መሆኑን ለመረዳት እንችላለን።

ሩዋንዳ በጀርመን ቅኝ አገዛዝ ሥር ነበረች። የመጀመሪያው ዓለም ጦርነት ላይ ጀርመን በመሸነፏ ምክንያት LEAGUE OF NATION ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ሩዋንዳ በቤልጅም አስተዳደር ሥር እንድትቆይ ሆኖ ነበር።

የጀርመንም ሆነ የቤልጅም አስተዳደሮች ያለማቋረጥ ያሰመሩት ነገር ቢኖር የሩዋንዳን ህዝብ በጎሣ መከፋፈልና አንዱን ጎሣ በሌላው ጎሣ ላይ እንደ አዛዥ/ አለቃ ማስቀመጥ ነበር። የቤልጅም አስተዳዳሪዎች ከአርባ አመቶች በላይ ሩዋንዳን ሲገዙ በልዩ ልዩ የአለቅነት ቦታ ላይ ያስቀመጡት በመልካቸው ቀላ ቀላ የሚሉትንና የፊት ገፅታቸው ስልክክ ለሚለው ለቱትሲ ተወላጆች ነበር። ታሪካቸውን በሚመለከት አረጋግጦ የሚጠቁም ዘገባ ገና ባይገኝም የቱትሲዎች ዘርያና ፍላሣ ከደቡብ ኢትዮጵያ መሆኑንና ግንዳቸው የኦሮሞ ዘር ነው የሚሉ ሁለት ፅሁፎች ይናገራሉ። በሌላው ወገን ቆዳቸው ጠቆር ገፅታቸው ደፍጠን የሚሉት ሁቱዎች ቅኝ ገዥዎች ያመጡት ይህ የአድልዎ ሥራ ያበሳጫቸው ነበር። ከዚህ በፊት ባቀረብኩት ፅሁፍ ላይ በሁለቱ መሀል ያለው ቅራኔ ከዘር ይልቅ የሶሻል ቅራኔ ነው ነበር። ይህንኑ በሚመለከት የቀረበ ሌሌላ ዘገባ ሁቱና ቱትሲ አሁን እንሀሚወራው የጎሣ መለዮ ከመሆናቸው ይልቅ የሀብትና የሥልጣን መለዮ ወይም መጠሪያ እንደነበሩ በመግለፅ እንዳውም ቱትሲ ማለት ባለፀጋ፣ ሁቱ ማለት ደሀ መሆኑንም ከታሪክ ጋር ያገናዝበዋል።

ወደ አሁኑ ሁኔታ ስንመለስ የፈረንሳይ ሚና ይጠበቅ ከነበረው ግምት ቀዝቅዞ ሌሎች የውጪ ሀይሎች "በተለይ አሜሪካ" ሠፋ ያለ ጣልቃ ገብነት እንደጀመረች ይታያል። ምንም እንኳ

የዲሞክራሲና የመልታይ ፓርቲ እንቅስቃሴዎች አመጣጥ በጥርጣሬ አስቀምጠውታል። አንዱ ጥያቄ "የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ አፍሪቃ ውስጥ እንዴት ነው የሚካሄደው?" የሚል ሲሆን ምላሹን በሚከተለው መንገድ በማስቀመጥ ጥርጣሬውን አስፋፍተውታል።

" የአፍሪቃ መሪዎች አንድ ዓይነት መልታይ ፓርቲ ስርዓትና ነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ካልመሠረቱ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ዕርዳታ እንደማያገኙ በምዕራባውያን መንግሥት (WESTERN GOVTS) ይነግራቸዋል። በአገራቸው ያለውን ችግር ለመቋቋም ሠፋ ያለ ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያምኑት የአፍሪቃ መሪዎች የሚያገኙት ዕርዳታ እንዳይቀርባቸው ሲሉ የተጠየቁትን ለማድረግ ፈራ ተባ እያሉ ይሰናዳሉ። ከዛ በኋላ አሸናፊውንና ተሸናፊውን ለይተው የሚመሰክሩ የምርጫ ታዛቢዎች ይጎርፋሉ፣ በምርጫው ሳቢያ ያልፈለጉት ወገን አሸናፊ ሆኖ ቢገኝ (አነጎላ) ሊስማማቸው የሚችል ነገር እስከሚያበጁ ድረስ አዲሱን አሸናፊ ሀይል ላለማወቅ(RECOGNIZE) በየምክንያቱ ወደ ኋላ ይጎተታሉ። በሌላ በኩል የኤኮኖሚ አማካሪዎች በየሚኒስትሪው እየገቡ የህዝብ (የመንግሥት) ንብረት የነበሩ ተቋሞችን ለምዕራባዊ ነጋዴዎች በርካሽ የሚሸጡበትን ሁኔታ ይዘረጋሉ። ይህ የዲሞክራሲ ወይም የመልታይ ፓርቲ ሂደት ከውጪ የመጣ ጭነት ከመሆኑም በላይ የአፍሪቃን የኤኮኖሚና የፖለቲካል ህይወት በምዕራባዊ ባንኮችና ባለንብረቶች እጅ እንዲጠቃለል የሚያደርግ ነው።"

የአሩሻ ስምምነት በሚባል ይጠራ የነበረው የሩዋንዳ ስምምነት ሚቹ ሀብሪያማና ላይ ይህን በመሠለ ተፅዕኖ መምጣቱን የሚናገረው ይኸው ዘገባ ያያይዝና "የአሩሻው ስምምነት ሊፈረምየበቃው IMF ዓለም ባንክ ተ.መ.ድ አሜሪካና ቤልጅየም የሀብሪያማና መንግሥት ላይ ከባድ ተፅዕኖ ስላመጡበት ነው" ይላል። የፈረንሳይ ከሥልጣን የተባበረውን መንግሥት እስካሁን ድረስ መደገፍ ቢታወቅም የሌሎቹን ጣልቃ ገብነት መድረሱን የሚጠቁም ነው።

## አዲሱ የሩዋንዳ መንግሥት

ባሁኑ ግዜ ፔትሪየቲክ ግንሩ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ስልጣን ላይ የተቀመጡት ሦስት ሰዎች ናቸው። ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስተር ተብለው የተሰየሙት የሁቱ ተወላጆች ሲሆኑ ቁልፍ የሆነውን የመከላከያ ሚኒስተር ቦታ የያዙት የፔትሪየቲኩ ግንባር መሪ ፖልካጋሜ ናቸው። ከጥቂት ቀን በፊት የነዚህን ሰዎች አጭር ታሪክ ኒውዮርክ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ አውጥቶት ነበር። ታሪካቸው የሩዋንዳን ችግር ለመገንዘብ ይረዳል በማለት ከዚህ በታች አሠፍረዋለሁ።

## ፖልካጋሜ (መከላከያ ሚኒስተር)

የ37 ዓመት ዕድሜ ያላቸው የቱትሲ ተወላጆች ናቸው። በ3 ዓመታቸው ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ዩጋንዳ የተሰደዱና በዩጋንዳ ሠራዊት ውስጥ ያገለገሉ ሲሆን፣ የዩጋንዳ ሠራዊትን የቀላቀሉት በ1982 ዓ.ም. ሆኖ ከአራት ዓመት በኋላ (1986 ዓ.ም.) ሙሴ ቬኒ በዩጋንዳ ስልጣኑን ሲይዙ የዩጋንዳ መረጃ ክፍል (INTELLIGENCE) ሃላፊ በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተው በ1990 ዓ.ም. ለውትድርና ትምህርት ወደ አሜሪካ በመንግዝ ካንሳስ ውስጥ የነበሩ ሰው ናቸው። ፓልካጋሜ የፔትሪየቲክ ግንባር ዋነኛውና ተደማጭ መሪ ሲሆኑ የሁለት ልጆች አባት ለመሆን የበ ባለትዳር ናቸው።

## ፋውስቲን ትዋጊሩሙንጉ (ጠቅላይ ሚኒስተር)

የ49 ዓመት ዕድሜ ያላቸው የሁቱ ተወላጅ ናቸው። የፈረንሳይና የእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ካናዳ ውስጥ ንግድ (BUSINESS) ትምህርት የቀሰሙ ሲሆን ሀብሪያማና የተገደሉ ቀን ኪጋሊ ውስጥ ስለነበሩና የመንግሥት ተቃዋሚ ናቸው ስለሚባል አደጋ እንዳይደርስባቸው ተብሎ ለጥቂት ሳምንታት የ ተ.መ.ድ ጥበቃ የተደረገላቸውና ወዲያውኑ ወደ ፔትሪየቲክ ግንባሩ ሠፈር እንዲቀላቀሉ የተደረጉ ናቸው።

## ፖሥቲየ ቢዚሙንጉ (ፕሬዚዳንት)

ወደ አርባ ዓመት የሚጠጋቸው የሁቱ ተወላጅ ሲሆኑ በቤልጅየም ከተማ በብሩሴልስ ውስጥ የፔትሪየቲክ ግንባሩ ዋና ተወካይ ነበሩ። በሥራቸው ፖልካጋሜን በቅርብ የሚጠጉ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቋንቋን በሚገባ የሚናገሩ ናቸው።

ከዚህ ሌላ ሁለቱ ሰዎች ማለትም ጠቅላይ ሚኒስትሩና ፕሬዜዳንቱ በሀብሪያማና መንግሥት ሥልጣን ይዘው ውስጥ ውስጡን ለፔትሪየቲክ ግንባር ይሰሩ ነበር። ሀብሪያማና እንደተገደሉ የሁቱ ተወላጆች እነዚህን ሰዎች ስንደ ከዳተኛ ቆጥረዋቸው ለመግደል ይፈልጉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

--------------------------

ልብወለድ

## የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብወለድ)
ከገረሱ

**ክፍል አስር**
ካለፈው የቀጠለ

**የመጨረሻው መጀመሪያ**

ባለፉት ዘጠኝ ተከታታይ እትሞች "የዴብራ ጦስ" በተሰኘ ርዕስ ባቀረብነው ታሪክ ካሣሁንና ፈጠነ የተባሉ ሁለት ጓደኛሞች በአሜሪካ ኑሮአቸው ወቅት የትዳር ጓደኛ ወይም የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ ለማግኘት በአደረጉት ጥረት ውስጥ ገጠመኞቻቸውን አሳይተናል።

ካሣሁን ኢትዮጵያዊ ጓደኛ ለማግኘት ብዙ ሞክሮ ተስፋ በመቁረጥ በአንድ ቡና ቤት ካገኛት ዴብራ ከምትባል አሜሪካዊት ጋር የፍቅር ጓደኝነት ጀምሮ፤ የአበሻ ሴትም እርም ብሎ በመጨረሻም ራሄል ከምትባል ልጅ ጋር መተዋወቁን አሳይተናል። ጓደኛው ፈጠነ በአሜሪካን ሴቶች ላይ የነበረው መጥፎ ግምት ሲንትያን ከተዋወቀ በኋላ ቀስ በቀስ እየተቀየረ መምጣቱን አይተናል። በእነኚህ ሁለት ጓዲኛሞች የአሜሪካ ኑሮ ገጠመኝ ታሪክ ውስጥ እስካሁን ድረስ ብዙ ነገሮችን ለማጤን የሞከርን ይመስለናል። እንግዲህ ወደታሪኩ መጨረሻ አካባቢ የደረስን ስለሆነ ይህንኑ በጽሞና ለመከታተል እንሞክር።

ካሣሁን ከራሄል ጋር በስልክ ሰፋ ያለ ጨዋታ ካደረገ በኋላ ራ ሄልንፈጽሞ ትሆናለች ብሎ ያልጠበቃት ልጅ ሆነችበት። ምን ራሄልን ብቻ፤ በድፍን ያበሻ ሴት ላይ አሳድሮ የነበረውን ግምት የበለጠ እንዲመረምር አደረገው። ራሄልን እሱ እንደፈለገውና እንዳቀደው አንዴ አውጥቶ የሚተዋት ልጅ ዓይነት አልሆነችለትም። የዚያን ዕለት ከሷ ጋር ስልኩን እንደጨረሰ ዴብራ ትደውልለታለች። እንደሌላው ጊዜ አልተንገበገበላትም። ሃሳቡ በሙሉ ያለው ከራሄል ጋ ነበርና ዴብራ ስታናግረው በግማሽ ልቡ ነበር የሚሰማት። ዴብራ "መጣሁ ቤት ቆየኝ" ስትለው አትምጪ ሊላትም ፈልጎ ነበር። ግን ፈራት። ቀዝቀዝ ባለ መንፈስ እንዳናገራት ዴብራ ሳትረዳው አልቀረችም።

ባለችው ሰዓት መጣች። ሁኔታው ቀዝቀዝ ሲልባት የምታደርገውን ታውቃለች። እቤት እንደገባች ልቡን መብላት ያዘች። "Honey I missed you." ብላ ተጠመጠመችበት። አንዴ ጉንጩን፣ አንዴ ዓይኑን አንዴ ከንፈሩን ትስመው ጀመር። እንደሌላው ጊዜ አል ተንገበገበላትም።

ቀዝቀዝ ማለቱን ስትረዳ " What is wrong honey?" አለችውና ትክ ብላ አየችው።

"Nothing" አላትና ለቀቅ አድርጎዋት ወደመቀመጫው ተመለሰ።

ሄደችና አጠገቡ ቁጭ አለችና ታባብለው ጀመር። "ምን ሆነሃል? የሆንከው ነገር አለ ንገረኝ፤ ሰሞኑን ስለጠፋሁ ነው?" አለችው።

"አይደለም፤" አላት። ምን ብሎ እንደሚነግራት ግራ ገባው።

"Then what is wrong? say it out!" አለችና ደነፋችበት። ዓመሏ ነው።

"ከእንግዲህ ከሷ ጋር ቢበቃኝ ሳይሻለኝ አይቀርም።" አለ በሆዱ። ብዙ ነገር ታስቦታል። "I think it is over" አላት እየፈራ እየተባ።

"What is over?" አለችና ጠየቀችው።

"You and me?" አላት በፍርሃት። በጥፊ የምታጮለውም መሰለው።

በመገረም ተመለከተችውና ዝም ብላ ታየው ጀመር። በማፈር የሰበረውን ዓይኑን ወደሷ የሚመልስበትን ጊዜ ጠብቃ፤ "What is up? someone else?" አለችና ጠየቀችው።

"What do you mean 'someone else'?" አላት።

"You know what I mean? Are you in love with someone else? That is what I mean." ትለዋለች።

"It is not what you think." ይላታል።

"ከእንዲህ በእኔ ላይ ፍቅር የለህም ማለት ነው?" አለችው።
ለካሣሁን ከባድ ጥያቄ ነበር። ሃሳብ ውስጥ ገባ። "እንዴት ፍቅር የለኝም ልበላት? አይባልም? ትህትና የሌለው አነጋገር ነው። እሷ ለራሷ ሰይጣን ናት፤" እያለ በሆዱ

ማሰላሰል ጀመር። ፍቅሬ አልቀነሰም እንዳይላት ደግሞ ላይገላገላት ነው። ላቀረበችለት ጥያቄ መልስ በመስጠት ፈንታ ዝምታን መረጠ።

"ጥያቄዬን አልመለስክልኝም?" አለችና አፈጠጠችበት።

"ዴብራ ብዙ ብናወራው ዋጋ የለውም። እንደመሰለኝ እዚሁ ላይ ብናቆም ጥሩ መሰለኝ ነው የምልሽ፤ ሌላ ማለት አልፈልግም።" አላት። ይህን በሚልበት ወቅት ዓይኗን ማየት ፈርቶ መሬት መሬት እያየ ነበር።

"እሺ ሌላ ጥያቄ ልጠይቅህ። ይህን ልትል ያስቻለህ ምን ሁኔታ ተፈጠረ? በኔ በኩል? ወይ እኔ ያስቀየምኩህ ነገር አለ ወይ? ከልብህ መልስልኝ።" አለችው።

የድሮዋ ዴብራ አልሆነችም። ድሮ የምትፈልገውን ነገር ስይጠይቅ ወይ በቃለ አጋኖ ወይ በትዕዛዝ መልክ ነበር የምታወራው፤ ዛሬ ግን ተለማማጭ ሆነች። ለስለስ ያለው የመለማመጥ ጥያቄዋን እንዴት እንደሚመልስ ግራ ተጋባ። ያለመደው ነገር ሆነበት።

"አንቺ ያስቀየምሺኝ ነገር የለም። በቃ እንደዚህ ሆነን ለማያዛልቅ ነገር አብረን መቆየቱ አልታየኝም። ያንቺንም የኔንም ጊዜ ማጥፋት ነው መስሎ የታየኝ።" አላት እየፈራ እየተባ።

"ጊዜ ማጥፋት ማለት ምን ማለት ነው?" ብላ ጠየቀችው።

አባባሏ ለካ እኔ ጊዜ ማጥፊያህ ነበርኩ የሚል አስተያየት የሚያስከትል መሰለው። ምን እንደሚላትም ግራ ገብቶት ዝም ብሎ ጣራ ጣራውን ያይ ገባ።

ዝም ማለቱን አይታ "እስካሁን ያደረግነውን ሁሉ፣ ያሳለፍነውን ጥሩ ጊዜ ሁሉ ዝም ብሎ ጊዜ የባከነ ዓይነት አድርገህ ወስደኸው ነው እንዴ?" አለችው።

ለምትጠይቀው ጥያቄ መልስ አለመስጥቱ ወይም መዘግየቱ ያሳሰባት መሰለ። ሰይጣኗ ከመጣ ደግሞ የሚችለው አይሆንም።

ያበጠው ይፈንዳ፤ እስከመቼ ተፈርቶ። "በኔ በኩል ያለውን ነግሬሻለሁ እንግዲህ፤" አላት ከመቀመጫው እየተነሳ፤ ወደ ጓዳ ይሁን ወዴት፣ ሊሸሽም ይሁን ብቻ እያውቀውም ምክንያቱን፣ ሲነሳ።

"ጥያቄዬን አልመለስክም። ምን እንዳስፈራህ አላውቅም። ጠልተኸኝ ከሆነ ጠልቼሻለሁ ማለት ካልሆነም ሌላ ምክንያት ሊኖር ይችላልና እሱን ንገረኝ።" አለችው መነሳቱ ገርሟት ከእግር እስከ ራሱ እየገላመጠችው።

"It is over Debra. I got to go now if you don't mind." አላት።

ዴብራ በገነች። ዓይኗ ተገለባበጠ። ብድግ አለች። ሽንጧን ያዘች። "ማንም እኔን ረግጦ አይሄድም። አንተ አብቅቶህ እንደሆነ እኔ አልበቃኝም። የትም ደግሞ አትሄድም። ሲበቃኝ እኔው ራሴ ነግርሃለሁ። It is not that easy Buddy. የሰው ህይወት ውስጥ ገብቶ እንዳው በቀላሉ የሚወጣ አይምሰልህ።" አለችው።

ሰይጣኗ መምጣቱ መሆኑ ገባው። ተመልሶ ቁጭ አለ። ቀና ብሎ አያት። ቁልቁል ሽንጧን ይዛ እያየችው እንደሆነ ሲረዳ ፈራት፤ የምታጎነውም መሰለው። ብዙ መልስ መሰጣጣት የባሰ ችግር ውስጥ የሚከተው መሰለው። እና ዝምታን መሣሪያው አደረገ።

እሷም ትንሽ ከተቆነጣጠረች በኋላ ቁጭ አለች። አጠገቡ። ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ። በሁለቱ አዕምሮዎች ውስጥ ግን ብዙ ተብሏል። ካሣሁን ዴብራን ለመሸኘት ቆጣ ብሎ መናገር እንደማያዋጣ ገብቶታል።

"ዴብራ፣ እንደምታውቂው ሁለታችን ከተለያየ ባህል ነው የመጣነው፤ ዘላቂ የሆነ ግኑኝነት መፍጠር እንደሚያስቸግረን አንቺም የምታውቂው መሰለኝ።" አላት ድምጹን ለስለስ አድርጎ።

"Is that so? ታዲያ ይህን ስታውቅ መጀመሪያውኑ ምን አስጀመረህ? ይህ የተለያየን ነን የምትለው በቂ ምክንያት አይደለም፤ በኔ ላይ ያለህ ፍቅር ካለቀ ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ግን ሌላ ሴት ወደህ ከሆነ ግን You are a dead meat." አለችውና ቦርሳዋን ይዛ ተነሳች። "ይህን ደግሞ ማወቅ የማቅት አይምሰልህ? እከታተልሃለሁ፤" ለመሰናበት ጊዜ እንኳ አልሰጠችውም። በሩን በኃይል በርግዳ ከፍታ ወጣች።

ካሣሁን እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ አልተከተላትም። እዚያው የተቀመጠበት ቁጭ ብሎ ቀረ። የምትመለስ የምትመለስም መሰለው። "መገላገሌ ይሆን፣ እግዜር ረዳኝ ይሆን?" እያለ ማሰላሰል ገባ።

ዴብራን ከሸኛት በኋላ በዓይነ ህሊናው ራሄል መጣችበት። ራሄልን ለማሸነፍ የመጀመሪያውን እርምጃ እንዳከናወነም ተሰማው። ከዚች እብድ መገላገል። ከዚያም ስንት ጊዜ ለፍቶ ተስፋ ቆርጠ የተቀመጠውን አሁን ግን ራሄልን የአገሩን ልጅ አግብቶ ቤተሰብ መሥርቶ መኖር በህሊናው መጣ። ራሄል "ማታ ማታ የሚደውልልኝ ወንድ ደስ አይለኝም፣ ለsex ብቻ የሚፈልገኝ ይመስለኛል" ያለችው ድንገት በሃሳቡ ብልጭ አለበት። ሰዓቱን ሲያይ ገና ከቀኑ አስር ሰዓት ነበረ። ስልኩንም አነሳ፣ ለራሄል ደወለላት። የሚፈልጋት ለsex ብቻ አለመሆኑን እንድትረዳለትም ጭምር። አገኛት፣ ቀን ብምድወሉ ገረማት። ቁም ነገር ያለው ጨዋታቸውን ጀመሩ።

ካሣሁን ዴብራን ያሰናበተበት ሰሞን ጓደኛው ፈጠነ በዴብራ አማካይነት ከተዋወቃት ሲንቲያ ጋር የጦፈ ፍቅር ይዞት ከተማው አልበቃ ብሎት ነበር። ሲንቲያ ፈጠነን በሁሉም ነገሩ ወደደችው። ረጋ ባይነቱ፣ ትህትናው ያልጠበቀችው ነገር ነበር። ፈጠነ የቸኮለበትን የሰገነት ላይ ጨዋታ በቶሎ አልጋበዘችውም።

"በመጀመሪያ ልወቅህ። ለዚህ ዓይነቱ በኔና ባንተ መሃል ለሚፈጠር ግኑኝነት አዕምሮዬ መዘጋጀት አለበት። እንዳው አገኘሁህ ብዬ ቶሎ የምፈጽመው ጉዳይ አይደለም፣" ብላ ቀደም አድርጋ ነግራው ኖሮ እሱም ቢሆን ቸኩሎ አለማድረጉ ነው መሰል እየወደዳት መጣ።

በዕረፍት ጊዜአቸው ተያይዘው ወይ ሲኒማ ወይ ሙዚየም ወይ ለስለስ ያለ ሙዚቃ የሚሰማበት የምሽት ክለብ ይሄዳሉ። አብሮ መዋል፣ አብሮ መጫወት የበለጠ መግባባትን ፈጥሮ በሁለት ተፋቃሪዎች መሀል ጽኑ መሠረት ያለው ግንኙነት እንደሚፈጥር በተግባር አስተማረችው። ፍቅር የሚመነጨው በመግባባት ከሚፈጠር ግኑኝነት እንጂ እንዲያው በቅርጽና በመልክ ተማርኮ ለወሲባዊ ስሜት በመሮጥ እንዳልሆነ እንዲገባው በተግባር አስተማረችው።

ሲንቲያ ፈጠነ ምንም ያህል ለወሲባዊ ግኑኝነት ቢቸኩል ስሜት አልሰጣትም። አብሯት ውሎ ሁኔታው ሁሉ ወደዚያ እየሄደ ካስቸገራት በዘዴ እንዳይቀየማትም፣ እንዳያኮርፋትም በማድረግ አሸኛኘቱን ታውቅበታለች። ትዝታዋን ይዞ እንዲሄድ የምታደርግበት ዘዴ ነበራት። ፈጠነ ያንን በውበት የተመላዋን ገላዋን ለመቋደስ ቢቸኩልም እሷ አለመዘጋጀቷን ስትገልጽለት ለጊዜው ኩርፍ ይልና ትንሽ ቆይቶ ይረሳዋል። በአንዴ አግኝቷት የሚፈልገውን ሁሉ አድርጎ እንደሚረሳት ልጅ አልሆነችለትም። ይልቅስ ሞክሮ ያቅተውና ስትለየው ማታ እቤቱ ይገባና ጭራሽ የበለጠ እያሰባት መምጣት ቀጠለ። ብቻውን ሲሆን በሃሳቡ መመላለስ እንደጀመረች እየገባው መጣ።

አንድ ወር ያህል በዚህ ሁኔታ ከቆየችው በኋላ አንድ ቀን ፈቃዱን ፈጸመችለት። እሱ ብቻ ፈልጎ ሳይሆን እሷም። እቤቷ ራት ጋበዘችው። ሻማ በርቶ እሷ በጥንቃቄ የሠራችው ራት ከተበላ በኋላ እንደወትሮው ሁሉ አንዳንድ ብርጭቆ የወይን ጠጃቸውን ይዘው ከሶፋ ላይ አረፍ አሉ። ሲንቲያ ሁኔታዋ ሁሉ ቀደም ሲል ከነበረው የተለየ መሆኑን ፈጠነ የተገነዘበው ቆየት ብሎ ነበር። ገላዋን የሚያሳይ ስስ ልብስ ለብሳ ሁኔታዋ ሁሉ በተለየ ፈገግታ የተሞላ ነበር። አነጋገሯ፣ አረማመዷ፣ አጠገቡ ቁጭ ብላ ጠቅላላ አኳሃኗ ከወትሮው የተለየ ወሲባዊ ቅኝት ቢኖረውም ፈጠነ መልዕክቱ አልገባውም ነበር። ለሲንቲያ ግን የመዘጋጀቷ ምልክት ነበር።

በዚህ ሁኔታ ለረዥም ሰዓታት ቆይተው ፈጠነ እንደሌላው ቀናት ሁሉ የሚሄድበት ሰዓት ደርሶ ሰዓቱን ተመለከተ። ለመሄድ መዘጋጀቱን ምልክት መስጠቱ ነበር።

"ምነው ሰዓትህን አየህ?" አለችው ሙዚቃ በመሰለ በለሰለሰ ቃና።

"መሸ፣ መሄጃዬ መድረሱ መሰለኝ?" አላት ዓይን ዓይኗን እያየ።

"የት ነው የምትሄደው?" አለችና ዓይኗን ሸኩርምም አድርጋ በፈገግታ አየችው።

ከዚህ በፊት ያላሳየችው ፈገግታ፣ ልብን ለሁለት ክፍል አድርጎ ነፍስ የሚነሳ ፈገግታ፣

"እቤቴ ነዋ! በዚህ ሰዓት ሌላ ቦታ የት ልሄድ?" አላት።

ብድግ አለችና ቁልቁል እያየችው ቀኝ እጇን ዘረጋችለት። ልብ የሚሰነጥቅ ፈገግታ አከላበት፣ "ዛሬስ አትሄድም፣ እዚህ ነው የምታድረው፣" አለችና የጨበጣትን እጅ እየጎተተች ወደ መኝታ ቤቷ ገባች። እሱም እየተወላከፈ ተከተላት።

*(በሚቀጥለው እትም የመጨረሻው ክፍል ይቀርባል)*

# ዕጣዬ

## ከአብረኸት

### ከአለፈው የቀጠለ

### ክፍል ፯

የአባቴን ካዝና ጎበኘሁት። ከጎጆ ቤት ከዳን አንድ ሳር መምዘዝ ምንም ያህል ጉዳት አያመጣበትም። የተጠራቀመውስ ሃብቱ ቢሆን ያው ለገንጣይ ወንበዴዎች ሊሰጠው አይደል? ሰውና ሰው የሚጨራረስበት የጦር መሣሪያ ሊገዛበት አይደል? ኤርትራን ከኢትዮጵያ ሊያስገነጥል አይደል? በዚሁ ገንዘብ እኔንና ሰይፍዬን ሊለያየን አይደል? "እንዴት የአባቷን ገንዘብ ዘርፋ ከወንድ ጋር ትኮበልላለች ለሚሉ ሰዎች ይህን ማለት እፈልጋለሁ።

ይህን አድርጌ ከምወደው ልጅ ጋር ስጠፋ ለአባቴ ግድ አልሰጥኝም። እናቴን በርግጥ አሳዝኜ ይሆናል። ምንም አማራጭ አልነበረኝም። እና እዚህ ቆይቼ የማልወደውን ተከስተን አባቴን ለማስደሰት ስል አግብቼ መኖርን ደግሞ አልፈልግም። እና ጠፋን።

በእቅዳችን መሠረት ሰይፉ ከእኔ ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ወደ ጎንደር ሄደ። እዚያ የሚያውቀው የድሮ ጓደኛው ጋ። እኔም በሁለተኛው ቀን ማታውን ጠፍቼ አውቶቡስ ተራ አካባቢ ሄጄ አደርኩ። ቲኬቴን ቆርጬ በጠዋት አውቶቡስ ተሳፈርኩ። ቀይ ሽብር ቀዝቀዝ ያለበት ወቅት ቢሆንም በየቦታው የይለፍ ወረቀት እንደሚጠይቁ ሰምተን ስለነበረ ሰይፉ ተሟሙቶ በጉቦ ለኔም ለሱም ያገኘው ወረቀት ስለነበረ ብዙም አልሰጋሁም።

ከዓይኔ በላይ ከፍ ብሎ ያለችውን ሁለት መስመር መሰል ጠባሳ አይተው ደግሞ ተገንጣይ እንዳይሉኝ ፊቴን ተከናንቤ ልክ የቤት ሠራተኛ መስዬ ነበር። አውቶቡስ ገብቼ ቁጭ እንዳልኩ ሆዴ ቡጭ ቡጭ ማለት ጀመረ። ፍርሃት ፍርሃትም ይለኝ ጀመር።

እናቴ ትዝ አለችኝ። መጥፋቴን ስታውቀው እንዴት ትሆነው ይሆን እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። ይህ ጊዜ ትልልቅ ልጆች ላሉዋቸው ቤተሰቦች ምን ዓይነት የጭንቅ ጊዜ እንደነበረ ታውቁታላችሁ። አውቶቡሱ መንቀሳቀስ ሲጀምር የበለጠ ፈራሁ። የጨለማ ጉዞም መሰለኝ።

አውቶቡሱም ጡሩንባውን እየነፋ በፍጥነት ከከተማው እየወጣ ሳለ ለመጨረሻ ጊዜ አዲስ አበባን በመስኮት ተሰናበትኳት። ጠዋት ስለነበረ ብዙም ሰው በመንገድ ላይ አይታይም ነበር። በልዑል መኰንን ትምህርት ቤት፤ በጉጃም በረንዳ፤ በአባኮራን አድርጎ ዮሀንስ ቤተክስቲያን አጠገብ ሲደርስ የድሮ ትምህርት ቤቴን የአርበኞች ትምህርት ቤት አካባቢን ሳየው ጓደኛዬ አምሳለ ትዝ አለችኝ። እንባዬ ዓይኔን ሞልቶ ፍረሽ ፍረሺ አለኝ። ይሄኔ ባትሞት ኖሮ እኮ አብራኝ ትጠፋ ነበር ብዬም አሰብኩ። እንጦጦ ጋራውን እንደወጣን ቁልቁል አዲስ አበባን አይቼ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበትኳት።

የስደቱ ጉዞ ተጀመረ። ለምለሟን አገሬን፤ ተራራዋን ሸለቆዋን በዚህ ጉዞ ላይ ባየሁባት ዓይኔ ከዚህ በፊት አይቻት አላውቅም። ድሮ የማያት እንዳው ለማየት ያህል ብቻ ነበረ። ዛሬ ግን በስንብት ዓይኔ ስለሆነ ያየሁዋት ልዩ ስሜት ነበር በውስጤ የሚንከላወሰው። የተወለዱባትን፤ አፈር ፈጭተው ያደጉባትን ቦታ ጥሎ መሄድ ምን ያህል ባር ባር እንደሚያሰኝ ሳታውቁት አትቀሩም። አውቶቡሱ ለምሳ ሲቆም እኔ አልወርድኩም፤ በመስኮት በኩል ቆሎ ገዛሁና በላሁ። አልራባኝም ነበር። የምጠፋ ሰው መስዬ ላለመታየት ነበር ጥረቴ።

የሁለት ቀኑ ጉዞ አልቆ ጎንደር ከተማ ስገባ ያ ሁሉ ጭንቅት፤ ያ ሁሉ ሃሳብ ለቀቀኝ። ለካ ብቸኝነቴ ነበር። እዚህ ሰይፉን ስለማገኘውና ከእንግዲህም ባለመለያየት አብረን ስለምንሆን በውስጤ ትልቅ ተስፋ ያዘለ ደስታ ወረረኝ።

ከአውቶቡሱ ወርጄ ሰይፍዬን በዓይኔ ብፈልገው አጣሁት። ደነገጥኩ። ትንሽ ብክን ብዬ ዓይኔ ሲቃኝ ከኋላዬ አንድ ሰው ትከሻዬን ነካ አድረገና ዞር አልኩ። የማላውቀው ሰው ነበር። ስሜን ጠራና ሰይፉ ቤት ሆኖ እንደሚጠብቀኝና እሱ እኔን ለመጠበቅ እንደመጣ ነገረኝ። በጣም ደነገጥኩ። ምንም ሳልለው ዓይን ዓይኑን ማየት ጀመርኩ። ከሰይፉ ጋር የነጋገርነው እንዲህ አልነበረም። ራሱ መጥቶ እንደሚጠብቀኝ ነበር የነገረኝ፤ ታዲያ ምን ተፈጠረ።

ግራ እንደገባኝ ገባውና "እይዞሽ እንሂድ፣ እኔ ነኝ የሰይፉ ጓደኛ" አለኝ።

አሁንም ዝም ብዬ እንባ በሞላው ዓይኔ አየው ጀመር።

"መጠርጥርሽ ጥሩ ነው፤" አለኝና ሰይፉ የነገረውን እኔና ሳይፉ ብቻ ከምናውቃቸው ነገሮች አንዱን ምልክት እንዲሆን ሲነግርኝ ነፍሴ መለስ አለ።

"ምነው ሰይፉ ደህና አይደለም እንዴ? አልኩት ሆዴ እየፈራ። አሁን ደግሞ ፍርሃቴ ለሰይፉ ነበር። ታስሮ ይሆን?

"እሱስ ደህና ነው፤ ደህና ያልሆነው ከተማው ነው።" አለችኝና ቦርሳዬ ይዞ ወደ ቤቱ ጉዞ ጀመርን።

በመንገዳችንም ላይ ጎንደር ስላለው ችግር አወራልኝ። መላኩ የሚሠራውን ግፍ ነገረኝና እዚህ ብዙ መቆየት እንደሌለብን፤ እስክንሄድም ድረስ ውጪ መውጣት እንደሌለብን ነገረኝ። ሰይፉም እኔን ሊቀበል ያልመጣው ለዚህ ፍራቻ እንደሆነም አወቅሁና ተጽናናሁ።

አቤቱ እንደደረስን ሰይፉ ገና ከበሩ ተቀበለኝ። ተቃቅፈን ሳንላቀቅ ሁለታችንም እንባችንን ለቀቅነው። እንላቀቅ ስንለው የሰይፉ ጓደኛ አበራ ታዘበን መሰለኝ "በል ልቀቃትና ትረፍበት።" አለው። የአበራ ታናሽ እህት መጥታ ቦርሳዬን ተቀበለችና ተሳስመን ተዋወቅን። እቤት ገባን። የሚበላ ነገር ከቀራረበልን በኋላ ጨዋታ ተጀመረ።

የሰይፍዬ ጓደኛ አስተማሪ ነበረ። ከአዲስ አበባ ነው የሄደው። ከሰይፉ ጋር የትምህርት ቤት ጓደኞች ነበሩ። እነሱም ቢሆን ከተለያዩ የቆየ በመሆኑ አብዛኛው ማምሻውን ያወሩት ስለጥንቱ ጊዜ ጓደኝነታቸው ጊዜ ነበረ። እኔና የሰይፉ ጓደኛ እህትም የራሳችንን ጨዋታ ጀመርን።

እቤት መዋል እንጂ ውጪ መውጣት እንደሌለብን አጥብቀው ነግረውናል። ስለዚህም እቤት መዋል ግድ ሆነብን። ትምህርት ቤቶችም በረብሻ ምክንያት የተዘጉ በመሆናቸው የሰይፉ ጓደኛም ጠዋት አንዴ ሄዶ ሪፖርት በማድረግ ተመልሶ እቤት ተከትቶ እንደሚውል አጫወተን።

በተለይ አዲስ ሰው የታየ እንደሆነ ከሌላ ቦታ ሸሽቶ የመጣ ፀረ አብዮተኛ ተብሎ ተይዞ እንደሚሰቃይ ሲነግረን ደነገጥን። ጎንደር እንኳን ከውጪ ከሌላ ክፍለ ሀገር ለመጡ ወጣቶች ይቅርና እዛው ተወልደው ላደጉት አደገኛ ቦታ በመሆኗ በብዛት እየጠፉ ወደ ሱዳን መግባታቸውን ነገሩን። መንገድ ላይ ዝር የሚል ወጣት እንደሌለ ሲነግሩን እኔ የበለጠ ደነገጥኩ።

እኛም ምንም አመጣጣችን ሌላ ቢሆንም አምልጦ የሚሄድ የመንግሥት ተቃዋሚ ተደርገን እንደምንወሰድ ስለዚህም መንገዱ ተገኝቶ እስከምንወጣ ድረስ እዚሁ እቤት ውስጥ ተደብቀን መዋል እንዳለብን ነገሩን። ሌላ ምን አማራጭ ነበረን። ቀደም ሲል በነገርኳችሁ ታሪኬ ላይ እንዳስረዳሁት እኔ የፖለቲካው ጉዳይ ስለማይገባኝ ይህ ሁሉ ነገርም አልገባኝም። ለማንኛውም አንዴ ከቤት ወጥቻለሁ፣ ከምወደው ሰይፉ ጋር ነኝ ያለሁት፤ የሚያጋጥመኝን ሁሉ መቀበል አለብኝ።

በሚቀጥለው ቀን የጉዞአችን ዕቅድ ወጣ። የሚመራ ነጋዴ ተፈልጎ ተገኘ ብሎ የሰይፉ ጓደኛ ነገረን። ነጋዴውም ገንዘብ እንደሚከፈለውና ጉዞውም ሌሊት ሌሊት እንደሚሆን አወቅን። ሳምንት በማይሞላ ጊዜ እንደምንቀሳቀስ ሆነ። እስከዚያው ድረስ መንገድ ላይ ሊያጋጥመን ስለሚችለው ነገር ሁሉ የሰይፉ ጓደኛ የሰማውን ሁሉ አጫወተን።

ይህ በዚህ እንዳለ ሆኖ የጉዞአችንን ቀን በመጠባበቅ ላይ ባለንበት ጊዜ አንድ ምሽት ላይ የሰይፉ ጓደኛ ሁለት ሌሎች ጓደኞቹን ይዞ እቤት መጣ። አንደኛው በነሰይፉ ዕድሜ አካባቢ ሲሆን ሌላኛው ትንሽ በለጥ ይላል። ትንሽ በለጥ ያለው ከኤርትራ የጣ እንደሆነ ወዲያው ነው ያወቅሁት። እሱም ሲያየኝ እኔም የኤርትራ ልጅ እንደሆንኩ አወቀኝና ልክ እንደተዋወቅን በትግርኛ አነጋገረኝ። እኔ በአማርኛ መለስኩለት።

ሳቅ አለና "ምነው አትችይም እንዴ ትግርኛ፣" አለኝ።

"እችላለሁ፤ እዚህ ያሉት ሌሎቹ ግን ስለማይችሉ ሁሉ በሚችለው ቋንቋ ላናግርህ ብዬ ነው፤" አልኩት በትግርኛ።

ወሬ ቀጠለ። ትንሽ ቆይቶ ለምን እንደመጡ ገባኝ። በትግርኛ ያናገረኝ ሰውዬ ቀደም ሲል የወጡ ዘመዶች ሱዳን ስላሉት እንሱ እንዲረዱን ሃሳብ ለመስጠትና በዛውም አንዳንድ የፖለቲካ ቅስቀሳ ሊደረግልን እንደሆነ ገባኝ።

እንደነገርኳችሁ የፖለቲካ ነገር ብዙ መከታተል ባልፈልግም በዚህ ጉዞ ላይ ብዙ ነገር ማወቅ እንዳለብኝ በመረዳቴ ይህን ውይይት በደምብ ማዳመጥ ፈለግሁ። ውይይቱ በመጀመሪያ በደርግ ማንነት ላይ ተካሄደ። እኛ ማለትም ሰይፉና እኔ በደምብ እንድንረዳ ተደረገ።

ቀጥሎ የመጣው ርዕስ የብሄር ጥያቄ የሚለው ነበር። በዚህ ርዕስ ሰፋ ያለ ንግግር ያደረገው ቅድም የነገርኳችሁ የኤርትራው ልጅ ነበር። ይህኛው ክፍል ረዥም ሰዓት ፈጀ። የኤርትራ ጥያቄ የኮሎኒ ጥያቄ ነው፣ የሚል ነበር ነጥቡ። ሌሎቹም ደግፈው ነበር የሚናገሩት።

ያልገባኝ ነገር ኖሮ ልጠይቅ ብፈልግም መጀመሪያ ላይ አውቄ ዝም አልኩ።

ከኤርትራ የመጣው ልጅስ እሺ "ኤርትራ ቅኝ ተይዛለች፤" ቢል ያምርበታል። የሌሎቹ ነገር ነበር የገረመኝ። በተለይ የሰይፉ ጓደኛ። ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት ሲል "ቀኝ ገዥዋ እኔ ነኝ" ማለቱ ይሆን? ነገሩ አልጥምሽ ሲለኝ አንድ ጥያቄ አቀረብኩ። "ቅኝ ግዛት ማለት ምን ማለት ነው?" የሚል ነበር።

ጥያቄዬን እንደጨረስኩ ሁሉም ለጥቂት ጊዜ ትክ ብለው አዩኝ። ከዚያም በፍጹም ሊገባኝ ያልቻለ ሰፊ ትንተና ተሰጠኝ።

"እንዳላችሁት እንዱ የኤኮኖሚ ጭቆና ነው። ታዲያ የትኛው አማራ፣ ኦሮሞ፤ ጉራጌ ወይም ሌላ ኢትዮጵያዊ ነው በኤርትራ የመበዝበዣ አውታር የምትሉት ያለው።" ብዬ መልሼ ጠየቅሁ።

የኤርትራው ልጅ ከፋኛ ገላመጠኝ። "አንቺ ኤርትራን ታውቂዋለሽ?" አለኝ በቁጣ ቃል።

"ሄጄ አላውቅም እንጂ አባቴ ነግሮኛል።" አልኩኝ።

"ስለማታውቂ ነው፤" አለኝ መልሶ።

"የማውቀው ነገር ግን አለ። በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ግን ትልልቅ የኤኮኖሚ አውታር የሆኑት የኤርትራ ሰዎች መሆናቸውን አውቃለሁ።" አልኩኝ። በርግጥ ንዴቴ መጥቶ ነው እንጂ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ይህን መናገር ባልነበረብኝ ነበር።

"ይህማ ባንዳዎች የሚሉት ነው። ከአንቺ ይህን አልጠብቅም። በተለይ ቅኝ ተገዥ ከሆነው ኤርትራ የተወለድሽ ሆነሽ ይህን ማለት ትክክል አይደለም።" አለኝ ሌላኛው ልጅ።

ሰይፉ ጎኔ ነበረና ቁንጥጥ አደረገኝ። መለስ አልኩና "አአይ ስላልገባኝ ነው የጠየቅሁት፣" አልኩና በማለሳለስ መልክ ተናገርኩ።

"በተቻለ መጠን ይህን አነጋገር ብትረሽው ጥሩ ነው፤ እኛ ጋ በየዋህነት እንደተናገርሽ ሌላው በተለይ በጉዞሽና በስደትሽ ወቅት ብታወሪው ትልቅ ችግር ውስጥ ይከታችኋል።" ብሎ ያው ልጅ ተናገረ።

እኔም ዝምታዬን መረጥኩ እሺ እንዳላችሁኝ ብዬ። የኤርትራው ልጅ ግን ከፋኛ አየኝ።

ዛሬ ይህን ታሪክ አሜሪካ ሆኜ፣ በተለይም በዘር በጎሳ ተነቋቁረን ባለንበት ጊዜ ይህችን የዛን ዕለት ጎንደር እያለሁ የተወያየናትን ነገር እንዳስታውስ የሚያደርጉኝ ብዙ ሁኔታዎች ስላሉ ነው። የፖለቲካ ሁኔታ አልገባሽ አለኝ የምለውም ከዚሁ ነው። ያኔ እንደዛ ወዳጅ ሆነው ሲደጋገፉ የነበሩት የሰይፉ ጓደኛና ያ የኤርትራ ልጅ ዛሬ እዚህ አሜሪካ እንደ ጠላት እየተያዩ እንኳን ሲገናኙ ለመነጋገር ሊደባደቡ ተገባብዘው በገላጋይ ምክንያት እንደተውት በቅርብ አየሁ። አጅሬ ይኸ ኛው ሲጠቀምበት ቆይቶ ልክ ኤርትራ ስትገነጠል አፍንጫህን ላስ፣ ከእንግዲህ አማርኛም አላወራልህም፣ እኔ ኤርትራዊ ነኝ፣ ሲለው የሰይፉ ጓደኛ ካልደበደብኩ ብሎ ለገላጋይ እንዳስቸገረ ሰማሁ።

እንዳው እንደርድሬ ሌላ ታሪክ ውስጥ ከትቼ አላምታታና ወደ ጎንደር ልመልሳችሁ። የዛች ዕለት ምሽት ውይይት ላይ የሚሰማኝን በመጠኑ ብናገር ያለሁበት ሁኔታ ስሜቴን ሰፋ ባለ መልኩ እንድገልጽ አልረዳኝም። ለማንኛውም የሚባለውን ሁሉ የተቀበልኩ መስዬ ለመታየት ሞከርኩ ውስጤ ግን እንደበገነ ቀረ።

ውይይቱ ሊነጋጋ ሲል ነበር ያለቀው። ሁሉም እዛው ቤት አደሩ። ልንተኛ ስንል ሰይፉ ጋር በመጠኑ አወራን። ይህን ስሜቴን ወደፊት ዓላማችን እስኪሳካ ድረስ ላለማውራት መወሰኔን ስነግረው ደስ አለው። በዛን ዕለት ውይይት ምንም ነገር ያልተናገረው ሰይፉ ነበር።

በዚህ መልኩ ጥቂት ቀናት እንደቆየን መንገድ ይመራናል የተባለው ሰውዬ መሂጃው ደረሰና እኛም ከሰይፉ ጓደኛና ከእህቱ ጋር ተሰነባብተን የጎንደር ከተማን ለቀቅን። እውነተኛውን የስደት ጉዞ ጀመርን።

ይቀጥላል

**ውድ አንባብያን**

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኸት (የብዕር ስሟ ነው) በኑሮዋ የገጠማትን ታሪክ በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የስደት ጉዞና ኑሮ ታሪክ ለአንባብያን እንዲጥም አድርገን ከማቅረብ በቀር የጨመርነው ወይም የቀነስነው ነገር የለም። እሷ አሁን ያለችው አሜሪካን አገር ሲሆን ያለችበትን ቦታ በሷ ጥያቄ መሠረት ከማቅርብ ተቆጥበናል።

# ላንዳፍታን በሞቅታ!

ጣጤው (ከአትላንታ)

ጠጪ እንኳ አይደለሁም። ያው እንደተለመደው ሁለት ሦስቷን ኳ አደርጋለሁ (እኔ ልሙት ከዛ በላይ አልችልም)። በሞቅታ የሚወነጨፍ አዕምሮን ይዞ ከወረቀትና ከብዕር ጋር መቀመጥን የመሠለ ፀጋ አጋጥሞኝ ቁጭ! ሆሆ!

እና እንዴት ናችሁ ላንዳፍቶች? ምን እንደማወራችሁ ግራ ገብቶኛል። ህይወትና የቴሌቭዥን ዓለም ተደበላልቀውብኛል። ፀጉሬን አበጥሬ ጃኬቴን ደርቤ ወጣ ስል የማገኘው ዓለም ራሱን የቻለ ታሪክ አለው። ከቤቴ ሳልወጣ በቴሌቪዥን መስኮት የምመለከተው ዓለም ደግሞ የሚገርምና ወየው ጉድ! የሚያሰኝ ነው። ሁለቱ ሲዋሀዱ የፈረንጅ አገር ህይወት ትርጉም ታገኛለች! ይህ ገንጠልጠል ያለ የብቸኛ የፈረንጅ አገር ኑሮ ጣዕም የሚያገኘው በየቀኑ በቴሌቪዥን ከሚቀርበው መልዕክት ጋር ሲጣጣምና ሲጨቃጨቅ ነው። ከዛ በላይ መንፈራገጥ... የት ሊደረስ?... ሠርቶ፣ ብልቶና ጠጥቶ፣ ቴሌቪዥን ተመልክቶ፣ እዳ መክፈል። ከዛ በኋላ እፎይ ብሎ ፎቴው ላይ ጋደም ብሎ እንደገና ቴሌቪዥኑን መክፈት! ለተፈለገው ዓይነት ነገር የሚስማማ ፕሮግራም ይቀርባል። ቴሌቪዥኑ ቢያመልጠው ሬዲዮውና ጋዜጣው ያመጡታል። INFORMATION በዝቷል።

ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ህይወት ራስዋ በፕሮፓጋንዳ መመራት ጀምራለች ብሎ የሚያምነው ፈረንሳዊው ፀሀፊ JACQUES ELLUL "ፕሮፓጋንዳ፣ በፖለቲካ ዓለም ውስጥ ብቻ ሳይወሰን ነፍስና ሥጋንም ጨምሮ ህይወትን ጨምድዶ በመያዝ የዘመኑን ሰው ኑሮ ወዲያና ወዲህ እያላጋው ነው" ብሎ ነበር። "ፕሮፓጋንዳ" በሚለው መጽሀፉ ላይ በተለይ "ተምሮአል" የሚባለው ሰው ኮሚክ ዓለም ውስጥ ይገኛል። ባንድ በኩል ፕሮፓጋንዳ አያታልለውም "ተምሯልና" ይባልለታል። ሀቁ ግን የፕሮፓጋንዳ ዋና ቀለብተኛ ይኸው "ተማረ" የሚባለው ወገን ነው ይላል። INFORMATION በዝቷል። በየደቂቃው በየሰዓቱና በየቀኑ ሁሉ ዓይነት ዜና ይፈልቃል። ምሁርም ከቀረቡለት አርእስቶች ውስጥ እየመረጠ ምሁራዊ አስተያየቶቹን ይጨብጣል። የተማረው ለምንድነውና?

ሶማሊያ (ትዝ አለቻችሁ?) ምን ላይ ደርሳ ይሆን? የሶማሊያን ብጥብጥ ገና እንደተያያዝኩት ናይጀሪያ፣ ሩዋንዳ፣ አጂ ሚምሠን፣ ሄይቲ... አረ ምኑ ቅጡ!... ተደራረቡብኝ። ዓለሚቷ ተቀላጥፋብኝ ቁጭ!

የሶማሊያው ብጥብጥ ግዜ የጄኔራል አይዲድ ቲፎዞ ነበርኩ። አሜሪካኖቹ "ረሀብተኛ ልንመግብ ወታደር ልከናል" ሲሉ "እሂሂ!" ብዬ ነበር። ሶማሊያ ውስጥ ሲገቡ የሚያሳየው የኒውዮርክ ታይምስ ግንባር ፎቶግራፍ (DEC. 9, 1992) በጣም አስቆኛል። "U.S. FORCES ARRIVE IN SOMALIA-ON MISSION TO AID THE STARVING" የሚል አርእስት ሥር ፊቱን ከሰል የተቀባ የፈረንጅ ወታደር መትረየሱን ደግኖ በቁጣ መልክ ይራመዳል።

ከጎኑ አንድ የቲቪ ካሜራ ቦግ ብሎ ከበራው መብራቱ ጋር በትከሻው የተሸከመ ጋዜጠኛ ይከተለዋል። አሁንም እዛው አጠገብ ሌላ ጋዜጠኛ ካሜራውን ዓይኑ ሥር አስጠግቶ ፎቶግራፍ ያነሳል። ከነዚህ ሁሉ ወደ ኋላ ቀረተ ብሎ በትከሻው ቦርሳ ያንጠለጠለና የቤዝ-ቦል ኮፍያ ያደረገ ሰው ተዝናንቶ ይራመዳል። ይሄን ሁሉ የሚያሳየን ፎቶ ያነሳው የኒ.ታ. ጋዜጠኛንም እንግዴህ አትርሱ።

የተራበ ለመመገብ መትረየስ መንጋጋቱ ገርሞኝ ነበር። ጦርነት ነው እንዳልል ጋዜጠኛውበዛብኝ፤ ልክ እንደጠረጠርኩት ገጠመልኝ! የሶማሊያ ጉዳይ እርዳታም ሳይሆን፣ ጦርነትም ሳይሆን፣ ትርዒት ነበር--የወታደር ትርዒት! እንግዲህ ይሄ ሁሉ የሚሆነው የዛየሩ ሞቡቱ ሴሴ ሲኮ ከአሁን አሁን ተገለበጡ እያልኩ በመጠባበቅ ላይ እያለሁ ነበር (በነገራችን ላይ ኸርማን ኮኸን-ታውቋቸው የለ? የሞቡቱ ጓደኛ መሆናቸውን አንብቤ ገርሞኝ ቁጭ ብያለሁ)።

ሞቡቱን ትቼ የሶማሊያው መሪ ጄኔራል አይዲድ ላይ አይኔን እንደጣልኩ ሩዋንዳ ቦግ ብላ ታየችኝ-ቢቲሊቪዥን! የሬሳ መዓት! የተደፋ ሬሳ፣ የተንጋለለ ሬሳ፣ የተቆራረጠ ሬሳ! የሩዋንዳው ግድያ በጣም አሳዘነኝ--ገረመኝም። ለምን ተብሎ? ይህን ያህል ታብዷል እንዴ? አሰኝቶኛል።

ሩዋንዳን ከሶማሊያ ጋር እየጠቀለለ የሚያጎርሠኝ ቴሌቭዥን ናይጀሪያንም ጎትቶ

ያመጣና "ምን ይመስልሀል?" አለ። INFORMATION ሲደራረብ! "ናይጀሪያ ደሞ ምን ልሁን ነው የምትለው? አልኩ።

ፕሬዚዳንት ባባንጊዳ ከሥልጣን ውርደው ናይጀሪያ ውስጥ የሲቪል መንግሥት ይመጣል የሚል ግምት አልነበረኝም። ሆኖም ለሲቪል መንግሥት መምጣት የነበረው ግፊት (በተለይ የፈረንጆቹ) በግርግር የሲቪል መንግሥት ሊያመጣ ይችላል ብዬ ጠርጥሬ ነበር፤ ልክ ሱማሊያ ላይ የተካሄደው ፕሮፓጋንዳ "አይዲድ መያዛቸው ነው" ብሎ እንዳስጠረጠረኝ። የጠረጠርኩት ሁሉ ሳይሆን ቀረ!

(ይቅርታ ፊት ለፊቴ ያለው ቴሌቪዥን ላይ የማየው ሠቀጠጠኝ! ብዙ ሰዎች ክብብ ብለው መንገዱ ላይ ቀና ደፋ የሚል አንድ ሰው ይደበድባሉ፤ በጡጢም በዱላም ይዠልጡታል። የሠውየው ደም ፍንጥቅ ብሎ ቴሌቪዥኔ ዓይን ላይ ተለደፈ! -- ሄይቲ) ሄይቲ ላይ አቋም የለኝም!

ሶማሊያም፣ ናይጀሪያም "ይቅርብን" ያሉት የ"ዲሞክራሲ" ለውጥ ሞዛምቢክም ውስጥ ገብቷል--የሚቀበለው ቢገኝ። በሞዛምቢክ ገጠር ለገጠር የተሠማሩት የዲሞክራሲ ሀዋርያዎች በየደረሱበት የሚቀርብላቸው ጥያቄ "ይቺ ዲሞክራሲ ቆንጅዬ ነገር ነች ነው የምትሉን?" የሚል ነው። በለጭ ፓኮ ውስጥ የተጠቀለለች፣ አላይዋ ላይ D የሚል ፊደል የተቀረፀባት ቆንጅዬ የዲሞክራሲ ከኒን፣ እንዴ ሲውጧት ... " ሻዛም" ...ህዝብ አዳሜን ዲሞክራት የምታደርግ ይመሥል!

ልቤን ያስጨነቀው የሩዋንዳው ነገር ነው። ስለ ቱትሲዎችና ሁቱዎች የማገኘውን ሁሉ ማንበብ ጀመርኩ፣ በቴሌቪዥንም መከተስ ቀጠልኩ። ቴሌቪዥን! የራሱን አጀንዳ እየደረደረ በአይንና በጆሮ ገብቶ ከአንጎል ጋር የሚወያይ "ምትሀተ ሣጥን"።

የሩዋንዳን ሁኔታ በመከታተል ላይ እንዳለሁ ሌላ ጉድ በቲቪ ቀረበ።

መሸምጠጥ አይሉት፣ መሥገር አይሉት፣ አንድ ነጭ ፎርድ ብራንድ በቀይና ሰማያዊ መብራቶች ታጅቦ በሎስ አንጀለስ አውራ ጎዳና ላይ ይንዛል፣ ይዘልቃል--ለብዙ ዱቂቃዎች! ከአሁን አሁን Staring O.J. Simpson የሚል ክሬዲት የማነብ መስሎኝ ለጥቂት ሴኮንድ ራሴን አሞኘቻለሁ። ድራማቲክ ነው የምለው የሽዋዝኔገር ፊልም T-2 እንኳ የኦጄን ዓይነት ድራማቲክ አልነበረውም። የኦጄን የብራንኮ ጉዞ ተመታትለዋል ከሚባሉት 95ሚሊዮን ህዝቦች ውስጥ አንዱ መሆኔን ስገልፅላችሁ ያለአንዳች መሸማቀቅ ነው። ከብዙዎቻችሁ ጋር አብረን ነበርን--እዛው ቴሌቪዥኑ ፊት! ቀለባችን ፊት!

የኦጄ ሲምሰን ጣጣ ሰማይ ምድሩ አልበቃ ብሎት ጠበቃዎቹን Marcia Clarke እና Bob Shapiroን ዋነኛ ተዋንያን በማድረጉ የጠበቆቹ ሚና ራሱን የቻለ ትርዒት እየፈጠረ ነው። የኒኮል ሲምሰንን ቴሌፎን ሎግ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት የከሣሽ ጠበቃ Marcia Clarke ነበሩ። ፍ/ቤቱ መድረክ ላይ ቆመው በፖስታ ታሽጎ የነበረውን ሎግ በእጃቸው ጨብጠው ምንነቱን እያስረዱ ለዳኛው ሊያቀርቡ ሲሉ፣ የተከሳሽ ጠበቃው Shapiro ብድግ ብለው ድምፅ ማጉያው ፊት ቆመው "ይሄ ሁሉ Grand Stand እንኳ አስፈላጊ አልነበረም" በማለት አቤቱታ አቀረቡ። የShapiro አባባል "ታድያ ሽር ጉዱ ምንድን ነው?" የሚል አይነት ነበር። እንደመገረምና እንደመደንገጥም ሆነው የኦሙት Marcia Clarke "I can't believe I am hearing this from Shapiro.....This is the proper way " አሉ።

Shapiro አመቺና አጋጣሚ ባገኙ ቁጥር Marcia Clarkeን ከመተቸትና ከማንጓጠጥ አይቆጠቡም። እንዴ እንዲሁ Marcia Clarke ዳኛው ፊት ቆመው የተለመደ ጥብቅናቸውን ሲያቀርቡ የShaprio ቴሌፎን ጮኸ! ፍርድ ቤት ውስጥ! Marcia Clarke ንግግራቸውን ያቋረጣቸው የቴሌፎን ጩኸት ሆን ተብሎ የተደረገ ነገር ነው በሚል መልክ አውራጣታቸውን ወደ Shapiro ጠቁመው ዳኛውን እያዩ "Is that Council's phone?" በማለት አቤት አሉ። የተቀመጡበትን ወንበር ሳይለቁ ቂጢጥ ብለው ከማፈር ፈገግታ ጋር Shapiro ፍ/ቤቱን ይቅርታ ጠይቀው ተቀመጡ። በየቀጠሮው ቀን እየተባባሰ የሄደው የጠበቆቹ ድራማ ጣራ የነካው የከሣሽ ጠበቃ____አተካሮአቸውን ለዳኛው ሲያቀርቡ Bob Shapiro "BullShit" የሚል ቃል የተናገሩ ግዜ ነበር። የሻፒሮ አባባል ለፍ/ቤቱ የቀረበው አቤቱታ "ቱልቱላ" ነው ማለታቸው ነበር። ሆኖም ወዲያውኑ የስሜን መጀመሪያ ፊደሎች (BS) በመጠቀሜ ፍ/ ቤቱን ይቅርታ እጠይቃለሁ ብለዋል። Marcia Clarke ቆንጅዬ ሴት አይደሉም ሲባል ሰምቻለሁ። የቁንጅናውን ነገር ተወት አድርገን ዓይናቸውን ብንመለከት ገዳይ ዓይን ያላቸው ጠበቃ ናቸው። ፍጥጥ ብሎ የወጣው ድቡልቡል ዓይን ኢቶ የሚባሉትን

ጢማም ዳኛ ሲለማመጥና፣ ቅንድብ እያርገበገበ ጎረጥ ጎረጥ ሲል ተመልካቹን ማነጋገር የሚችል ሀይለኛ ዓይን ነው። በተጨማሪም ከሚለብሱት ሚኒስከርት ውስጥ አንዳንዴ ብቅ እያለ የሚታየው እግራቸው ቆንጆዬ መሆኑን ማ ይከራከራል?

የ አጀን ጣጣ ለፍ/ቤቱ ተወት አድርገን ወደ ሌላው ዓለም እንመለስ። አዎ ከሱማሊያ ነበር የጀመርኩት፤ የሱማሌ "ቴክኒካል" ትዝ ይላችኋል? ጀርባው ላይ መትረየስ የተጠመደበት ቶዮታ ፒክ አፕ?

ጥይት ያልበሳው የሞጋዲሾ ግድግዳ አልነበረም። የተበሳሱ ቤቶች፣ የፈራረሱ ፎቆች፣ ግማሽ ጣራው የት እንደገባ ያልታወቀ ቤት...!

አንድ አይዲድን የሚደግፍ ሱማሌ ጋር ስንወያይ "ታዲያ ሞጋዲሾን ለምን ያፈራርሳሉ?" ብዬ ጠየቅሁት። እንደማቅማማት አለና "ጦርነት ነዋ ሌላ ምን ትጠብቃለህ?" አለኝና ቀጠል አድርጎ "ለመሆኑ ከተማ ሲፈርስ፣ መብራት ሲጠፋ፣ ቴሌፎን ሲቋረጥ፣ የቧንቧ ውሀ ሲደርቅ ማ ይመስልሀል በብዛት የሚጨነቀው? ማ ይመስልሀል በውነት?" ብሎ ጠየቀኝ። የምመልስለትን እያሰላሰልኩ ሳልጨርስ "አሜሪካኖቹ ናቸው የጨነቃቸው...ህዝባችን እንደሆን የሚኖረው ሜዳ ላይ ነው" አለኝና አረፈው። የሚገርም ፍልስፍና!

ከመገልበጥ መንችቀቅን የመረጡት ፕሬዚዳንት ባባንጊዳ የናይጀሪያን ምርጫ ቶርሽ ብለው ስልጣኑንም ለጀኔራል አባቻ አስረክበው ቁጭ እንዳሉ የምርጫው አሸናፊ ነኝ የሚሉት ማሹድ አቢዮላ ፈረንጅ አገር ሰንብተው እንደተመለሱ ጉድ ፈላ! ማሹድ አቢዮላ ደጋፊዎቻቸውን ሰብስበው አንድ ሠፊ አደባባይ ላይ ቆመው "ከዛሬ ጀምሮ የናይጀሪያ ፕሬዚዳንት እኔ ነኝ" ብለው አወጁ! ጀኔራል አባቻ (አዎ ፕሬዚዳንት ጀኔራል አባቻ) አዲስ የጨበጡትን ሥልጣን እንዲህ በአደባባይ የሚቀናቀን ደፋር መምጣቱ አብሽቋቸው "ይቺን ይወዳል!" በሚል መንፈሥ ማሹድ አቢዮላን አስጠፍረው ከርቸሌ ከተቱ። ካሁን አሁን ናይጀሪያ ትተራመሳለች እያለ የሚያወራው የፈረንጆቹ ጋዜጣ ናይጀሪያ በሠራተኞች አድማ መዋጧን ወዲያው እያከታተለ ማውራት ቀጠለ። የተባለውም ሳይሆን፣ አድመኞቹም ተመልሰው ወደ ሥራቸው ገብተው ናይጀሪያ በሰላም እስካሁን መቆየቷን አየን። የፈረንጆቹን "መልታይ ፓርቲና" "ዲሞክራሲ" እንደ ኢትዮጵያ እልል ጅላ ሳትቀበል ቀርታ ናይጀሪያ እስካሁን በሰላም መቆየቷ ገረመኝ። "NIGERIA IS NO BANANA REPUBLIC" አልኩ።

በአሜሪካኖቹ ዓይን ኢትዮጵያ የዲሞክራሲ አርአያ ነች-- ለአፍሪቃኖች። በቅርቡ ከአገር ቤት የተመለሰ ጓደኛዬ ጋር ስንጫወት ነበር።
እሱ አዲስ አበባ ውስጥ ሲዘንጥ እዚህ የሆነውን የፕሬዚዳንት መለሰን ጉብኝት አጫወትኩት።

በወሬ የሠማሁትን አንዲት ሳላስቀር ነገርኩት። "ሌላስ?" አለኝ።
"ሌላማ ያው አለ አይደል ጉብኝቱ እንዳልተሳካ ነው የሚነገረው" አልኩት። ከድሮ ጀምሮ "POLITIC IS A DIRTY GAME" የሚል እምነት እንዳለው የሚናገረው ይህ ጓደኛዬ እንደመገረም ራሱን ነቅነቅ አድርጎ "እኔ ደግሞ አዲስ አበባ ሆኜ ያየሁትን ልንገርህ ... በቴሌቪዥን ላይ ያየሁት መለሰ ዜናዊ የክብር ዘብ ሲጎበኙና ሀያ አንድ ግዜ መድፍ ሲተኮስለት ነው" አለኝ።

ገረመኝ! ለምን ስለመድፍ መተኮስ አልሰማሁም? ወይስ ይሄ ቱሻ ሲጠመጥመኝ ነው? "ምን ሆነሃል አንተ?" አለኝና "የአንድ አገር መሪ ሲመጣ የሚደረገውን ፕሮቶኮል ለመለሰ ዜናዊ መስሎህ ነበር እንዴ?... ሞኝ ነህና!" አለ።

ጉድ ፈላ! ስለ ቴሌቪዥን ዓለም የጀመርኩት ፅሁፍ ላይ የመለሰ ዜናዊን ጉብኝት ደነቀኩበትና ጽሁፌን በምን እንደምደመድም ጨነቀኝ።

....I WILL BE BACK WITH MORE ....STAY TUNED!!!

# የማወቅ ትርጉሙ ምንድን ነው?

ከአይን ምስክር (ሲልቨር ስፕሪንግ)

**የእኛ ኢትዮጵያኖች ችግራችን ምንድን ነው?**
<u>ገንዘብ፤</u>

**ገንዘብ እንዴት ማግኘት እንችላለን?**
<u>በመሥራት፤</u>

ምንድን ዓይነት ሥራ ብንሰራ ገንዘብ ልናገኝ እንችላለን? እንደየ ችሎታችን ማንኛውንም አይነት ሥራ ሳንንቅ ስንሥራ ብቻ ነው።

**ሥራ ለመሥራት ሰላም ያስፈልጋልን?**
አዎን ዋናው ሰላም ሲገኝ ብቻ ነው።

**እንዴት ሰላምን ማግኘት እንችላለን?**

እያንዳንዳችን ሰላማዊ ሰው ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው። በተጨማሪ ደግሞ ከህብረተሰቡ ውስጥ በአዕምሮ በሣል ሰዎች በመጀመሪያ ራሳቸው ራሳቸውን አሻሽለው ከመጥፎ ነገሮች ተቆጥበው ለህፃናትም ሆነ ላላወቁት አዎች ጥሩ ነገሮችን ሲያስተምሩ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ስለ ሰላም ማውራት ተገቢ ባለመሆኑ የተጀመረው ነገር ተግባራዊ ሣይሆን ቀርቷል። እድገት ልናገኝ የምንችለው፤ ራሳችንና ሀገራችንን ለማዳን የምንችለው እኛ ጤናማ ሰዎች ስንሆን ብቻ ነው። በተበሳጨንና ችግር ባጋጠመን ቁጥር ራሳችንና ሃገራችን ለመጉዳት አለመጣጣር። እኛ ሰዎች ቋሚዎች አይደለንም፤ "እኛ ከሞትን ሰርዶ አይብቀል" ብለን ማሰብ የለብንም። እኛ ኢትዮጵያውያኖች ለአንድ ነገር ጓጊዎች፣ ችኩሎች፣ ሰልቺዎች ከሆንን ውለን አድረናል። ሁላችንም የተለያየ ሀሳብ አለን፣ ተመሣሣይም አለን።

እያንዳንዳችን እንደመሰለን፣ እንደተመቸን፣ እንደቸገረን የተለያየ ድርጅት ማቋቋም ተለምዷችን ሆኗል። መማሩ አይደለም ዋናው ቁም ነገሩ፣ በተግባር ማዋሉ ነው። ለሃገራችን ህዝብ ማለትም 90% ለሆነው ገበሬ ወደኋላ ላለነው ሰዎች የሚያስፈልገን የተቀነባበረ ፍልስፍና ሣይሆን በአሁኑ ሰዓት የሚያስፈልገው ነፃ የሆነ ገበያ፣ ነፃ የሆነ ትምህርትና፤ የጤና አጠባበቅ ትምህርትን፤ ነፃ የሆነ ሥራን ብቻ ነው።

አንድ ሰው በትክክል የአንተን ሃሳብ የሚቀበልህ ከተመገበ በኋላ ነው። በአረረ አንጀቱ በተራበ ሆዱ በደነዘዘ አዕምሮ ላይ የተቀነባበረ የፖለቲካ ትምህርት ማስተማር ሰብስቦ መጮህ አይዋጥለትም። በድንጋይ ላይ ውሃ መጨመር ነው።

ጎበዝ እስኪ ከራሳችን እንጀምር፣ ለራሳችን ሆነናልን? ወይስ ከመጥፎ ነገሮች ተቆጥበናል? ከራሳችን የተረፈ የተቸገረ ዘመድን ረድተናልን? ከዚያስ ለሃገራችን ምንድን ሃሳብን አቅርበናል? ምንድን ሰርተናል? የሰራነው ሥራ ለህዝቡ ይዋጥለታልን? በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አለንን? የህዝቡን ችግር እናውቃለን? ስለሃገራችን አጠቃላይ ሁኔታዎች እናውቃለን?

የሚገርመው ነገር ከእኛ ይልቅ፣ የውጭ ዜጎች ስለሃገራችን አጠቃላይ ሁኔታዎችን በቃልም ሆነ በፅሁፍ ለእኛ ያስረዳሉ፤ በካርታም አስቀምጠውልናል።

እኛ ግን ከጥቂት ሰዎች በስተቀር 95% አናውቅም። ለምን? ሥልጣኔ ሃገራችን ከብዙ ዓመት በፊት ነበር አሁን እንዴት እየከሰመ መጣ? በዚያን ወቅት የነበሩት ትውልዶች የተማሩ ነበር ማለት ነው? ወይንስ እንዴት?

**በአሁኑ ዘመን የፖለቲካ ድርጅትና የሃይማኖት ድርጅት በዛ፤ ለምን ?**

የማይሆን ነገር አይሆንም። ለእኛ የፖለቲካ ድርጅት ብዛትና የሃይማኖት ድርጅት ተከታዮች ብዛት አስፈላጊውን ግብ አይመታልንም። ሃይማኖት ስለቀየርን የተለየ ፅድቅ አናገኝም፣ ድርጅት ስላበዛን ሃገርን አልረዳንም፣ እድገት አናገኝም።

አንድ ጓደኛዬ ትዝ አለኝ በቀን 15 ሴቶችን የሚያሳድድ ሁልጊዜ ሳየው ታዲያ ደስተኛ አይደለም። አንድ ቀን ሃሳቡን አነሳሁለትና ሱስነት ነው፤ ስንወያይ እንደሲጋራ ሱስ ነው አለኝ። እኔም ሰማህ ወንድም የፈሪ በትሩ እስር ነው ይባላልና አንዱን ብትይዝ ከበሽታህ ትድናለህ ያለበለዚያ መጨረሻህ አያምርም አልኩት። በመጨረሻም የታወቀ የሃይማኖት ተከታይ ሆኖ ጥፋቱን ያስተምራል፣ ይመክራል። እግዚአብሄ በሙለሙኑ ከበሽታው ድኖ ከዚህ ደርሷል። ይህን እንደምሳሌነት አቀረብኩት እንጂ ብዙ ነው ነገሩ፤ ሳያደምጡ መመለስ፤ የተናገሩትን መደጋገም፣ ያላዩትን መዋሸት የብዙዎቻችን ተለምዶ ሆኗል። ያልሰራነውን ሰራን፣ ያላገኘነውን አገኘን፣ የማናውቀውን ከኔ በላይ አዋቂ ላሳር ነው

የምንል ብዙዎቻችን ነን። ውሸትን መደለያ (ማታለያ)፣ ስርቆትን መከታ፣ ጥላቻን መመሪያ ማድረግ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤ ምክንያቱም በሰራው ሥራ በእግዚአብሄር ቤት እኩል ያገኛል። ይህንም ባሳለፍናቸው ጊዜያቶች ሁላችንም ያገኘነው ልምድ ነው።

ሌላው ደግሞ የመማር የማወቅ ትርጉሙ የጠፋብን እኛ በተለይም አፍሪካውያን ነን። ከኢትዮጵያውን ደግሞ በ50% እንደኔ አእምሮ ከሆነ የማወቅ፣ የመማር፣ ትርጉሙ መጥፎውንና ጥሩውን ለይቶ የሚያይ፤ የተማረውን ጥሩ ነገሮች በተግባር ማስተማር፣ ማሳወቅ ሰዎች መጥፎ ነገሮችን እንዳይከተሉ በትክክል ማስረዳት ነው።

ግን ሆኖ ያገኘሁት እጅግ በጣም የሚያስገርም ነው። ርህራሄ የሌላቸው ጨካኞች ሰዎችን እንደ ዕቃ የሚቆጥሩ፣ የማያከብሩ ለሰው ልጆች ህይወት ቅንጣት ታክል የማያዝኑ ከዚያም አልፎ ተርፎ እራሳቸውን ለማጥፋት የሚጥሩ ሰዎች ሆነው አግኝቻቸዋለሁኝ።

ምናልባት እናንተ ሣታውቁት ቀርታችሁ አይደለም። ነገር ግን አንዳንድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የተከተሉትን መጥፎ ሱስ እንዲያቆሙ የሚረዳ ሃሣብ ይሆናል ብዬ ነው ይህችን ጫር ጫር ያደረኩትኝ።

የአንዱን ወንድሜን አደገኛ ሱስ ልግለፅላችሁ፣ እዚህ ሃገር ከኖረ 12 ዓመት አሳልፏል። ኑሮው ግን ዕድገት ሳይሆን አይገኝ ሁኔታ ላይ እንዳለ ልገልፅላችሁ ነው። (1ኛ) የ21 ዓመት የሲጋራ ሱስ፣ (2ኛ) የ7 ዓመት የመጠጥ ሱስ፣ (3ኛ) የቡና ሱስ፤ እንዲሁም የሴት ለከፋ ሱስ ያለበት ሰው በመሆኑ የወደፊት ኑሮው ሞትን ከቆየ ደግሞ የተንዛዛ ዕብደትን ነው የሚያስከትለው። ከዚህ ሁሉ ነገር አስቀድሞ መጠንቀቅ ይኖርበታል ያለበለዚያ ራሱን ጎዳ እንጂ ማንንም አይጎዳም።

ሌላው ደግሞ ራስን የሚጎዳ ነገር በምትኖርበት ቦታ የዕዳት ጉድለት የሚያስከትለው ጠንቅ ነው። ያዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ መጥቶ የሚያደርገው በራሱ ላይ ችግር መጨረሻ ዕብደትን እንጂ ሌላ አያጋጥመውም፤ እንዲሁም አንዷ እህቴ አንድ ቀን ወደ ሰፈራቸው ጎራ ብዬ ነበር። ዘመድ ለመጠየቅም። እንደአጋጣሚ ጭቅጭቅ ተነስቶ ደረስኩና ምንድነው ችግሩ ስላቸው "አንቺ አንተ ለምን አታጻዳውም ይባባላሉ። ያጨሱትን ሲጃራ ለምን አታፀዳውም ይባባላሉ። መቼም ቤቱ በሲጋራ ቁርጥራጭ የሞላና አሳማ የገባበት ባህር ይመስላል። ግማሹ ሲያጨስ፤ ግማሹ ይስላል፣ በሶስት በኩል መስኮት ተከፍቶም የሲጋራው ጭስ ግን አይን ይቆጠቁጣል። የብስጭቱ መድሀኒት፣ የደስታው ምልክት ደግሞ የቤቱ መጋየት ከሆነ ማህይም ሆነ የተማረ ምንድነው ልዩነቱ? እንደኔ እንደኔ የፈለጋችሁትን በሉ እንጂ እንደዚህ ከሆነ ያለመማሩን እመርጣለሁኝ። ችግር ያለባችሁ ወደሚመለከተው ሀኪም ሂዱና ችግራችሁን ብታስረዱ መፍትሄ ታገኛላችሁ። ያለበለዚያ በህይወት እያላችሁ የምትጎዱ እናንተው ናችሁ።

ሌላው እግዚአብሄር የሚረዳን ሃሳባችን የሚሳካው ልባችን ንፁህ አድርገን አእምሮአችንን አስተካክለን ስንፋቀር፣ ስንረዳዳና፣ ስንተዛዘን ነው። የምንጀምረውም በአጠቃላይ ስብሰባ ሳይሆን ከቤታችን ነው። ስንመካከር ከመጥፎ ነገሮች ተቆጥበን ለሌሎች ጎረቤቶቻችን አርአያ ስንሆንና ሥራን ሳንንቅ በመሥራት፤ የተቻለንን ወገንን፣ ቤተሰብን ስንረዳና ስንጠቅም ነው። ያለበለዚያ ለሃገር፣ ለወገን መቆርቆር አያስፈልገንም፤ ለራሳችን ካልሆንን።

መጀመሪያ እራስህን አስተካክል። አለበለዚያ አንተ አንዱ የሃገር በሽታ ነህ ማለት ነው።

*ዓይን ምስክር (የብዕር ስም) በሜሪላንድ የሲልቨር ስፕሪንግ ናቸው።*


## ማስታወቂያ

የላንዳፍታን መጽሄት በምትኖሩበት አካባቢ ለማከፋፈል የምትፈልጉ በአድራሻችን ደውሉልን።

ለአከፋፋዮች ጥሩ ኮሚሽን እንከፍላለን። በዚያውም በአገራችን ቋንቋ ለሚጻፍ መጽሄት ዕድገት አስተዋጽዖ እናደርጋለን። አድራሻችን

**LANDAFTA**
**P.O.Box 49301**
**Atlanta, GA 30359**
**ስልክ (404) 728-9122**

አዳም ሔዋን

# ቀበጥ ሙሽራ . . . ከወደ ፈረንጅ አገር

ከአብዬ (ከአዲስ አበባ)

ይህ ፈጠራ አይደለም። የሆነ የተደረገ ነገር ነው። ፀሐይ የሞቀው ሰው ያየው አገር ያወራቸው እውነተኛ ታሪኮች ናቸው። የታሪኩ ባለቤቶች በሕይወት አሉ። እኛም ምስክሮቹ ቆመን እንሄዳለን። እግር የጣለው ይሁን በአጋጣሚ ሁኔታውን የተመለከቱ ብዙ ታዛቢዎች መቁጠር ይቻላል። በነገሩ ያገባናል ያሉ ባለጉዳዮችም የሚያዋጣቸውን የመሰላቸውን እያደረጉ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው። . . . አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ ከፈረንጆቹ ዘንድ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት ለጉብኝትም ይሁን ለሥራ ሲመለሱ የተለያየ ጠረን፣ የተለያየ ልማድ ይዘው ይመጣሉ። የአገር ቤቱን ኑሮ፣ ወግና ባሕሉን ጨርሶ የረሱ ይኖራሉ። ከአውሮፕላን ከወረዱበት ጊዜ ጀምሮ ልክ እንደኖሩበት የፈረንጅ አገር መሆን የሚሞካከራቸው አይጠፉም። አንዳንዶቹ ደግሞ ድህነት ባጎሳቆላቸው ዘመዶቻቸው ላይ እንደመኩራት እንደመዘባነን የሚያደርጋቸውም አይታጡም። እግራቸው የአገራቸውን አፈር ሲረግጥ በናፍቆትና በሰቀቀን በተመሰቃቀለ ስሜት የሚያደርጉትን የሚያጡ እንዳሉ ሁሉ እንኳን የተወለዱባትና ያደጉባት አገራቸው ቀርቶ ስለዚህች አገር ሰምተው የማያውቁ የሚመስሉም አሉ። አንዳንዶቹም በምዕራቡ ዓለም በለመዱት መጠን እዚህም ማድረግ ይሞክራቸውና ትዝብትና ግምት ላይ ይወድቃሉ።

. . . አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ። ለአሥር ዓመታት ገደማ ጀርመን አገር ትኖር የነበረች ኮረዳ ትመጣለች ተብሎ ወዳጅ፣ ዘመድ አዝማድ ሽር ጉድ ይላል። በመምጫዋ ዕለት በአውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው ተቀበሏት። ወይዘሪት ኮረዳ ደልደል ያለች ሙሉ ሰው "ሴትዮ" ሆናለች። የመጣው ሁሉ እገላብጦ እየሳማት "አላገባሽም ወይ? ልጅ አልወለድሽም ወይ? ትልቅ ሰው ሆንሽ አይደል" እያለ ያታክታታል። እርሷ ደግሞ የመጣውን ሁሉ መሳሙ፣ ለሁሉ መልስ መስጠቱ ሰልችቷታል። ደብሯታል። እንደብሽቀትም አድርጓታል። ሲጋራዋን አውጥታ ለኮሰችና ማግ ማግ፣ ቡልል ቡልል አደረገችው። ፈረንጅ አገር ማንም ሥራዬ ብሎ ልብ የማይለው ሲጋራዋ እዚህ ግን የጉድ ጉድ አሰኛት። እነ እታባ፣ እነ እትዬ፣ እነ እቴሜቴ፣ እነ አክስት፣ እነ አጎት ፊት፣ አባት፣ እናት ባሉበት እነ ወንድም ጋሼ፣ እነ ወንድም እሽት ፊት ሲጋራ ማጨስዋ አይን የበላች ዓይን አውጣ አድርጎ አስቆጠራት። እርሷ ግን ደንታም አልሰጣት።እዚያ ያለው ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጅና የሚያውቋትሁሉ ከፈረንጅ አገር የሚመጣ ሁሉ ከተለየ የምቾትና የድሎት ዓለም ዕውቀት በዕውቀት ሆኖ፣ ወርቅ ብር ጭኖ፣ ሻንጣ ሙሉ ረብጣ ዶላር ተሸክሞ የሚመጣ የሞላው የተረፈው አድርጎ ስለሚቆጥር እጅ እጅ ማየቱ አይቀርም። ዋና ዋና ዘመድ አዝማዱ ብቻ ሳይሆን የቋጠሮ ቋጠሮው ሁሉ ምናምን ይከጅላል። ለራሱ ችግር ጠብ የሚልለትን ያስባል። የጥንት ዝምድናውን ወዳጅነቱን ምናልባትም የዋለለትን ውለታ ያሰላስላል። የምትወረወርለት ውራጅ የምትሰጠው ጉርሻ ብትኖር ይቀላውጣል።

ከውጭ የሚመጡት ደግሞ እንደደረሱ የሚሆኑትና የሚያደርጉት እንደባሕርያቸው፣ እንደኖሩበት አገር ባህልና ልማድ ይለያያል። . . . አንዳንዶቹ ታስረው የከረሙ ይመስል ገና ከመድረሳቸው እግራቸው ሰላሳ ቦታ ይረግጣል። አንዳንዶቹ ገና ከአይሮፕላን ማረፊያ እልፍ ሲሉ ሽታውና ግማቱ አፍንጫቸውን ሰንትሮ ለእንፋሉዌንዛ ይዳርጋቸዋል። አንዳንዱ ደግሞ የሚያየው ድህነት፣ ጉስቁልና፣ የዘመዶቹና የሚያውቃቸው ሰዎች ሁሉ ከሳት፣ ጥቁረት፣ በየመንገዱ ላይ የሚያየው ጭቅቅትና ዲሪቶ፣ ቡትቶ የተጀቦነው የለማኝ መዓት፣ ስለ ሀገሩ ድህነትና ችግር ይገምተውና ያስበው ከነበረው፣ ብዙ ጊዜ እጥፍ ይሆንበትና ስቅቅ፣ ሽምቅቅ ብሎ በሚያርፍበት ጓዳ ይወሸቃል። ሰው ሁሉ ጉስቁልቁል ብሎ ጥቁር አፈር የመሰለ፣ ከተማዋ ደግሞ የተወረረች የምትመስል ትሆንበትና ከቤትም መውጣት የሚያስፈራው አለ።

አንዳንዶቹ ደግሞ ገና የደረሱ ዕለት አንድም አዝማሪ ቤት እንዳይቀራችሁ የተባሉ ይመስል የአዲስ አበባን አዝማሪ ቤት ሁሉ ሲያስሱና አሸሼ–ገዳሜ ሲሉ የሚታዩ አሉ። ወደ ሒልተን ወደ ግዮን ብቅ ብለው ለየት ብሎ ለመታየት፣ ከፈረንጅ አገር ገና መድረሳቸውን ለማሳየት የሚራቀቁም ሞልተዋል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ሴት ከሌለበት አገር የመጡ ይመስል አጎጠጎጤዎቹ መሐል ከቆንጆዎቹ ሰፈር ዘፍ ይላሉ። ሚስት የምትሆን ፍለጋ ላይ ታች የሚሉ፤ ፈረንጅ አገር ያፈሩትን ጥሪት ስራ ላይ ሊያውሉ የሚችሉበትን የሥራ መስክ የሚያጠያይቁም በዚያው ልክ ናቸው። የሚስት ፈላጊው ባሕርይና የሚያደርጋቸው ድርጊቶች እንደሰው ባሕርይና ልማድ የተለያየ ነው። አንዳንዱ በየአዝማሪ ቤቱ፣ በየዳንስ ቤቱ አይኑ የሚገቡትን ያነጣጥራል። በሒልተን፣ በሶደሬ፣ በግዮን፣ በሸበሌና በታወቁሆቴሎች አካባቢ ያንዣብባል። አንዳንዱ ለዘመድ አዝማድ ሁሉ ካልዳራችሁኝ ይላል። በቤተሰብ ስብሰባ በዘመድ ሸንጎ ላይ አቤቱታው ይነገርለታል።

ተሳክቶለት ለቁምነገር የሚበቃ ይኖራል። ያልሆነለት ያልያዘለትም ሊኖር ይችላል። በቅብጠት የተደመደመ፣ የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበ ዱብ ዕዳ የተፈጠረበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል።

. . . ከወራት በፊት እንዲህ ሆነ። አንዱ አውሮፓ ምድር ይኖር የነበረ ወደ ሀገር ቤት ይመጣል። ሲነባበትም ከአንዲቷ ኮረዳ ጋር ወጣ ገባ ይላል። ይህቺን ኮረዳ ልቡ ፈቅዶ ኖሮ ሊያገባት ይወስናል። እርሷም ትስማማለች። የሠርጋቸው ቀን ይቆረጥና ድል ያለ ድግስ ይደገሳል። . . . በዕለቱ ዘመድ አዝማድ፣ ወዳጅ ጓደኛ በተገኘበት ሙሽራና ሙሽሪት በቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት በተክሊል የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸው ተፈፀመ። አንድ ልብስ ለብሰው በራሳቸው ዘውድ መሰል ነገር ደፍተው እስከሞት ድረስ ላይለያዩ ቃል ተገባቡ። ጋብቻቸውን ከፈፀሙ በኋላ ትንሽ ሰነባብተው ወደ አውሮፓ ይዟት ይበራል።

እዚያ መኖር ሲጀምሩ ሳይግባቡ ይቀራሉ። አጅሬ አቶ ባል የእርሷን ነገር አንድ ማሰሪያ ሳያበጅ ሲበር ወደ ሀገር ቤት ይመጣና የመጀመሪያይቱን ሚስቱን የፈታኋት ስለሆነ ሚስት የምትሆን የቤት ልጅ አፋልጉኝ ይላል። ከተሸከመው ረብጣ ዶላር እየመዠረጠ ፍለጋውን ያጧጡፋል። ይቀናውና ትገኝለታለች። ሠርግ ይደገስና ዳግም ተሞሽሮ ለዚችኛው ሚስቱ ደግሞ እስከሞት ድረስ ቃል ሊገባ ሙሽሪትን ይዞ በአጃቢዎች ታጅቦ ቤተክርስቲያን ይደርሳል። ደግሞ ሌላ የተክሊል ሥነሥርዓት ሊፈፅም!! . . . አጋጣሚ ሆኖ የመጀመሪያዋ ሚስቱ የሩቅ ዘመዶች በሠርጉ ላይ ነበሩ። የተመለከቱት ሙሽራ የሚያውቁት ሆነባቸው። ነገሩ ከነከናቸው። አጠያይቀው ሲያጣሩም የልጃቸው ባል አማቻቸው ነው። ጎረምሳ ጎረምሳዎቹ ካልገደልን ብለው ለገላጋይ አስቸገሩ። "ሙሽራ አይደበደብም ደግሞም ቤተክርስቲያን ደጃፍ ጠብ አይሆንም" ተብለው በሰው ብርታት አቶ ሙሽራ ከዱላ ተረፈ። የመጀመሪያ ሚስቱን በተክሊል ያገባው በዚሁ ቤተክርስቲያን ስለነበር ለሠርግ የተጠራው እድምተኛ ሁሉ ጉድ አለ። አቶ ሙሽራ አይንህ ላፈር ተባለ።

ነገሩን የሰሙት የመጀመሪያ ሚስቱ አባት በማግስቱ በአስራ አምስት ሳንቲም ከላሰር ፋይል ከፍተው ፍ/ቤት ገተሩት። በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀሙ ይቀጣልኝ አሉ። እርሱ ፈትቻለሁ እያለ ቢወተውትም የተፋቱበትን ብጣሽ ወረቀት ግን ማቅረብ አልቻለም። በጋብቻ ላይ ጋብቻ ደግሞ ወንጀል ነው። በሕግ የሚያስቀጣ ብርቱ ወንጀል! . . . የቤተሰብ ሽማግሌ በመካከል ገብቶ ካልገላገለው እስከ ሶስት ዓመት ለሚደርስ ጽኑ እስራት ጠጉሩን ተላጭቶ እጁን ተጠፍሮ ከርቸሌ ይወርዳታል። የፍ/ቤቱ ችሎት ክርክር ገና ያላለቀ ስለሆነ የዚህ ቀበጥ ሙሽራ መጨረሻ አልታወቀም። ከፈረንጅ አገር የሚመጡ ኢትዮጵያውያኖችን እያጠመዱ "ሚስት" የምትሆን ኮረዳ የሚያገናኙ ደላሎች አሉ ይባላል። ወደ ሒልተን፣ ወደ ግዮን፣ ወደ ሸበሌ አካባቢ እየተንጎራደዱ እንግዳም መስለው ከፈረንጅ አገር የመጣ የሚመስላቸውን፣ "ሚስት" ፈላጊ ሊሆን የሚችለውን እንደሚያጠምዱ ያጠምዱታል አሉ። እነርሱ በሚገባ ያውቋቸዋል። አንዳንዶቹንም ለመታየት ሲሉ በሚያደርጉት over act ይለዩአቸዋል። በሚታወቁ የከተማው አዝማሪ ቤቶች ውስጥ አገር ደህና ብለው አሸሼ-ገዳሜ ሲመቱ ያገኟቸዋል።

አንዳንዱ የግድ እነዚህን ደላሎች ማግኘት ይኖርበታል። ብዙ ዓመት ውጭ ቆይቶ ሲመጣ ዋና ዋና ዘመዱ አልቆ ሊደርስ ይችላል። ወይም ደግሞ ያለውም ዘመድ አዝማድ ከከተማ ውጪ ሆኖ ሊቸገር ይችላል። አብሮ አደግ ጓደኛ የልብን የሚያጫውቱት ወዳጅ ገሚሱ እንደጨው ዘር ተበትኖ፣ ገሚሱ ኑሮ እንደማይሆን አድርጎት ሰው ማጣት ይኖራል።

. . . የድሮ ዝርዝርና አድራሻ ደግሞ የሚጠቅም አይሆንም። የድሮ girl friend ዛሬ የኮራች የደራች የቤት እመቤት ሆናለች። በያኔው ዘመን ዓይን የሚገቡት አንድም አግብተዋል አለያም አርጅተዋል። . . . ሽንጧ የነብር ጅራት ስትባል የነበረችቱ - ዛሬ ደንደሮ ቢጤ ሆና ሊሆን ይችላል። አንገተ መቃዋ - ኩልኩልት አውጥታ ሆዷ ገፍቶ ዘርፋጣ ሆና ሊሆን ይችላል። ቦንቦሊኖ የነበረችው - ኮሣሣ ባልቴት ወጥቷት ይሆን ይሆናል። ደም ግባትና ውበት አብሮ አይሰነብትም። ፀጉሯ ወርዶ ወርዶ የተዘፈነላት ውብ - ዛሬ ሽበት የወረራት ማድያት የጠባበሳት የሚቲዎች እናት ሁና ሊሆን ይችላል።

. . . ያላገቡትም ቢሆኑ ወይ ባል አጥተው ወይ ሲመርጡ ኖረው በተራቸው ምራጭ ሆነው ሌላ የሕይወት መንገድ የጀመሩ ናቸው። ዕድሜ እንዳይሆን እንዳይሆን አድርጓት ታይታ የማትጠገብ የነበረችው እህል ከፊቷ የማይበላ አስጠሊታ ሆና ሊሆን ይችላል። የድሮው ሊስት የያንጊዜው ዝርዝር አይሠራም። . . . አሁን ደግሞ ደረስኩ ደረስኩ የሚሉቱ ለቁምነገር አይሆኑም። አይነግቡዎቹ የዛሬ ቆንጆዎች ፋፋ በልተው ያደጉ ቡፍ ያሉ ልጆች ናቸው። ገና መዝለል፣ መቦረቅ፣ መሳቅ እንጂ ሌላ የሕይወት ጣጣ የማያውቁ። ለሕይወት ፈተና ያልተዘጋጁ ብርር ብርር የሚሉ የመስቀል ወፎች። ከእነዚህ ጋር ብርር ብርር ለማለት የሚችለው ደግሞ ከእነርሱው ጋር ሸቅብ ቁልቁል ለመብረር አቅሙም ጊዜውም ያለው ጭልፊቱ እንጂ ከፈረንጆቹ አገር ለመጣው ሚስት ፈላጊ አይቻለውም። በአስተሳሰብ በvalue ሰፊ ልዩነት ያለው ሌላ ትውልድ . . . ደግሞም የሌላ አዲስ ትውልድ ድርሻ! . . . እናም የኪሱን አቅም አይተው እንደሚሆን እንደሚሆን የሚያከናውኑትን ደላሎች ማግኘት የግድ ይሆንበታል። የተሳካለት ሊኖር ይችል ይሆናል። ያልሆነለት ገንዘቡንም ከስሮ የተዋረደም አይጠፋም። የደላላ ነገር አያስተማምንም - እንኳን ሚስት ጥሩ ጎረቤት የማትሆነዋን ሞላጫ አይን አውጣ እንከን የማይወጣላት የሴት አውራ አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል።. . . በቅርቡ አንዱ እንዲህ ሆነ። ከረጅም ጊዜ በኋላ ወደ ሀገር ቤት መጥቶ ሰነባብቷል። ወዲያም ወዲህም ቢል እጁ የሚገባ

ቆንጆ ይጠፋል። ቢያየው ቢያየው ሴቱ ሁሉ ባለ ቀለበት ነው። በኋላ ቢቸግረው በእነዚሁ አገናኝ አማካይነት እንዷት ቆንጆ ይተዋወቃል። ስለ ልጅቱ ጥሩነትና የቤት ልጅነት ብዙ ብዙ ተነገረው። እርሱም የበኩሉን ግምገማና ምዘና ለማድረግ ተዘጋጀ። ብዙ መቀራረብ አብሮ መውጣት፣ አብሮ መግባት ተጀመረ። በእርግጥም ጥሩ ልጅ ናት። በዚህ ላይ ቆንጆ ናት። በአለባበሷ፣ አነጋገሯ፣ አስተሳሰቧ ዘመናዊ ናት። ይህ ኀደለሽ አትባልም። በቀጠሮ ትገኛለች። ቃሏን ታከብራለች። ጨዋታ ታውቃለች። በሌላ በሌላውም ተስማምታዋለች። ይህ እውነተኛ ባሕርይዋ መሆኑን በብዙ መንገድ ለራሱ አረጋገጠ። በወዳጅ በዘመድ መካከልም በግብዣና በጥሪ አስመስሎ አስገመገማት። ሁሉም ይህንኑ አረጋገጡለት። የራሱ ሊያደርጋት ወሰነ። ሊያገባት እንደሚፈልግ ሃሳብ አቀረበላት። "ከአገር ልታወጣኝ" ብላ ቀለደችበት። "የሰው አገር ሰው አላገባም" ብላ አሾፈችበት። ነገር ነገሯ ከልቡም መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር።

. . . ልጅት የምትወደው እጮኛዋ ወደ ባሕር ማዶ የተሻገረባት ነበረች። ተከትላውም ለመሄድ ብዙ ጥረት አደረገች። አልተሳካላትም። አቶ እጮኛም ፈረንጅ አገር እንደደረሰ ሊወስዳት ብዙ ሞከሯል። አልተሳካም። በኤምባሲ ውስጥ ቪዛ ያስመታሉ ለሚባሉ የውስጥ ሰዎች ሁሉ ገንዘብ ተከፈለ። አልተቻለም። forged ይሠራሉ በሚባሉ ሰዎች ተሞከረ። አልሆነም። ከዚህ ሰው ጋር ሲያስተዋውቋትም እንዲህ በአጭር ጊዜ ግጥምጥም ይላል ብላ ባትገምትም የጋብቻ ጥያቄ ሊነሣ እንደሚችል ገምታለች። ሰውዬዋ እዚህ በሚቆይበት አጭር ጊዜ ጠባይ አሳምሮ መገኘት እንደሚገባት አውቃለች።

ገንዘቡን ሳይሆን እሱነቱን የወደደች መሰለች። የምታስብለት ሆና ለመታየት ትንሽዬ ድራማ ሰራች። እንደምትስማማው ሆና አከራረመችው። ፈረንጅ አገር የሚኖሩ ወንዶች እዚያ ያሉትን አበሻ ሴቶች ብዙም ለጋብቻ እንደማይመርጡ ልቅም አድርጋ ሰምታለች። ፈረንጅ አገር የከረረሙ አበሻ ሴቶች ለትዳር የማይመቹ ፈጣጢዎች ናቸው ሲባል ጆሮዋ ሰምቶ ያውቃል።

ጨዋነትና እርጋታ ዘመናዊ አስተሳሰብና አለባበስ የመጀመሪያ criteria መሆኑ ገብቷታል። ለገንዘብ አለመንሰፍሰፍና ትንሽ ቆጠብ ማለት፣ ቀጠሮ ማክበር በተናገሩት መገኘት የሚያስመርጥ መሆኑን ጠንቅቃ ተረድታለች። ከዚህ ሰው ጋር በቆየችበት ጊዜም በልቧ ይህን ይዛ በእነዚህ መመሪያ ነበር ራሷን የገዛችው። እንደገመተችውም ሆነ። ትልቁ አሣ ከመረብ ገባ።

ይህ ሰው የጋብቻ ጥያቄ ሲያነሳባት ያ ስንት የደከመችለት ቪዛ እየኳተነ ወደ እርሷ ሲመጣ ታያት። አልተግደረደረችም። ልታገባው እንደምትፈቅድ አረጋገጠችለት። ከጥቂት ቀናት በኋላ አቶ ሰውዬ ወደ ፈረንጅ አገሩ መመለስ ነበረበት። ተመልሶ መጥቶ ሒልተን ሆቴል ተደግሶ እንደሚጋቡ ወይም እርሱ ካለበት አገር እንደሚወስዳት ቃል ገብቶላት ወደመጣበት በረረ። ልጅት እንባ በእንባ ሆና ሸኘችው። አቶ ሰውዬ ካለበት ሆኖ ጠዋት ማታ ስልክ ይመታል። የናፍቆት ሰቀቀን የመለያየት ሰቀቀን ክፉኛ የጎዳቸው ፍቅረኛሞች መሰሉ።

. . . ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ልጅት ወደ ፈረንጅ አገር የምትበር መሆኗን ለወዳጅ ዘመድ በይፋ አሳወቀች። የልቧን በልቧ ይዛ ጓዟን ጠቀለለች። ዘመድ አዝማድ ተሰናብታ በአውሮፕላን ወደ ፈረንጅ አገር ነጎደች። አስቀድማ ግን ዝርዝር ዕቅዷን ለእጮኛዋ ጽፋለታለች።

በተለያዩ የአይሮፕላን ማረፊያዎች ሁለት ሰዎች የእርሷን መምጣት በናፍቆት ይጠባበቃሉ። አቶ እጮኛ ሊወስዳት ሞክሮ ያልተሳካለትን እጮኛውን በናፍቆት ሰቀቀን በአንድ የአይሮፕላን ማረፊያ ይጠብቃል። አቶ ሰውዬ ደግሞ የወደፊት ሚስቱን የልጆቹ እናት የምትሆነውን ቆንጆ በሌላው የአውሮፕላን ማረፊያ ይጠብቃል። አጅሪት ግን የበረረችው ወደ ቀድሞው እጮኛዋ ነበር። እጁን ዘርግቶ በእቅፉ የተቀበላት አቶ እጮኛ ነበር። አንደኛው ልቡ በደስታ ፈነደቀች። ሌላኛው ባዶ እጁን አጨብጭቦ በሐፍረት ተሸማቀቀ።

ከእንዲህ የሚሸውዱ ብቻም ሳይሆኑ የተሸወዱም ደግሞ አይታጡም። ይሆናል ብለው የገቡበት ትዳር እንደ ወህኒ ቤት መውጫ የሌለው የሆነባቸው አይጠፉም።. . . "የባል ያለህ" የምትል አንዷት ቆንጆ በአውሮፓ ብዙ ዓመታት የኖረ ሰው ትተዋወቃለች። በተዋወቀችው በአጭር ጊዜያት ልታገባው ትወስናለች። ብዙም ከማታውቂው ሰው ጋር እንዷት ይሆናል ተብላ ተመከረች። አልሰማችም። ትዳርን የሚያክል ነገር በሩጫና በጥድፊያ አይሆንምና የሰውየው ማንነት ይጠና ተባለች። የሚሰማ ጆሮ አልነበራትም። . . . Babe ነው። darling ነው። ማቀማጠል፣ ማሞላቀቅ ነው።

. . . ለማሰብም ፋታ ነሣት። በኮረዳነቷ ዘመን ያላየችውን ብርቅዬነትና ሞልቃቃነት አሁን ገና ያገኘች መሰላት። ነሆለለች። ለጓደኛ ምክርና ተግሳፅ ቦታ አጣች። ውላ አድራ ትንሽ ሰነባብታ የሰውዬውን ማንነትና ባሕርይ ለማጥናት አላሰኛትም። በቃ ወሰነች። ገባችበት።ሠርጉ ቀን ተወሰነና ጓደኛ ሁሉ ለሚዜነት እንዲዘጋጅ ለአጃቢነት እንዲሰናዳ አደረገች። ቅልጥ ያለ ሠርግ በግዮን ሆቴል ተደገሰና ተሞሸረች። ሙሽራዬ ተባለላት። የሚቀናባትም ሆነች። የልቧ ደረሰ ደስ አላት። ወይዘሪት ቀርቶ ወይዘሮ ሆነች። ተገላገለች። የት ባገኙሁት ያለችውን "ባል" በእጇ አስገባች። ለዚያውም የብረት መዝጊያ የሚሆን። በፈረንጅ አገር የሚኖር፣ ፋብሪካ ያለው፣ ብር የሞላው! ከሠርጉ ጥቂት ቀናት በኋላ ወደ አውሮፓ ለመብረር መሰናዶ ተጀመረ። የስጦታና የግብዣ ዓይነት ተደረደረ። እርሷም አውሮፓ ስትደርስ ደብዳቤ የምትጽፍላቸው ወዳጆቿን አድራሻ ሰበሰበች። Invitation የምትልክላቸውን ጓደኞቿን ስም መዘገበች። አውሮፓ በረረች።

ስንብትና ሽኝቱ ተሟሙቆ ሰነበተና ከአቶ ባል ጋር ወደ አውሮፓ እንደደረሰች አቶ ባልን ጨርሶ የማታውቀው ሌላ ሰው ሆኖ አገኘችው። ያልነገራት ብዙ ጉድ ያለው ታሪክ ብዙ መሆኑን አወቀች። ከልጆቹ እናት ጋር በቅርቡ የተፋታ የአራት ልጆች አባት ነበር። ስለዚህ አንድም ነገር አልነገራትም። ፋብሪካ አለኝ ኩባንያ አለኝ ሲላት የከረመው ሁሉ የፈጠራ ወሬ መሆኑን ደረሰችበት። መሞኘቷ ገባት። እንደመጠየቅም ሲቃጣት Babe Darling ሲላት በከረመበት አንደበቱ Damn Bull sheet ይላት ጀመር። በማታውቀው አገር አይዞሽ ባይ በሌለበት ልታደርገው የምትችለው አልነበራትም። አበሳዋን ቆጠረች። ፓስፖርቷን ቆልፎባት የትም እንዳትሄድ አደረገ። ለነገሩ የምትሄድበትም አልነበራትም። ከቤት መውጣትም ሆነ ከሌሎች ጋር መገናኘት በእርሱ ችሮታና ፈቃድ ብቻ የሚሆን ነገር ሆነ። ያደረገችውን የሆነችውን እንዲጠብቁና እንዲነግሩት የተነገራቸው ልጆቹ ቁም ስቅሏን አሳዩዋት። እንደ ሚስትም እንደ ገረድም እየደረገ፣ ሲሆንለት በፍቅር እያባበለ ሲለውም በጡጫ እያጠዘ ሲቀልድባት ከረመ። ለብዙ ወራት በዚህ ሁኔታ ከኖረች በኋላ እያደር አገሩን ስትለምድና ሁኔታውም ሲብስባት ፈታችው።

ሌላው ደግሞ እንዲህ ሆኗል . . .

ከዓመት በፊት ወደ ሀገር ቤት ብቅ ብሎ በዘመድ ተፈልጋለት እንከን የማይወጣላት ቆንጆ አገባ። በአሜሪካን አገር ብዙ ዓመት የኖረ ሰው ነው አሉ። ሙሽርነቱን በወጉ ሳይጨርስ አፓርታማ ተከራይቶ ሙሽራ ሚስቱን ከፎቅ ላይ ሰቅሎ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ አሜሪካ በረረ። ሙሽሪት አቶ ባል የሚልክላትን ዶክሜንት እየያዘች ቪዛ ልታስመታ አሜሪካን ኤምባሲ ትመላለሳለች። Application Recieved የሚል ማሕተም ፓስፖርቷ ላይ እየመቱ ይመሉሱአታል። ያስፈልጋል የተባለችውን ዶክሜንት ይዛ በሄደች ቁጥር Application received እየተባለች ተቸገረች። ይህቺን ያወቀ እበላ ባይ ወንደ ላጤ ደግሞ ደጅ ይጠናል። አቶ ባል የሚልክላትን ረብጣ ዶላር ተንተርሣ ብቻዋን ተኮራምታ ለምታድር ለዚህች ቆንጆ "Escort" ባል የሚያስፈልጋት መሆኑን አውቋል። ቢሆንለት ቢሳካለት ጥሩ የገቢ ምንጭ ደህና መደጎሚያ እንደምትሆነው ተረድቷል። እንዴት እንደሆነ ምን እንደደረሰለት ባላውቅም ከመልኩ ወዛ ወዛ፣ ከአለባበሱ ፀዳ ፀዳ በማለቱ ሳይሳካለት አይቀርም ያሰኛል። ታዲያ ከየት አመጣው? ሎተሪ አልደረሰው ወይ ውርስ አላገኘ!

ወደ አገር ቤት ከሚመጡት አንዳንዶቹ ሚስት ፈላጊ ቢሆኑም ባል ፈላጊ ሴቶች ጨርሶ የሉም ማለት አይደለም። የሴቶቹ ጎልቶ አይወጣም። እነርሱም ቢሆኑ ብዙ አይደሉም።

. . . አንዲት "ባል" ፈላጊ አምና ወደ አገር ቤት ብቅ ብላ ነበር። ገና ከመድረሷ ተዋከበች። ታስራ የከረመች ይመስል ተሽከረከረች። ሰላሳ ስፍራ ረገጠች። በደረሰችበት ሁሉ ጉራዋን ቸረቸረች። ሁሉን የምታውቅ መስላ ተመፃደቀች። ለትንሽ ቀናት ላወቀችው ሁሉ ስለ claimax ቀባጠረች።ከፈረንጅ አገር የመጣች መሆኗን ለፈለፈች። የሞላላት የተረፋት መስላ ለመታየት በሒልተን ሆቴል ሰውን ሁሉ በግብዣ አምበሻበሸች። በአዝማሪ ቤት ከበር መልስ ከፈለች።

ለአንድ ሰሞን ወዳጅ ዘመድዋ፣ አጃቢዋ በረከተ። በጣም በአጭር ጊዜ የፈላጊዋ ቁጥር በዛ። በቁልምጫ የሚጠራት እበላ ባይ በረከተ። ብዙ ጎረምሣ ተቀባበላት። ያለአንዳች ውጣ ውረድ ለጥብስ አደረሿት። አንዳንዱም ገንዘቧን ለመብላት ሲል ቀረብ ብሎ አያት። እዚህ ግባ የማይሉት ዱርዬ ሁሉ እንዳሻው ገለባት። ሌላውም "እንሞክራት" ብሎ ሞከራት። መቀለጃ እስከትሆን ተሞከረች። ሳታውቀው ራሷን ትዝብት ላይ ጣለች። ለነገሩ ይሉኝታና ትዝብት የምታውቅ ቢጤም አይደለችም።

በመጨረሻም አንድ ኮሣሣ የመንግስት ሠራተኛ በመደበኛነት ይዛ ስታወዛውዘው ሰነበተች። እሱንም አንድ ቀን ብዙ ሰው በተጠራበት በአንድ ግብዣ ላይ ሙሉ ልብስ ለብሰህ አልመጣህም ብላ ክፉኛ ከፍ ዝቅ አድርጋ አዋረደችው። አንዲት አሮጌ ጃኬት ለብሶ ጭሎ መስሎ በዚያ ሁሉ ባለ ሱፍና ባለ ከረባት መካከል ስታየው አፈረችበት። ይሉኝታም ሳይዛት እዚያው ድግሱ ላይ አንቧረቀችበት። ቤተክርስቲያን የገባች ውሻ አደረገችው። አቶ ወዳጅም መግቢያ ቀዳዳ ጠፍቶት ሲርበተበት እንደምታሳድረው አሽከሯ ተንጣጣችበት። እዚያ የነበረው ተጋባዥ ሁሉ እየተጠቃቀሰ ሲስቅባት ደግሞ የባሰውኑ በሸቀች። ሁሉንም ሰው መስደቧ ይሁን ወይም እንደ ወዳጇ ልታሽቆጠቁጥ ፈልጋ ተጋባዡን ሁሉ በግልምጫ ገረመመችው። . . . የፌሲታ ተቆጢታ! የባሰውኑ መሳቂያ መሳለቂያ መጠቃቀሻ ሆነች።

ከዚያ በኋላ እዩኝ እዩኝ ባለችበት ከተማ ተደበቀች መሰል ድምጿን አጥፍታ ከርማ ሹልክ ብላ ሽኝት ሳታበዛ ልጅት ወደ አይና አውጣዎቹ አገር አሜሪካ ነጎደች። አሜሪካ የአይን አውጣ አገር አይደል?

እርስዎስ ወደ ሀገር ቤት ብቅ ብለው ያውቃሉ? ቆይታዎ እንዴት ነበር? ምን ታዘቡ? እርስዎስ ትዝብት የገቡ በምን ይሆን? ብቅ ብለው የማያውቁም ከሆነ እንግዲህ አንድ ቀን ሞልቶልዎት ወደ ሀገር ቤት ብቅ ቢሉ ለሀገር ባህልና ወግ ለትዝብት ግድ የሌለው አይን አውጣ እንግዳ እንዳይባሉ ጠንቀቅ ይበሉ። አነጋገርዎ የደላው ሙቅ ያኝካል እንዳይመስልብዎ እንደመዘባነን፣ እንደመራቀቅ ባያሰኝዎ ደግ ነው፤ "ሚስት" ፈላጊም ከሆኑ ቀበጥ ሙሽራ እንዳይወጣዎ በጥንቃቄ ይራመዱ። የአንዲቱ ሞላጫ መሸጋገሪያ እንዳይሆኑ ወይም ደግሞ የመንደር ጎረምሣ ቀላቢ እንዳይሆኑ ከውሳኔ በፊት ትንሽ ለራስዎ ፋታ ይስጡ። . . . "የሰው የለው ሞኝ፤ ከወንዙ ከቀዩው ከደጁ ሲገኝ ይባል የለ!"

. . . የአብሲኒያ ጮሌ እንዳይከረባብትዎት!

# "አላለልኝ ይሆን?"

## ከትዝታ አለብኝ (L.A)

(ካለፈው የቀጠለ)

ታሪኬን እስካሁን ልብ ብሎ ለተከታተለ ጠባዬን መረዳት የሚችል መሰለኝ። ጠባዬ የሚገባ ቢሆን እንግዲህ በታሪኬ መጀመሪያ ላይ እንደነገርኳችሁ ይህን እንድፅፍ ያነሳሳኝ እህቶቼ ከኔ ልምድ ቢማሩ ብዬ ነውና ጠባዬም ግር ይበላችሁ አይበላችሁ እህ ብላችሁ አዳምጡኝ።

አንድን ድርጊት ስፈፅመው በዚያ ወቅት ማለትም ድርጊቱን በማከናውንበት ወቅት የሚሰጠኝን እርካታ ብቻ በመመልከት ብቻ እንጂ እርቆ በማሰብ ውጤቱ ጎጂ ይሁን አይሁን በማመዛዘን እንዳልሆነ የተረዳሁት ከመሸ በኋላ ነው፤ ዉሎ አድሮ መለስ ብዬ ሳየው ለካ ህይወቴ ሁሉ እንዲህ ነበር። እና አሁንም ሰውዬዬን ተመናቅሬበት እስቀይሜው ከሄደ በኋላ እንደገና ስልክ መደወሌ ከዚሁ የመነጨ ይመስላል እልህ ካልሆነ ማለቴ ነው።

በስልክም ሳነጋግረው ባደረግሁዋቸው ስህተቶቼ የተፀፀትኩ መሆኔን ይቅርታ በመጠየቅ ገልጫለሁ። መልሼ ስደውልለትም "ይቅርታ አድርግልኝና ተመልሰህ ና" ልለው ፈልጌ ይሁን አይሁን አላውቅም አትጠይቁኝ። የማውቀው ነገር ቢኖር አጠገቤ የነበረ ጊዜ ተቅበጠበጥኩ፤ ተመናቀርኩ፤ ጥሎኝ ሲሄድ ጊዜ ተናደድኩ፣ እልህ ገባሁ፣ ይኸው ነው። እሱ ያነሳው ጥያቄ ደግሞ አለ። በርግጥ ለጋብቻ ዝግጁ ነኝ ወይ? የማግባት ውስጣዊ ፍላጎትና ዓላማ አለኝ ወይስ "ቆማ ቀረች፣ ባል አጣች፣ ወንድ ሁሉ ጠላት፣" የሚለውን የአበሻ ወሬ ኩም ለማድረግ? ትዳር መስርቶ ቤተሰብ ይዞ መኖር መፈለግ ጤነኛ የሆነ የሰው ልጅ ዓላማና ፍላጎት ነው። ይህም ፍላጎት በውስጣችን ያለ ተፈጥሮአዊ ስለሆነ ከዚህ ብንሸሽ ችግር ቢኖርብን ነው ማለት ነው? አለ አይደል ያለመብሰል? እና "ሰው ሲያደርገው ለምን ይቅርብኝ ብዬ ነው እንጂ ለጋብቻ ደንታ የለኝም" የሚሉትን ሴቶች አትመኑአቸው፤ ውሸታቸውን ነው። እያንዳንዷ እንዲህ ባይ ሴት በውኗ አትፈፅመው እንጂ በ ኅሊናዋሺ ጋብቻ ፈፅማለች። "ያለ ወንድ መኖር አይቻልም እንዴ?" ሲሉ ትሰማላችሁ ቀጣፊዎች በኋቸው። ወንዱም ቢሆን እልዲሁ ይመስለኛል፣ ስለ ወንዱ ወንድ ቢያወራው ያምራል። እኔ በርግጥ ጋብቻ ፈላጊ ነበርኩ፣ ነኝም ልበል ታዲያ ጓደኞቼ ስላደረጉት አይደለም። ይህንን ወሬኛ አበሻ አፍ ለማስያዝም አይደለም፤ በርግጥ ወሬኛን ማሳፈር ተገቢ ቢሆንም። ታዲያ የጋብቻው ፍላጎቱ ካለኝ ምን ነካኝ? እንግዲህ ለወጣት እህቶቼም ምክር ቢሆን ብዬ ነውና ታሪኬን የጀመርኩበት ይህ ዓላማዬ እንደተበቀልኝ ሆኖ ኑዛዜዬን ልጨርሰው።

ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ ገና የዛን ጊዜ፣ ጥንት ልበለው በወጣትነት ዕድሜዬ አገሬን ጥዬ ወደዚህ ስመጣ በዓላማና በተስፋ ነበር። በፊልም ካየሁትና በየቦታው የሚወራው ሁሉ አሜሪካን የመምጣት ፍላጎቴን አግሎት ነው የመጣሁት ነው። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሊጨረስ ሲል መቼም ማትሪክን አልፎ ዩኒቨርሲቲ የመግባት ዕድሉ እንደቀጭን ክር የመነመነ በመሆኑ እንዳማራጭ ተደርጎ በወቅቱ አሁንም ቢሆን የተያዘው ወደ ውጪ በተለይ አሜሪካን መምጣት ነበር፣ ፋሽንም ነው። ገና አስራአንደኛ ክፍል ሲገባ ቀደም ብሎ ውጭ አገር የሄደ ዘመድና ጓደኛ መፈለግ ይጀመራል። ደብዳቤ መፃፍ ይጀመራል፣ የ I-20 ዘመቻ ይያዛል። እኔም ከዚህ አመለካከት ነፃ ነበርኩ ብላችሁ አትመኑ፤ ያ ነው እንግዲህ መነሻው። እኔ 12ኛን ጨርሼ በዘመድ አየር መንገድ ገባሁና ሆስቴስ ሆንኩ። ዘመድ ስላችሁ ይግባችሁ፣ ቀጠን ያለች ፈገግታ ያላት ወጣት ሴት ዘመዱ ብዙ ነው፤ አለ አይደል? በርግጥ ሆስቴስ የመሆን ፍላጎት ኖሮኝ አልነበረም። ብቻ እዚህ አሜሪካን ለመምጣት ላለኝ ህልሜ አቋራጭ መንገድ ስለሚሰጠኝም ነበር። መቼም ታውቁታላችሁ I-20 ለማግኘት ያለውን ጣጣ። ከዚያም ጥቂት ጊዜ እንደሠራሁ ለውጡ መጣና አገር ተደበላለቀ። ፖለቲካ የሚሉት ነገር አይገባኝም፤ መቼም ገብቶኝ አያውቅም። ለኔ ፊትም ሆነ አሁን ቁጭ በሎ መነታረክ ብቻ ነው የሚመስለኝ፣ ለውጡ ሲመጣ የሚገባኝ ነገር ጃንሆይን ወታደሮች ከሥልጣን አወረዱአቸውና እነሱ ሥልጣን ያዙ፤ ለምን? ጠልቄ የማውቀው ነገር የለም። መነን ትምህርት ቤት እያለሁ ተማሪዎች ሲሰለፉ ለኔ የሚታየኝ ረብሻ ነው። ጥሩ ዕረፍት የሚሰጠኝ ቀን፣ ትምህርት ቤት በረብሻ ሲዘጋ ለመዞር ያመቻል፤ ሲኒማ ቤት መግባት ይቻላል። ይህ ነበር እኔና ጓደኞቼ የሚገባን ነገር። እንግዲህ ሆስቴስ ሆኜ ለውጡ መጣ፤ በወቅቱ ከምናጓጉዛቸው ሰዎች መሀል

"የት እንደምንሄድ አውቀሻል?" አለኝ።
"ለምርመራ መሰለኝ" አልኩት።
"ምርመራሽማ አልቋል" አለና ሳቅ አለ።
"ታድያ ምን ይሆን?" አልኩት።
"አብዮታዊ እርምጃ ልወስድብሽ" አለና አሁንም ሳቅ አለ።
"የሚጨክን ልብ ያለህ አትመስልም" አልኩና ፈገግ አልኩ።
"ቢራ አልናፈቀሽም?" አለኝ።
"መናፈቅ ነው?" አልኩት። በጀ ገባ፤ አጠመድኩት፤
"ያኔ ሻምበል ጋር ሳይሽ እኮ——" ከማለቱ እባክህ የዚያኑ ጊዜ አውቄብሃለሁ አልኩት ውሸቴን።

ከዚያም ወደ ነፋስ ስልክ አካባቢ ደበቅ ያለ ሆቴል ገባን። ሻወር ሁሉ ያለው ነበርና ተጣጥቤ የመጣንበትን ፈፀምን። እኔም ውዬ ሳላድር እንደምፈታ ሲነግረኝ ለሌላ ዙር የባለስልጣን ጨዋታ እራሴን አመቻቸሁ።

በሳምንቱ ተፈታሁ።

ውበቴ፣ ወጣትነቴ፣ ሴት መሆኔ፣ ለችግር ቢጋብዘኝም ከችግር አወጣኝ። ከመቶ አለቃዬ ጋር ደግሞ ለጥቂት ወራት ተምነሽነሽን። ሥራዬም እንድመለስ ተደረግሁ። ሁኔታውን ሁሉ አመቻችቼ ከዕረፍት ብዬ በነፃ አውሮፕላን አሜሪካን ጠፍቼ ገባሁ። የድሮ ጓደኞቼንም አገኘኋቸው። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ለጉብኝት እንኳ ብዬ አገር ቤት አልተመለስኩም። ——እስራ ስድስት ዓመት ሆነኝ።

ውበቴና ቁንጅናዬ ለህይወቴ የምፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያሟሉልኝ ሆነው የታዩኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሬ ነው ብል አልሳሳትም። የምፈልገውን ነገር ሁሉ ለማግኘት መዋሸት ማታለል፣ ማምታታት አለብኝ በሚል እምነት ነው ያደግሁት ማለት መሰለኝ። ከአንዱ ጋር እያለሁ እሱን አታልዬ ወይ ዋሽቼ ከሌላው ጋር መውጣት እንደትልቅ ሙያም አድርጌ በመውሰድ ነበር የን አፍላ ዕድሜዬን ያሳለፍኩት ብዬ ብነግራችሁሳ? ይህች ቀላማጅነቴ አብራኝ አድጋ ይሆን?

ይህን የጥንት ታሪኬን፣ እንደማመሬን ለምን እንደነገርኳችሁ የምታስታውሱት መሰለኝ። እንግዲህ ልብ ብላችሁ እዩት። ለኔ ጋብቻ ልዩ ትርጉም ያለው ይመስላል። ውበቴን ከኔ ጋር ለዘላለም ይኑርና በዚሁ ውበቴ ወንድን ማርኬ፣ አምታትቼው በቁጥጥሬ ስር አግብቼው እሱ የሚፈልገውን ሳይሆን እኔ የምፈልገውን፤ እሱ ተስማማበት አልተስማማበት ምን ተዳዬ? ብቻ እኔ ከተስማማሁበት መፈጸም ያለበት፤ . . እንደዚያ ነበር ማለት ነው እኔ ለጋብቻ የምሰጠው ትርጉም።

ዕድሜዬ እያረጀ ሲሄድ ይህ ስሜቱና ዓላማዬ ግን አላረጀም። የምፈልገውን ነገር ሁሉ በምፈልገው መንገድ የማግኘት ጉጉቴ ዘመን በዘመን እየተተካ ሲሄድ እየደበዘዘ በመሄድ ፈንታ እየጎላ በመሄዱ ነው መሰለኝ የሚያቅበዘብዘኝ።

በዚህች በአሜሪካንም በቆየሁበት በዚህ የአስራ ስድስት ዓመት ጊዜ ያው ጉጉቴ ሁሌም ከውስጤ እንደተንከላወለ ነው። ድሮ ጥንት አዲስ አበባ ሲኒማ ኢትዮጵያና ሲኒማ ኢምፓየር እንደሚታዩት ፊልሞች ቆንጃጅት እስታሪንጉ ለኔ ሲል ሁሉን በጣጥሶ፤ ቢያስፈልግም ገድሎ በመጨረሻ በአሸናፊነት ሲወጣ የምገኝ ሆኜ ነበር የሚታየኝ። ዛሬ ባይሆን ነገ፤ ነገም ባይሆን ተነገወዲያ፤ ተነገ ወዲያም ባይሆን ከዚያ ወዲያ ይኸው ዓላማዬ ግቡን ይመታል እያልኩ ስጠብቅ ነው እንዲህ ሆኜ የቀረሁት። ስንቱን ጎረምሳ፤ ስንቱን cute ወንድ እያፈራረቅሁ፤ ስንቱ እኔን ለማግኘት ያለ የሌለውን ሲያራግፍ፤ እኔም ዛሬ ያገኘሁትን እየናቅሁ ነገ የበለጠው ይመጣል እያልኩ ስማስን ከዚህ ደረስኩ።

ዛሬ ታዲያ እቤቴ ድረስ የመጣልኝን ይህን ሰው እንዲያ አመናጭቄ መላኬ በዚህ አብሮኝ በከረመው ባህርዬ ምክንያት ይሆን? በዚህ አብሮ አደግ ባህርዬ ሳቢያ በስልክ የቀላመድኩታና የዋሸሁት ያልሆነ የሆነ ነገር ሁሉ እሱ እኔ ጋ ሲመጣ ሊጋለጡብኝ ሲሉ ፈርቼ ነው?

አሁንስ ከሄደ በኋላ ስልክ ምን አስደወለኝ?

በሉ እንግዲህ የታሪኬን የመጨረሻ ክፍል በሚከተለው እትም አቀርብላችሁዋለሁ።

ይቀጥላል።

++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++

## ውድ አንባብያን

ይህ ታሪክ በዚህ መጽሄት ላይ መውጣቱን የተመለከተውና ታሪኩን የተከታተለው የዚህ ገጠመኝ ሁለተኛ ባለታሪክ የዚህኑ ታሪክ በሱ በኩል ያለውንና የተሰማውን ልኮልናል። የትዝታ ታሪክ እንዳለቀ በተከታታይ እናቀርብዋለን።

++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++

# ባላገርና ፖለቲካ

ከሂርጳሳ

(ከአለፈው የቀጠለ)

ባለፈው ዕትም የመንግሥት ውድቀት መቃረቡን፣ የባላገር ልቡ ከመንግሥት ጋር አለመሆኑን ይህንንም በተለያየ መንገድ መግለጽ መጀመሩን ተጨዋውተን ተለያየን። ዛሬ ደግሞ ከዚያው በመቀጠል የሀገሬ ባላገር በድህነቱ እናት በጎስቋላው ኑሮው ላይ የፖለቲካ ንፋስ ሲያመሰቃቅለው እንመለከታለን።

ባላገር በወደቀው መንግሥት ላይ ያለውን፣ ያሰማውን ሁሉ መዘርዘሩ አንድም ለቀባሪው አረዱት እንዳይሆን አለያም በወደቀ ዛፍ ላይ መጥረቢያ ማብዛት እንዳይሆንብኝ ብዬ አሰብኩ። የባለጊዜዎችን ጠረን፣ የባለጊዜዎቹን እውነት በአገሬ ባላገር በደልና ምሬት አስታክኬ ለማሳመርና ለማራመድ እንዳይመስልብኝም ሰጋሁ። . . . ባለፈ ጊዜ–ለወደቀ መንግሥት ብዙ ብዙ ነገሩን ብተወውስ አልኩ፤ ሆድ ይፍጀው ብዬ ቢቀርብኝ ወደድኩ።

. . . ወዲህ ደግሞ አንዳንዱን ነገር ባልፈው የባላገር ብሶት ከተነሳ ሳልተነፍሰው ሳይወጣልኝ ቢቀር የሚያመኝ ሆነብኝ። የአገሬ ባላገር ከባለጊዜ ፖለቲከኛ ጋር የተፋጠጠበት፤ ሁለት ዝሆኖች የተጣሉበት መስክ ሆኖ መጎዳቱን ሳላወሳው ማለፍ አልሆንልህ አለኝ።

ባላገር የፕሬዚዳንት መንግስቱን መንግሥት አንቅሮ የተፋበትን ምክኛት ከመዘርዘር በመለስ የወያኔ መረማመጃ መንገድ መሪ፣ ወንዝ አሻጋሪ ሆኖ ውስጥ ውስጡን ያገዘበትን ሁኔታ ሳልገልጽ ማለፍ አይሆንልኝም። . . . የዛሬዎቹ ባለጊዜዎች ሹሞቻችን ከተሜው ፊት ነስቶ ሆድ ሲብሳቸው "እኛ እኮ 85% የሚሆነው የገጠሩ ባላገር ይደግፈናል። አብሮን ተዋግቷል።" እየተባለ አፍ ተሞልቶ የሚቦተለከውን ዛሬም ባላገሩ ላይ የሚቀለድበትን መነሻ ሳላሳይ ዘልየው መሄድ ደግሞ አይሆንልኝም።

የእኔ እውነት የዚህ እጀ ጎልዳፋ ድሃ ባላገር ምሬትና ብሶት ነው። የዛሬውን ምሬቱን ችላ ብዬው ማለፍ ይከብደኛል። ከመሰረቱ እንጂ ከወገቡ መጀመር ደግሞ አይሆንልኝም። አፈር ገፍቶ፣ አፈር መስሎ፣ አፈር በልቶ በባዶ እግሩ፣ በባዶ አንጀቱ፣ ቅማል፣ ትኋን፣ ቁንጫና ቅንቅን በወረራት ጎጆው የኩሬ ውኃ እየጠጣ፣ ወዝ የሌላት ቁራሽ እየበላ ኑሮውን መግፋት (ይህችም ኑሮ ተብላ) ቢሳነው፣ ብረት ይዞ ከዱር ቢገባ ከዱር ደግሞ የጠበቀውን ሳላወሳው ማለፍ አልሆንልህ አለኝ። ያቺ ደሳሳ ጎጆው የመንደር ምስረታ በሚባል ዘመቻ ፈርሳ:–

የሞተ ሰው መልካም ቀኑ የደረሰ፣
የእኛማ ቤታችን በቁሙ ፈረሰ።

ሲል ጎጆውን ያፈረሰበትን ስርዓትና ባለ ጊዜ ለማፍረስ ደግሞ፤ቤት ይፍረስ አሉ ልጅ የዳርንበቱን፣

ሀዘንና ደስታ ስንት ያየንበቱን፣
ማፍረስስ አልጋውን ትኋን ያፈራውን።

ብሎ ጠመንጃውን ወልውሎ ኮብልሎ ዱር መግባቱ እውነት ነው። ጎጆዬ ሲፈርስ ቆሜ አላይም ብሎ ዱር የገባው ባላገር ቁጥሩ ልክ የለውም። ከገበያ ሳይቀር እየታፈሰ ወደማያውቅበት አገር ሰፈራ መላኩ ቢብስበት "ተዉኝ ቢል" የሚሰማው አጥቶ በሽመል እየተለመጠ በኤን ትሬ፣ በአይሮፕላን ጋምቤላና አሶሳ ቢጭኑት በአገር የቀረው ባላገር:–

ለመሸጥ ለመግዛት ገበያ ወጥተን፣
ሠፈራ ተነዳን በአፈሙዝ ተገደን።
ኧረ ዘመቻውስ ከአባት የቆየ ነው፣
እኛን ያስቸገረን ሰፈራ ሂዱ ነው፣
እኛን ያስቸገርን ከአገር ልቀቁ ነው።
እንግዲህ መሄድ ነው በረሃውን ወርደን፣
ደግሞ እንደ ዶሮቹ ሰፈራማ ካሉን።
ብሎ ብረት ይዞ መግባቱ እውን ነው።

የደረሰ ልጅ እየታነቀ ተጎትቶ ወደ ጦር ሜዳ መነዳት ሕግ ሆኖ በራስ ቀዬ በገዛ አገር መግባት መውጣት እንደ አይጥና ድመት ከሹማምንቱ ጋር ድብብቆሽ ቢሆንበት :–

ከጎታ ላይ ድመት ከማገር ላይ አይጥ፣
ድመት እይዝ እይዝ
አይጥ እመልጥ እመልጥ፣
እንደዚህ እኮ ነው የእኛ አቀማመጥ።
ወንድ ወለድኩኝ
ብሎ ወላጅ ደስ አይበለው፣
ነገ ጠዋት ብሔራዊ ለሚመለምለው፣

ሲል ጥገት ላሙን የእርሻ በሬውን ሸጦ ጠመንጃ ገዝቶ ጫካ መግባቱ አሌ የሚባል አይደለም። ተመልምሎ እንደ ፍሪዳ እየተጎተተ ወደ ጦር ሜዳ ከሚሄድ አንደኛውን አሻፈረኝ ብሎ ከዱር መግባቱ አንድም ምርጫ ማጣት፣ አንድም ወንድነት ነው። ከዱር የነበረውን "እንቢ ባይ" ከመቀላቀል ሌላ መሄጃ የለውም። ዱሩን ቀድሞ የያዘው ደግሞ ቀድሞ ዱር የገባው ነበር።

በዚህ አይነት ተገፍቶ ለወያኔ ያደረ ባላገር እየተቆጠረ ነው ዛሬ ድረስ "ድፍን ባላገር ሆ! ብሎ ይደግፈናል" እየተባለ ያለው።

ግራ የገባው የመንግስት ሹም መያዣ መጨበጫ ሲጠፋው በመጨረሻዋ ሰዓት እንኳ የሚወስደው እርምጃ ጭራሽኑ የሚያስጠላውና ባላገሩን የሚያስበረግገው ነበር። . . . በብቸናና በመርጦ ለማርያም አውራጃዎች ውስጥ ለምሣሌ እንዲህ ሆኗል። ለውትድርና ከተመለመሉት በርካታ ባላገሮች የተወሰኑት በሌሊት ከማሰልጠኛ ጣቢያው ጠፍተው ይወጣሉ። ይህን የሰማ አውራጃ አስተዳዳሪ አሰሳ አድርጎ አንድ ሁለቱን ይይዛል። የሌሎች መቀጣጫ እንዲሆኑ ይባልና በአሰሳ የተያዙትን ምልምል ባላገሮች ቀሚስ አስለብሶ በገበያ ውስጥ ሲያዞራቸው ይውላሉ። ወንዱን ልጅ እንደ ሴት ቀሚስ አልብሰው ገበያ ውስጥ መንዳታቸው በድፍን ጎጃም ተወራ።

ጎጃሜና መንግሥት ያን ቀን በቁርጥ አበቃላቸው። ማን ወንድ ሆኖ ማንን ቀሚስ ያስጠልቃል? ተባለ። እንቆቅው ጎጃሜ ማን የታጠቀው ሱሪ ከማን ይበልጣል? ሲል እልህ ያዘው። በዚያው ሰሞን ብቻ ብዙ ጎበዝ ዱር ገብቶ አደረ።

. . . ወዲህ ደግሞ መንግስት በሄሊኮፕተር ወረቀት ይበትናል። ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ የባላገሩን ድጋፍ ለማግኘት ቅስቀሳ ይዟል። "ትኋን ያዘ ተብሎ ቤት አይቃጠልምና ተበደልኩ ብለህ ተገፋሁ ብለህ አገርህንና ነፃነትህን በወራሪ አታስደፍር" እያለ ወረቀት ይረጫል። ባላገር ግን በአንድነት ተመካክሮ በየቀዬው ተማምሎ "እንጃ አባክ!" እያለው ነበር።

የመዋጋት ፍላጎቱ የወደቀው የመንግስት ወታደርም የባላገሩ ድጋፍ በሚያስፈልገው በዚያች ወቅት በተስፋ መቁረጥ መንፈስ የሚያደርገው ድርጊት የባላገሩን ድጋፍ የሚያስገኝለት ሳይሆን የበለጠ ለሽንፈትና ለውድቀት የሚያጋልጠው ነበር። . . . ወያኔ ደብረታቦርን ዳግመኛ መልሳ ስትይዝ በጎንደርና በጎጃም ድንበር ላይ መንግሥት ብዙ ሠራዊት አፍሶ ነበር። ይህ ሠራዊት ደግሞ መዋጋት የሰለቸው፣ በብዙ መስዋዕትነት የያዘውን ገዥ መሬት አዛዦቹ እየሸጡ ምራሉን ያላሸቁት ጦር ነው ይባላል። ከተማ ሲደርስ በየቡና ቤቱ እየገባ ሰውን ሁሉ ለማስበርገግ በገጠር ደግሞ የአባወራ ሚስት ለመድፈር የሚቃጣው መሆኑ በግልጽ ይወራ ነበር።

እንዲያውም በዚያው ሰሞን አንድ ባላገር የሕግ ሚስቱን አንድ ወታደር በጠመንጃ አስፈራርቶ ይጎትትበታል አሉ። ባላገሩ ሐዘኔታ ያገኝ መስሎት "ኧረ ጎበዝ የሰማኒያዬ ናት፣ የሰማኒያዬ ናት" እያለ ሊያስጥል ይወተውታል። የሕግ ሚስቴ ናት ማለቱ ነበር፣ የሕግ ሚስት ክብር ናት፣ የሚሞቱላት፣ የሚጋደሉላት፣ ከአባት ርስት በላይ የምትቆጠር። እጅሬ ወታደር "ግድ የለህም መቶ ሃያ አደርግልሃለሁ" ሲል መልሶለት የሕግ ሚስቱን፣ ባልተቤቱን አስነወራት አሉ። ያ ባላገር ማታውኑ የድሃ ጎጆውን አዳፍኖ ልጆቹን በትኖ ከዱር መግባቱ በድፍን ጎጃም ሲወራ ሰነበተ። "ነግ በእኔ" ያለውም ተከተለው።

ባላገር የድሃ ጎጆውን ያፈረሰበትን ሹም፣ ደህና ማላውን የነጠቁትን ኮሚቴዎች የሚያስወግድለት፣ ምንም ይሁን ምንም ብቻ የሚበቀልለት ጉልበተኛ ቢያገኝ ልቡ ፈቅዷል። የድሃ ጩኸት የሚሰማበት ጆሮ የሌለው፣ የደረሰ ወንድ ልጅ ከጉያው እየነጠቀ ለጥይት የሚማግድን መንግሥት የሚጥልለት ደህና ቀን የሚያመጣለትም መስሎት የወያኔን መምጣት ተመኝቷል። ሲመቸው ፊት ለፊት ሳይሆንለትም ውስጥ ውስጡን ወያኔን አግዟል፣ መንገድ መሪ፣ ወንዝ አሻጋሪ ሆኖ አረማምዷል።

ቂጣ ጋግሮ ጥሬ አንፍሮ አብልቷል። ባላገር ከመንግሥት ጠላት ጋር ላለመወገን የሚያመነታበት ልቦና አልነበረውም። እንኳን የሰው ልጅ በሰው አምሣያ የተፈጠረው፤ እንኳንስ ኢትዮጵያዊ እንደ እሱ ጠይም ሰው ከጉግማንጉግ ጭራቅ ጋርም ቢሆን በመንግስት ላይ ለመነሳት የሚያቅማማበት የቀረለት አንዳች ነገር አልነበረውም።ኢሕአዴግ ደግሞ ለዘዴው ሲል ተለሳልሷል፤ ጠባዩን አሳምሯል። እርግብ ለመያዝ በደረቷ ተኝታ እንደምትሳብ እናቲት ድመት አፉን ዘግቶ አንገቱን ደፍቶ ጨዋ፣ ገራም መስሏል። ጥሬ እንዲቆሉለት፣ ቂጣ እንዲጋግሩለት፣ ውሃ እንዲያጠጡት እንኳ ወደ ባላገር መንደር ጎራ ሲል አስተዛዝኖ መለመኑን አውቆበታል። ባላገር ደግሞ ይህቺን መሳይዋን ትህትና ልብ ይላል፤ ይገምታል። በዚህ ላይ ካድሬዎቹን አሰማርቶ ባላገሩን ይቀሰቅሳል። የወያኔ ካድሬዎች መናኛ መስለው ከአልፎ ሂያጅ መንገደኛ ጋር ተመሳስለው ይሰልላሉ። በየከተማው ውስጥ ባሉ ሆቴሎች አልጋ አንጣፊ ሆነው፣ አስተናጋጅነት ተቀጥረው፣ በየመንደሩ ልዋጭ የሚያዞሩ መስለው በየከተማው መንግስት የሚያደርገውን ልቅም አድርገው ይሰልላሉ። ሌላው ደግሞ የቅይጥ ኢኮኖሚው ኢንቨስተር መስሎ በታዋቂ ተወላጅ በኩል ለጦር አዛዦችና ለመኮንኖች ብር እያስታቀፈ፣ ውስኪ እየጋተ፣ ጮማ እያስቆረጠ፣ የሰራዊቱን ጓዳ ጎድጓዳ ያስበረብራል። ጥይት ሳይተኮስ ለሚለቀቅ ገዢ መሬት ምን ያህል እንደሚከፍል ይደራደራል።

ወያኔ ያልደረሰችበት ቀበሌ ባላገር ከሌላ አካባቢ ባላገር ጋር እየተላላከ ስለወያኔ ያጠያይቃል። ግዳጅ የሚሉት የችግር አማርኛ የሰው ባላገር ወያኔ ይዛ የምትመጣው ግዳጅ እንዳላት ለማወቅ ይላላካል። በገበያ፣ በለቅሶ፣ በተዝካር፣ በየሰንበቴው ባላገር ሲገናኝ ሌላ ጨዋታ ቀረ።

"ኧረ ይህቺ ወያኔ የሚሏት የግድ የምትለው ምን አላት? ሲል ይጠይቃል አንዱ ባላገር
"የግድ የምትለውስ የላትም አሉ" ይላል ሌላው
"ሠፈራ ሂዱ አትልም?"
"የለም"
"አምራቾች አትልም?"
"የለም!"
"ይህቺማ ደህነኛዋ ናት በል"
"ኮሚቴ አላት?"
"የለም"
"ብር አንጡ ትላለች?"
"ኧረ እሷ ብርም አንጡ አትል ምንም አንጡ አትል። የግድ የምትለው አንዳች ነገር የላትም። አንዳንዴ ቂጣ ጋግሩልኝ እያለች ዱቄት ይዛ ትለምናለች። የፈቀደ ይጋግርላታል፤ በጅም ካላሉአት የግድ ጋግሩልኝ አትልም።"
"ዳኝነትስ የምታውቅ ናት?" ይላል ጠያቂው መልሶ
"ለኢሠፓና ለአውራጃ ለኮሚቴው ደህና መድሃኒት ናት። እጇ ከገባላት ይዛ ጥብስ ታደርገዋለች። ይላል ሌላው ባላገር

. . . እንዲህ እንዲህ እየተጠያየቀ ባላገር ይህቺ ወያኔ የሚሏት ደርሳ የመንግሥትን መውደቅ፣ የበደሉትን ሹማምንት ውርደት፣ የተነጠቀው ማሳው ሲመለስለት፣ የእስከ ዛሬ በደሉ ሁሉ ዳኝነት ሲታይለት ለማየት ተመኝቷል። ወያኔ የምታመጣለትን ደግ ደግ ነገርም ይኖራል ብሎ ጓጉቷል። ብዙም ዘፍኗል።

እነ በግ አረዱ፣
እነ አሸከር ወግዱ፣
ወያኔ መጣና ተገለጠ ጉዱ።

ብሎም አወድሷል።

የራሱን መጨረሻም በውል ሳያውቀው:-

ቆፍረህ ቆፍረህ ባመጣኸው ዕዳ፣
ኢሠፓ እንጨት ልቀም መንጌም ውኃ ቅዳ።

ሲል በኢሠፓና በፕሬዚዳንቱም ላይ አሹፏል።

*        *        *

መንግስትና ወያኔ ማዶ ለማዶ ተፋጠዋል። መንግሥት ከአባይ ወዲህ ወያኔ ከአባይ ማዶ!
. . . በዚህ መሃል አንድ ቀን ፕሬዚዳንት መንግስቱ ብዙም አጀብ ሳያበዙ በሄሊኮፕተር ወደ ጎጃም ከተፍ አሉ። በጎጃም ክፍለ ሀገር ያለ ትልልቅ ባልስልጣንና ሹምንት የሚሞካከረው ባለስልጣን ሁሉ ከደጀን አለፍ ብሎ ባለው ኢትኖራ የገበሬዎች አምራቾች መንደር ተሰብስቦ ቆያቸው። እርሳቸው መላ ይዘው የሚመጡ ይመስል በተስፋና በጉጉት እንደየደረጃቸው ተኮልኩለው ጠበቁአቸው። ሁሉም በልቡ የእርሱ ጀንበር እየጠለቀች መሆኑ ገብቶታል። ነገር ግን በጓድ ፕሬዚዳንት ፊት የፈራና የደነገጠ መስሎ ላለመታየት ሁሉም ልቡን ነፋ አንገቱን ሰገግ አድርጎ ከእላቸው በፊት ለመሞት የተዘጋጀ መስሎ ተቀበላቸው። ደግሞ እርሳቸው የሚያመጡት መላ አይታወቅም። ከረባት ያሰረ ሹም የለም፣ ሙሉ ሱፍ የለበሰ ሰው አይታይም።

ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ቅዝዝ ብለዋል። እንደሌላው ጊዜ አይኖቻቸው ወዲያ ወዲህ አያማትሩም። ነገር ግን የድንጋጤም ይሁን የፍርሃት ምልክት አይታይባቸውም። ድል እየተመታ ያለ ጦር መሪም አይመስሉም። እርሳቸውም እንደባለስልጣኖቻቸው ራሳቸውን አደፋፍረው ይሁን በእውነትም ሳይበገሩ ቀርተው ብቻ ፍርጥም ብለዋል። እንደደረሱ ጥቂት ሹሞችን ጨብጠው አነጋገሩና ከኢትኖራ አምራቾች ተመልምሎ ሲሰለጥን የሰነበተውን የባላገር ሠራዊት ይጎበኙ ጀመር። ይህ ሠራዊት ከገበሬ ማኀበራት የተመለመለ ሲሆን በበቂ ሁኔታ ሰልጥኖ ከነፍስ ወከፍ መሣሪያ ሌላ የቡድን መሣሪያዎችን ጭምር የታጠቀ ነው ይባላል። የኢትኖራ ገበሬዎች አምራቾች ጠንካራ የሚባል አምራች ሲሆን ከመንግሥትና ከአለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪዎች ባገኘው ዕርዳታ ጭምር እንደ ሞዴል አምራች የሚቆጠር ነበር።

የአምራች ማኀበሩ ተራው አባል ግን እንደማንኛውም ባላገር ከልክ ያለፈ ምሬትና ብሶት ነበረው። በባዶ ቤት፣ በባዶ አንጀቱ በረሃብ ተኮራምቶ የሚኖር መሆኑ ሐሜት ሳይሆን ውስጥ አዋቂ ወይም ጠጋ ብሎ የጠየቀ ብቻ የሚያውቀው እውነት ነበር። ተመራጮቹ የኮሚቴ አባላት ግን ምቹ ኑሮ ያላቸው ትላልቅ ባለስልጣኖች ነበሩ።

ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ሰራዊቱን ሲጎበኙ ተሰብስቦ የቆያቸው ባለስልጣናትም እንደየደረጃቸውና እንደየፕሮቶኮላቸው ጠጋም ፈንጠርም ብለው እጆቻቸውን ወደ ኋላ አድርገው ይከተላሉ። ፕሬዚዳንቱ ሰራዊቱን እየጎበኙ እያለ የአምራቾች ማኀበር ሊቀመንበሩ ሸነጥ አደረገውና መሸለል፣ መፎከር ያዘ። እየተንቆራጠጠ አለው አለውና ዞር ሲል ጓድ ፕሬዚዳንት በአርምሞ ቆም ብለው እያዩት ነው። ትኩር ብሎ አያቸው፣ እርሳቸውም ትኩር ብለው አዩት። ተግባብተዋል። ሁለቱም በዚህች ቀውጢ ወቅት ለሕልውናቸው መቆየት እንደሚፈላለጉ በዓይን ብቻ ተነጋገሩ። ቃልኪዳናቸውን ማደስ ሊኖርባቸው ነው። አዳኙን እንዳየ ነብር ፈንጠር አለና:-

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፣
አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፣
መንግሥቱ ኃ/ማርያም የተከሉት ዋርካ፣
ቢገፉት አይወድቅም ጠላት ቢተካካ።

አለ።
ተሰልፎ ከነበረው ሠራዊት አንድ ሁለቱ እየተንቋረጠጡ በመፎከር ተቀበሉት። ፕሬዚዳንት መንግስቱ ዝም ብለው በተመስጦ ፉከራውን ሲያዳምጡ

ቆዩና እስካሁን ያልመጣላቸው አዲስ ሃሳብ ትዝ እንዳላቸው ሁሉ ከፊታቸው ላፈጠጠባቸው ችግር ጥሩ መላ ያገኙ ያህል አንገታቸውን ሰገግ አድርገው ቀና አሉ። ራሳቸውን ነቅነቅ አደረጉና፡-

"ጓዶች የምንገናኘው ቀይ ባሕር ነው" አሉ።

"የምንገናኘው ቀይ ባሕር ነው" የሚል የብዙ ባላገሮች ድምጽ እንደ ነሐሴ ነጎድጓድ አስገመገመ። ሹሙ ሁሉ አሁን ከቅድሙ ትንሽ ቀለል ያለው መሰለ። ፕሬዚዳንት መንግስቱ ስራዊቱን ተሰናብተው ከጎጃም ባለስልጣኖች ጋር ለመወያየት ወደ አዳራሹ አመሩ። ስብሰባው አጭር ነበር። መመሪያውም ጥብቅ! ወዲያው ሁሉም ሹም ስቴሽን ዋገኑን እያስነሳ ወደ ግዛቱ ተፈተለከ።

ድፍን የጎጃም ሹም መሰንበቻውን በተሰጠው መመሪያ መሰረት ለምልመላ ከወዲያ ወዲህ ይራወጣል። ባላገር ግን ሁኔታውን አውቋል። ወያኔ ደብረ ታቦርን መልላ ስትይዝ ወልድያን በእጇ ስታስገባ መሃል ሜዳ ድረስ ስትዘልቅ ክደብረ ታቦር አልፋ አመድ በርን፣ ወሮታን ጨምራ ሐሙሲትን ይዛ ከአባይ ማዶ ዘንዘልማ ላይ ቆማ ባሕር ዳርን ማዶ ስታየው የመንግሥት ጀንበር በእርግጥም እየጠለቀች መሆኑን በሚገባ አውቋል።

የመንግስት ሹም ደግሞ ይህን የገበሬ ሠራዊት በገፍ መልምሎ ወያኔን ከአባይ ማዶ ገድቦ እንዲይዝ እንዲያደርግ ውርድ ከራስህ ተብሏል። ጥብቅ መመሪያ ተቀብሏል። ኢትኖራ ላይም ለፕሬዚዳንቱ ቃል ገብቷል።

ባሕር ዳር ጭንቅ በጭንቅ ሆናለች። የሚወጣ የሚገባ መኪና የለም። ቁጥር ስፍር የሌለው ሰራዊት ይተራመሳል። የወታደር መኪናዎችና ታንኮች ሰራዊት የጫኑ ካሚዮኖች ይሄዳሉ ይመጣሉ። አፍጦ የመጣውን ጠላት ለመመከት የተሰናዱ ይመስላሉ። . . . ወዲህ ደግሞ አለቃና ጭፍራ፣ አዛዥና የበታች በየፊናቸው በራሳቸው መንገድና ብልሃት ነፍሳቸውን ለማዳን ድብብቆሽ ጀምረዋል። ትልልቁ ሹም ኮተቱን አስጭኖ ቤተሰቡን አዲስ አበባ ልኮ ለአንድ ለራሱ ደግሞ አዲስ ላንድ ክሩዘር እስከ አፍ ጢሙ ነዳጅ አስሞልቶ ከግቢው አቁሞ ይጠባበቃል። ግም ቢል ፈትለክ ለማለት! ትንንሹ ሹም መግቢያ መውጫ ፍለጋ ወደ አንድ ስርቻ ለመግባት አቆብቁቧል። የባላገሩ የኮሚቴ አባላትም እንደአቅማቸው ዞር ለማለት ተዘጋጅተዋል። ባላገር ይህን እያየ፡-

እነ ፍርድ ሸንጎ
እነ ሊቀመንበር ምንና ምን ናቸው፣
አውራጃው ኢሠፓው ምንና ምን ናቸው፣
ሲሮጡ ያድራሉ ዛሬ በተራቸው።

እያለ ይገጥምባቸዋል።

ከአባይ ወዲህ ማዶ በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ከአባይ ወዲያ ማዶ ከሐሙሲት ጀምሮ እስከ ወልዲያ፣ እስከ መሐል ሜዳ ድረስ ወያኔ ተደላድላለች፣ ምሽግ ቆፍራ መሬት ገብታለች። በኢሠፓ ቢሮ በባለስልጣን ቤት ውስጥ ገብታ ተንሰራፍታለች። ግልገል ሱሪዋን፣ ሽርጧን፣ ሽበጧን፣ ጨርቃ ጨርቋን እያንጨፈጨፈች አስጥታበታለች። ቀን ቀን ጥፍት ብላ ትውልና ማታ ማታ ከበሮ ስትደልቅ ታድራለች። ከአባይ ማዶ ላለው አገር መንግሥት ሆናለች።

ባላገር ደግሞ የደረሰበትን በደል እንዲፈታለት፣ የጓጓለት ዳኝነት እንዲታይለት አቤቱታውን ጀምሯል። በወደቀው መንግስት ማሳዬን ተነጥቄ፣ ልጄ ከቤት ወጥቶ ቀርቶብኝ፣ ቤቴን አፍርሰውብኝ እያለ የወያኔ ባለስልጣን ነው ለተባለው ሁሉ አቤት ማለት ይዟል። እከሌ የሚባለው ሹም ማነህ የሚባለው ኮሚቴ እንዲህ አደረገኝ፣ እንዲህ ሆኜ፣ እንደዚያ ተጎድቼ እያለ በደሉኝ የሚለውን ለመክሰስ ይዳክራል። ገሚሱ ደግሞ የወያኔ ኮተት ተሸካሚ፣ አጋሰስ ነጂ፣ የኮር ምልምል፣ መንገድ መሪ፣ ቋንቋ አስተርጓሚ ሆኖ ያዘጠዝጣል። ውሎ አድሮ፣ ወጥቶ ወርዶ ሁኔታውን ሲያየው ወያኔ አንዱንም የምትቆርጥ አይደለችም።

ዳኝነቱን ሁናበት የምታውቀውም አትመስልም። የተረፈው ነገር የለም። ፋይዳ ያለው ጠብ ያለለት ነገር አልነበረም።

. . . የወያኔ ግዛት ዳኝነት የለው፣ አስተዳደር የለው፣ ሹሙ ከጀሌው አይለይ፤ ትናንት አቤት የተባለበቱ የወያኔ ሹም ነገ በቦታው ላይ አይገኝ። ባላገር ግራ የገባ ነገር ሆነበት። . . . አቤት የሚባልበቱ የሹም ቢሮ ወያኔ መኝታ አድርጋዋለች። የቀረውንም ማብሰያ፣ ሌላውም የአጋሰስ ማሰሪያ ሆኗል። ብቻ ዝም ብሎ የሜዳ ላይ ፍርድ! . . . ባላገር ደግሞ የሜዳ ላይ ፍርድ አይሆንለትም። ጣለው፣ ገረፈው ማለት ደም አቃብቶ ነገ ሌላ ጣጣ እንደሚያመጣም ያውቃል። ሁኔታው አላማረውም፣ ለንግግርም አላመቸውም።

. . . መንግሥት ከአባይ ማዶ እንካሳና አንድ አይናው ሳይቀር ድፍን የአገሩን ባላገር ይመለምላል፣ ለውጊያ ያሰለጥናል። ከአባይ ወዲህ ማዶ ወያኔ የአገሩን ባላገር ሰብስባ ሕዝባዊ ፍርድ ስታስፈርድ ትውላለች። ባላገር ስራ ትቶ ሞት ሲፈርድ፣ ዕድሜ ልክ እስራት ሲበይን፣ ሐብት ንብረት ሲወርስ፣ ቀኑን ሙሉ በስብስቦሽ ላይ ተጥዶ መዋል ያዘ። ግራ ቀኝ የሚያዳምጥ ዳኛ በሌለበት በቂም በቀል አንደበት የቻለውን ያህል በተከሳሽ ግለሰቦች ላይ የፍርድ ዓይነት ሲቆልሉ መዋል እንጂ መላ ያለው ነገር ጠፋ። ባላገር እንደጓጓው ነገር የሚቆርጥ ሹም፣ አቤቱታውን ሰምቶ አንተም ተው አንተም ተው ብሎ አስማምቶ በሀገር የሚያኖር ዳኛ ተወያኔ መሃል አላገኝ አለ። እንዳማረው ቀረ። ይሆናል ብሎ ያሰበውና እየሆነ ያለው ዱባና ቅል

(ወደ ገጽ 40 ይዞራል)

## . . . ባላገርና ፖለቲካ

ለየቅል ሆነበት። ባላገር በሆዱ ማጉረምረም ያዘ:—

የአገሬ ባላገር በል አውራ
በል አውራ የማታገኘውን፣
አውቄብሃለሁ ከሆድህ ያለውን።

ሲል እርስ በእርሱ መነጋገር ጀመረ። የወያኔ ነገር ነገሯ፣ አካሄዷ ገብቶታል። ትሻል ሂዳ ትብስ እንደመጣች ጠርጥሯል።

ይሆን ብዬ ነበር እንዳይሆን የሆንኩኝ፣
ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁኝ።

ሲል የልቡን ተነፈሰ።

ቢያየው ቢያየው ወያኔ ማለት ሕዝባዊ ፍርድ፣ የኮር ምልመላ፣ ግምገማ፣ ስብሳቦሽ እያለች ከማወነጃጀል፣ ከማቆላለፍ በቀር አንዳች የሚረባ ነገር የሌለባት ሆና አገኛት። መሾም፣ መሻር፣ መሾም፣ መሻር . . . ደግሞ ሳይሰነበት ሌላ መሾም እንደገና ደግሞ እሱን ሽሮ ሌላ መሾም–የልጆች ጨዋታ ዓይነት!!

ወይ ሹመት ወይ ስራ ፍለጋ ወደ ወያኔ ተጠግቶ ሲያቶስቁስ የከረመው ሁሉ ብዙም ሳይሰነብት ግምገማ፣ ሕዝባዊ ፍርድ ተብሎ እስር መግባት ሆነ። ከገቡ ደግሞ መውጣት የለም። ይህን ያየ ባላገር:—

የኢሕአዲግ ግዛት በጣም የረቀቀው፣
ሰዎ የሾመውን ዓርብ አውርዶ ጣለው፣
ሲያዘጠዝጥ ከርሞ ወህኒ ተረፈው።

በማለት ወያኔ ጉያ የገቡ ልጆቹን ያስጠነቅቅ ጀመረ።

. . . ምርጫ የለም። መንግሥት ከዓባይ ማዶ ማኅበር እንደደረሰባት ባልቴት ያደፈድፋል። አንዳንዴም ወያኔ በያዛቸው ቀበሌዎች ላይ በአውሮፕላን ቦንብ እየጣለ ሰማይ ምድሩን ያደበላልቀዋል። ወያኔ ደግሞ ዳኝነት አታውቅ፣ አስተዳደር የላት፣ መላ አትሰጥ። ባለገር ምርጫ በሌለው አጣብቂኝ መሃል ገባ። አፉን ሞልቶ ከፉው ቀን አለፈልኝ እንዳይል የመጣለት የተረፈው ደግ ነገር የለም። ለሄደው እንዳያዝን የማይረሳው ቁስል አለው። እናም:—

ለሄደው እንዳላዝን የቆየ ቂም አለኝ፣
ወይ እንዳልደሰት የዛሬው ባሰብኝ፣
ዝም ብዬም እንዳላይ አላስችልህ አለኝ፣
ንቄም እንዳልተወው የራሴው ሆኖብኝ፣
የሰማዩ ጌታ እስቲ አንተው ገላግለኝ።
ሲል አምላኩን መማፀን ጀመረ።

(ይቀጥላል)

## ሰብአዊ መብት ተሻሻለ

እየራበን ጠግባችኋል፣
እየሞትን ኖራችኋል፣
በአምባገነኖች ተመረን፣
በዘረኞች ተሰቃይተን።
ገበሬው ሞፈሩን ሰቅሎ፣
ተማሪው ብዕሩን ጥሎ፣
እየተሰቃየ ወታደሩ፣
እየተጉላላ ምሁሩ፣
መኖር እያቃተን
"ኖራችኋል" ተባልን።
መቶ ሺዎች በእስር ሲማቅቁ፣
ኢትዮጵያዊያን ያለ ፍርድ
በአደባባይ ሲገደሉ፣
ዘረኝነት ስር ሰድዶ፣
አትራፊ ፋብሪካዎች፣
ታዋቂ ምሁሮች፣
እስትንፋስ የሚዘሩ ሐኪሞች፣
አየር መንገዳችን ሳይቀር፣
በዘረኞች ሲበታተን —
ሰራተኛው ሲባረር፣
እያየን እያስተዋልን
ተብሎ ተነገረን።
"ሰብዓዊ መብት ተሻሻለ"፣
ፕሬስ ሲታፈን
ጋዜጠኛው ወህኒ ሲወርድ፣
ኢትዮጵያን ማለት ሲያስወነጅል፣
በችሎት ሲያስፈርድ፣
ወገን በረሃብ ሲሞት
ዳቦ እያለ ሲያቃትት፣
የምርጫ ኮሮጆ ሲቀርብለት፣
በአይናችን እያየን፣
በጆሮአችን እየሰማን፣
ከወዳጃችን ካስጠቂያችን፣
ከታላቁ አሜሪካ ተመሰከረልን፣
እንዳሻን መኖራችን
ዲሞክራሲ መጥገባችን ተነገረልን፣
ተባለ!
"ሰብአዊ መብት ተሻሻለ"
(አገሬ)

# አውላቸው ደጀኔ
## 1927-1986



ታዋቂው ተዋናይና የኪነ ጥበብ ባለሙያ አውላቸው ደጀኔ ባደረባቸው ህመም ሲታከሙ ቆይተው ባለፈው ነሀሴ 20 1986 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ቀብራቸውም አዲስ አበባ በቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስትያን ተፈጽሟል። አውላቸው በ1917 ዓ ም ግንቦት 24 ከአባታቸው ከአቶ ደጀኔ ድንቁና ከእናታቸው ከወይዘሮ ዠማነሽ ዘወልደማርያም እንጎለላ አጠገብ ደበ ጎጆ በምትባለው ቦታ ይወለዳሉ።

አውላቸው በመጀመሪያ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት፣ ከዚያም በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት፣ በሀረር የአገር ፍቅር ቲያትር ቤት በመጨረሻም ከፍተኛ ዝናን ባተረፉበት ቀደም ሲል ቀ.ኃ.ሥ. በኋላም ብሄራዊ ቲያትር ቤት ለረዥም ዘመናት አገልግለዋል። የጎንደሩን ፋሲለደስ የኪነት ቡድን አሰልጣኙ በመሆን ዝናን ከሚያተርፍበት ደረጃ አድርሰውታል። አውላቸው ከተውኔት ሥራ በተጨማሪ የተለያዩ ሀገረሰብ ሙዚቃ በመጀመሪያ ያሰባሰቡትና በመድረክ እንዲታዩ ዘፋኞችንና ተወዛዋዦችን ያሰለጠኑ እንደሆነ ይነገርላቸዋል። የተለያዩ ብሄረሰቦች በሚገኙበት አካባቢዎች በመሄድ በቴፕ ቀድተው ውዝዋዜውን አጥንተው በመምጣት ያሰለጥኑ እንደነበረ ታውቋል። በአፍሪካ፤ በሩቅ ምሥራቅና በአውሮፓ አኩሪ የተለያዩ ብሄረሰብ ጨዋታዎቻችንን በማሳየት ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

በተውኔት ሥራ አውላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፉበት "ንፁህ ደም" የተሰኘው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የታየው ተውኔት ነበር።

አውላቸው በጠቅላላው ሠላሳ የሚሆኑ ተውኔቶች ላይ ተሳትፈዋል። አብዛኛው ተውኔት ላይ የተሳተፉት በመሪ ተዋናይነት ነበር። አውላቸውን በቅርቡ በጣም ታዋቂ ያደረጉዋቸው ተውኔቶች ጡረታ ከወጡ በኋላ በመሪ ተዋናይነት የሰሩዋቸው "ባልቻ አባ ነፍሶ" በሀገር ፍቅር ቲያትርና "የእዛውንቶች ክበብ" በብሄራዊ ቲያትር ነበር። "የእዛውንቶች ክበብን" የተመለከተ ሁሉ ግራዝማች ተግ ይበሉን ሁሌ ሲያስታውስ ይኖራል።

አውላቸው የአምስት ልጆች፤ ሶስት ሴቶችና ሁለት ልጆች አባት ነበሩ። ሁለቱ ልጆቻቸው ያሉት አሜሪካን አገር ነው። አውላቸው በመድረክ ላይ ብቻ ሳይሆን ሁል ጊዜ ኮሜዲ የተላበሰው ጨዋታቸው በሚያውቋቸውና በቤተሰቦቻቸው ጋ የማይረሳ ትዝታ አለው።



አውላቸው እንደ ባልቻ አባ ነፍሶ

# የግጥም ጉባኤ

## ዋ እናት ጦቢያ

ማህደረ ዛጉዬ
(ሴንትሉዊስ፣ ሚዙሪ)

የታሪክን ሥንክሣር በራፍ፣
አዲስ ምዕራፍ ከፋች
የጥቁሮችን መስተዋድድ፣
መስተፃምርን መሥራች
ማንነት ኅሞታቸውን፣
ኮስትረው በውል ያስመኩሽ
ግስላ ሆነው ወኔ ይዘው፣ ታሪክን የፃፉልሽ
ከአልፋ ኅልቀተ ዓለም፣
በየጎራው የሚያስኮሩሽ
የነብር አራሽ ሆነሽ፣ እነደነበሳ የተጋፈጥሽ
ዋ ኢትዮጵያ ብሎ ሀገር፣
ተሠርዞሽ የለም ተባልሽ?
ለአፍሪቃ ህዝቦች አርነት፣
የማንነታቸው መግለጫ
በንዋዩ ቅኝ ግዛት፣ ለደነበረ ገገር ምርጫ
ዳማ-ከሴ ቅባ-ቅዱስ፣ ሠላሳ አፅቅ ማጠጫ
ለኮሎኒያሊስት ድንፋታ፣ነዛሪ ኃያል ጡጫ
የትብብር የቡሄ ችቦ፣
የስንደዶ ድምር ግጫ።
የትውልድ መዘክር አሻራ፣
የትምሳሌነታቸው ጮራ
እምዬ ኢትዮጵያ እናት-ዓለም፣
የጥቁር ጫጉላ ሙሽራ
ይወዷታል እንጂ በፍቅር፣
በናትነት ይመኩባታል
ከአልማዝ ዕንቁ በበለጠ፣
እንደ ፅላት ያከብሯታል
እንዴት እንደአስቃጥላ ሰፌድ፣
እንቀርቅበው ይጥሏታል።
ዋ ኢትዮጵያ!
የስንቱ ቲዎሪ ሀሳብ፣
ባዳ ነገር አዲስ ርዕዮት
ዘመን አመጣሽ የንግዴ ልጅ፣
ተረት-ተረት ውሸት-ውሸት
ደግሞ እምዬ ትሁን፣
የመቶ አመት ታሪክ ያላት?
ምነው ኢትዮጵያ እናት ዓለም፣
እንደዚህ ህፀፅሽ በዛ
እንዳልነበሩ ልጆችሽ፣ ለጥቁር ህዝቦች ቤዛ።
የነብር አራስ ሆነሽ፣ እንዳንበሳ የተጋፈጥሽ
ዋ ኢትዮጵያ ብሎ ሀገር፣
ተሠርዞሽ የለም ተባልሽ?

## ወይ የጊዜ ግሽበት
(ዘ ኢንፍሌሽን ኦፍ ታይም)

ከልሳኑ ሥምረት
(ሴንት ሉዊስ፣ ሚዙሪ)

እንደ ሲባጎ ተቀንጭቦ፣ በመቀስ ከተቆረጠ
እንደ ጤፍ ዱቄት ልሞ፣
በወፍጮ ከተዳመጠ
የረዥም ዘመን ልፋት፣
እንደ ቲማቲም ከፈረጠ
የትእየለሌ ተመክሮ፣ እንደ ቅቤ ከቀለጠ፤

ጊዜም እንደ ቀጭን ድር፣ ሰልስሎ ከተጠበሰ
ዋጋውን አጥቶ መንምኖ፣ አርሮ ከተጠበሰ
ተቆልቶ ተኮማትሮ፣ እንደ ቋንጣ ከታመሰ
ይብላኝ እንጂ ለገዝጋዡ፣
ታሪክስ መች ይሞታል
ይህ ትውልድ ባይሰማው፣
መጪው ጀግና ያመጣዋል።

የሦስት ሺህ ሥልጣኔ፣
በምዕት ዓመት ከተፈታ
የዘመናት የአበው ቅርስ፣ በግሽበት ከተመታ
የፀረ-ቅኝ አኩሪ ታሪክ፣
በልብ ወለድ ከተምታታ
የኅብረት የፈረንጅ ቀለም፣ ከቀረበ ለጨረታ
ቱሪስት ይታለል እንጂ፣
በድንጋይ ዳቦ ማን ሊረታ።

ታሪክ እንደ እንሶስላ ሥር፣
በባልጩት ከተላጨ
እንደ ሠናፍጭ ላምቶ፣ እንዳፈር ከተፈጨ
ተዘራዝሮ ተራርቆ፣ በዝርያ ከተቋጨ
ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃ፣
ሊጡ ቀጥና ተረጨ፤
እንደፍትፍት ተፈትፍቶ፣ መርሁ ተኅሳቆለ
ሙሉኩዩሉ ተከስክሶ፣ እንደ ክምር ተቆለለ
የንድፈ-ሀሳብ ጋጋታ፣ የባዕድ ምች መገለ
ስህተቱ አፍጥጦ ወጥቶ፣
እንደ ቡጉንጅ ጓጎለ፤
ኬኒያታ እንዳሉት፣ ማንነትህ ታረደ
አይ ሚስተርን አማኝ! ሀገርህ ተወሰደ
አይን ጨፍነህ ስትፀልይ፣
ታሪክም ተደመደመ።

# የዘፈን ግጥም

ከኀበዜ ረታ
(ዳላስ፣ ቴክሳስ)

ጠንበለል ሎጋ ናት የአርቲ ኩትኩት፣
እህል የማትበላ ማርና ወተት፣
ንጉሥ ከሥጋቸው ፈልቀቅ ያሉላት፣
እንች ፍተይ ብለው እንዝርት ሰጧት፣
ፈተለች የነጭ ሀር ለቤተ መንግስት፣
ደግሞ ጀምራለች የአለላ ስፌት።
ጦርዋ ባለ ሽቦ ፈረስዋ ሠጋር፣
ምጣድዋ ቀንጠፋ ወንበርዋ ግራር፣
ከዚች ዓይነት ሰው ጋር ፍቅር መጀመር፣
ብረት ምጣድ ጥዶ ቅቤ መጋገር፣
ውሃ በብርሌ ወዝቶ ማደር።
የሚያምረው ደረቷ የሚያምር ቁልፍ አለው፣
ያንን ገለጥ፣ ፈታ፣ ዳበስ፣ አድርጎ ይገባል ሀብት ያለው፣
ሀብት የሌለኝ ድሀ ከበርዋ ላይ ቆሜ፣
ጭራሮ መዝጊያዋን ጨረስኩት ቆርጥሜ።

---

## "ዕሮሮ"

ብሩክ ተረፈ
(ከዳላስ)

ልቤ አንዱን ከጀለ ወዳጅ ያገጣጥመኝ፣
የትዳር ጓደኛ ከየት ብዬ ላግኝ፣
እዚህም እዚያም ስዘል እድሜዬም ገፋብኝ፣
እንዲህ ለምትሉ ለእናንተም ምርጫ አለኝ።

ዘፈኑ፣

መጀመሪያ ማወቅ መተዋወቅ፣
ቀስ ብሎ በፍቅር መሳሳብ፣
ሲይዝ አይታወቅ ልብ ሲሰርቅ፣
እንዲህ ያደርጋል ወይ ፍቅር.....
ወይ ፎንቃ።

ሁሉ ተትረፍርፎ ሰላሙን ላጣችሁ፣
ትዳራችሁ ሊፈርስ ጥቂት የቀራችሁ፣
በፍቅር ቫይታሚን ጉዳት ላለባችሁ፣
የጥሌን ጨዋታ እንኩኝ ልጋብዛችሁ።

ዘፈኑ፣

ምግብማ ሞልቷል ሆዴ መች ጎደለ፣
ፍቅራችን ብቻ ነው ያልተደላደለ፣
ሁል ጊዜ ብበላ ብጠጣ እንዳሳማ፣
ምን ያደርግልኛል ለኔ ካልተስማማ።

በላጤነት ኑሮ ብዙ ልምድ ላለው፣
ቴሌቪዥን ብቻ ጓደኛው ለሆነው፣
ሳያስበው ፍቅር ለነደፈው፣
ይህን ዘፈን ያዳምጥ መድህኒት ቢሆነው።

ዘፈኑ፣

ብቸኝነቴን ነው እኔ እማስታውሰው፣
አልጀመርኩም ነበር ፍቅር ከሌላ ሰው፣
ዛሬ ተረታሁኝ ድንገት ሳላስበው።

እየወደዳችሁ ለተለያችኋት፣
ለብዙ አመታት ለምትናፍቋት፣
በውጪው አለማት ላለችው በስደት፣
አንድ ልበላችሁ ይህን ዘፈን ስሙት።

ዘፈኑ፣

ስናፍቅሽ ውዬ አንቺን ውብ ሳልምሽ፣
ስጠብቅሽ ውዬ አንቺን ውብ ሳልምሽ፣
መራራቅ መጣና መራራቅ መጣና፣
ዛሬም አልተገኘሽ።

የፍቅርን ሚስጥር ጠልቆ የተረዳ፣
ሁሌ ትዝ እያለው እሚያስብ በማለዳ፣
የኔዋ ከዳችኝ እያለ ለሚገባው እዳ፣
ይህን ቢዘፍን ይሻላል ብዙም ሳይጎዳ።

ዘፈኑ፣

እረ በከተማው ጭራሽ በሀገሩ፣
ከእኔና አንቺ በቀር እነማን ነበሩ፣ (2x)
አለም ሳይሰለጥን ጊዜው ሳይሻሻል፣
የሰራነው ሁሉ እንዴት ይረሳሻል። (2x)



# ቢስቁም ባይስቁም



## ዳኛና ምስክር

ሰውዬው ለምስክርነት ተጠርቶ ቃሉን ለመስጠት ፍ/ቤት ይቀርባል። ዳኛውም ስሙንና ዕድሜውን ከጠየቁት በኋላ ወደ መስቀለኛ ጥያቄ ከመግባታቸው በፊት

ስንት ልጆች አሉህ? ሲሉ ይጠይቁታል። ለምስክርነት የተጠራውም ሰው "አበበ፣ ቆዩኝማ በቀለ አለ። ወይኒቱ አለች። ደግሞም ካሳዬም አለ። እንጌትነት፣ እነሽዋረገድ . . . ደግሞ እነ እልፌ" እያለ ሲቆጥር ዳኛው ያቋርጡትና

"ስማቸውን ተወውና ቁጥራቸውን ንገረኝ" ይሉታል።

"የለም ጌታዬ! እኔ ለልጆቼ ስም እንጂ ቁጥር አልሰጠኋቸውም" አለ ይባላል።

* * *

## ከወደ እግርሽ ሲደርስ . . .

ለአንድ ትልቅ ድግስ ወደ አንድ አገረ ገዢ ቤት የተጠራ አዝማሪ ተጋባዦን እያዝናና እያጫወተ ተጋባዦቹም ባለቤቶቹም ደስ ይላቸዋል። ነገር ግን አዝማሪው የሚፈልገውን ያህል ሽልማት ባለማግኘቱና የተሰጠውም ጉርሻ እንደነገሩ በመሆኑ ይበሳጫል። በዚህም ምክንያት ያሞገሰ መስሎ የሚሳደብበትን ነገር ሲፈልግ የአገረ ገዢው ሚስት በመልካቸው ውብ ቆንጆ ሆነው ከወደ እግራቸው ግን ሸፋፋ ቢጤ መሆናቸውን ይመለከታል። አዝማሪውም ወዲያው ይህቺን ሸፋፋነታቸውን ቀለብ ያደርግና በማንጎራጎር

አይንሽን ጡጉርሽን፣ አንገትሽን ዳሌሽን
ውበት ደምግባትሽን
ሰራና ሰራና እግዜር ቢታክተው
ከወደ እግርሽ ሲደርስ አለሽ እንደመተው"
ሲል ያሞገሰ መስሎ ሰደባቸው ይባላል።

* * *

## እሺ . . . ነገ

አንድ ባለጉዳይ ጉዳይ ያጋጥመውና ወደ አንድ ባለስልጣን ቢሮ ይመላለሳል። ባለስልጣኑም ጉዳዩን ሳይመለከቱለት ባለጉዳዩ ወደ ቢሮአቸው በመጣ ቁጥር "እሺ ነገ" እያሉ ይመልሱታል። መመላለስ የሰለቸው ባለጉዳይ አንድ ቀን እንደተለመደው ወደ ባለስልጣኑ ቢሮ ገብቶ ጉዳዩ ምን እንደደረሰለት ይጠይቃል። "እሺ–ነገ ተመለስ" ሲሉ የተለመደውን መልስ ይሰጡታል። ነገሩ ያበሳጨው ባለጉዳይም

"እባክዎ ጌታዬ! ከዚህ ከእርስዎ መ/ቤት ሥራ እንዳለ ይፈልጉልኝና ባይሆን ጉዳዬ ይቅር" ይላቸዋል ባለሥልጣኑም

"ምን ሥራ ትችላለህና ነው ሥራ ፈልግልኝ የምትለኝ ይሉታል። ባለጉዳዩም

"ጌታዬ ቢያቅተኝ ቢያቅተኝ እንደዚህ እንደርስዎ "እሺ ነገ ተመለስ" እያልኩ እዚህ ተቀምጩ ለባለጉዳዮች መልስ መስጠት ያቅተኛል ወይ አለ ይባላል።

* * *

## ሾርባህን አቅምሰኝ

የአንድ ትልቅ ሬስቶራንት ባለቤት የሆነ ሰው እየተዟዟረ ሰራተኞቹን በመቆጣጠር ላይ እያለ በድንገት ወደ ወጥ ቤት ሲገባ የወጥ ቤቱ ኃላፊ ያለሥራ ተቀምጦ ያገኘዋል። በሁኔታው የተናደደው የሬስቶራንቱ ባለቤት በሥራ ሰዓት ተዝናንቶ የተቀመጠውን ወጥ ቤት በመቆጣት ምን እንደተዘጋጀ በቁጣ ይጠይቀዋል። የወጥ ቤቱም ያዘጋጀውን የምግብ ዓይነት እየዘረዘረ መናገር ሲጀምር የሬስቶራንቱ ባለቤት ያቋርጠውና

"በል የሰራኸውን ሾርባ መቅመስ እፈልጋለሁ" ሲል ይጮህበታል። የወጥ ቤት ኃላፊውም "ጌታዬ . . ." ብሎ መናገር ሲጀምር ባለቤቱ አቋረጠውና ወደተጣደው ብረት ድስት ራመድ ብሎ በጭልፋ ጨለፈና ምጥጥ አድርጎ እያጣጣመ "አንተ ሰነፍ አሁን ይህን ነው ሾርባ ብለህ የሰራኸው?" ሲል የስድብ ውርጅብኝ ያወርድበታል። በጌታው ቁጣ የደነገጠው የወጥ ቤትም "ጌታዬ! ይህ እኮ የዕቃ እጣቢ እንጂ ሾርባ አይደለም" አለው ይባላል።

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

ለ6 ተከታታይ እትሞች

| | | | |
|---|---|---|---|
| U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።
በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ____________________

ADDRESS ____________________

CITY ____________ STATE ________ ZIP ____________

PHONE ( _______ ) ____________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ____________________

ADDRESS ____________________

CITY ____________ STATE ________ ZIP ____________

PHONE ( _______ ) ____________

እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን ያስተዋውቁ

| | |
|---|---|
| 1/4 page 3.5" x 4.75 " | 1/8 page 3.5" x 2.25 " |
| 1/2 page 7.25" x 4.75 " | |

**ADVERTISMENT ORDER FORM**

I would like to place an advertisment on LANDAFTA.

Name: ______________________

Address: ______________________

City: ______________________

St. ___ Zip: ____________

Phone: ______________________

PLEASE, MARK THE SPACE BELOW TO INDICATE YOUR CHIOCE LIKE THIS (X)

## SINGLE ISSUE RATES

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

## TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላ
ን
ዳ
ፍ
ታ

Enclosed, please find: 1. A copy of the advertisment to be placed.
2. A check for the amount marked above.

Please, send a copy of the proof before printing. ☐

I Want my ad Translated in Amharic ☐
(no extra fee - please indicate words or phrases to be translated)

For Information, Please Call Advertisment Department:
Publisher at: Phone/Fax (404)728-9122

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359

